# መጽሐፈ ዕዝራ

## መግቢያ

### ዕዝራና ነህምያ

ምንም እንኳ በመጽሐፈ ነህምያ መግቢያ ላይ የሚገኘው "የሐካልያ ልጅ የነህምያ ቃል" (ነህ 1፥1)፣ የሚለው ሐረግ መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፈ ነህምያ፣ በመጀመሪያ ሁለት መጻሕፍት እንደ ነበሩ የሚያመለክት ቢሆንም፣ በጥንት የዕብራይስጥ ቅጆች ላይ ግን አንድ መጽሐፍ ሆነው ቀርበዋል። ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን (ፍላቪየስ ጆሲፈስ፤ 37-100 ዓ.ም.) እና የአይሁድ ታልሙድ ስለ መጽሐፈ ዕዝራ እንጂ ስለ መጽሐፈ ነህምያ አላወሱም። ረጅም ዘመን ያላቸው የሰብዓ ሊቃናት (ሰብቱአጀንት) ቅጆች፣ ዕዝራንና ነህምያን የሚያቀርቡት እንደ አንድ መጽሐፍ አድርገው ነው። ሁለቱን መጻሕፍት 1ኛ ዕዝራና 2ኛ ዕዝራ በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ ከሁለት የከፈላቸው አርጌንስ (185-253 ዓ.ም.) ነው። ጀሮም የላቲኑን ቩልጌት በሚተረጕምበት ጊዜ (390-405 ዓ.ም.)፣ መጽሐፈ ነህምያን ሁለተኛው የኤስድራስ (የዕዝራ) መጽሐፍ ብሎ ሰይሞታል። በዊክሊፍና (1382) በኰቨርዴል የተዘጋጁት (1535) የእንግሊዝኛ ትርጕሞችም መጽሐፈ ዕዝራን፣ "1ኛ ኤስድራስ"፣ መጽሐፈ ነህምያን ደግሞ "2ኛ ኤስድራስ" በማለት ሰይመዋቸዋል። እነዚህ መጻሕፍት በዕብራይስጡ ቅጆች ላይ እንደ ሁለት መጻሕፍት ሆነው ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረቡት በ1448 ዓ.ም. ነው።

### ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጹና ጸሐፊው

እንደ 1ኛ እና 2ኛ ዜና መጻሕፍት ሁሉ፣ የዕዝራና የነህምያ መጻሕፍት የቀረበ ግንኙነት አላቸው። ሁለቱም መጻሕፍት (1) ስለ ቤተ መቅደሱ ዕቃዎች (ዕዝ1፥9-11)፣ (2) ከምርኮ ስለ ተመለሱት ሰዎች (በዚህ ርእስ ላይ ዕዝ 2፤ ነህ 7፥6-73 ጋር ተመሳሳይ ነው)፣ (3) ስለ ዕዝራ የትውልድ ሐረግ (ዕዝ 7፥1-5)፣ (4) ስለ ነገድ አለቆች (ዕዝ 8፥1-14)፣ (5) ከሕዝብ ጋር ስለ ተጋቡት ሰዎች (ዕዝ10፥18-43)፣ (6) ቅጥሩን በመሥራት ስለ ተባበሩትና ስለ ረዱት ሰዎች (ነህ3)፣ (7) ኪዳኑን ስላተሙት (ነህ10፥1-27)፤ (8) በኢየሩሳሌምና በሌሎች ከተሞች ስለሚኖሩት ሰዎች (ነህ11፥3-36) እንዲሁም (9) ስለ ካህናትና ስለ ሌዋውያን (ነህ 12፥1-26) ያወሳሉ።

ከዚህ በተጨማሪ በመጽሐፈ ዕዝራ ውስጥ ሰባት ዐበይት ሰነዶች ወይም ደብዳቤዎች ይገኛሉ (ከመጀመሪያው በስተቀር የቀሩት በሙሉ የተጻፉት በአረማይስጥ ቋንቋ ነው፤ የመጀመሪያው የተጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ነው)። ሰነዶቹም የሚከተሉት ናቸው፤ (1) የቂሮስ ዐዋጅ (1፥2-4)፤ (2) ሬሁምና ተባባሪዎቹ በአይሁድ ላይ ያቀረቡት ክስ (4፥11-16)፤ (3) የቀዳማዊ አርጤክስስ መልስ (4፥17-22)፤ (4) ከተንትናይ የመጣው ዘገባ (5፥7-17)፤ (5) ቂሮስ የሰጠው ትእዛዝ (6፥2-5)፤ (6) ዳርዮስ ለተንትናይ የጻፈው መልስ (6፥6-12) እና (7) ቀዳማዊ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ሥልጣን (7፥12-26)። እነዚህ መዛግብት በፋርስ ዘመነ መንግሥት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ከተጻፉት ከሌሎች ሰነዶችና ደብዳቤዎች ጋር ተመሳሳይ ቅርጽና ይዘት እንዳላቸው ተረጋግጧል።

በመጽሐፈ ዕዝራ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ክፍሎች የራሱ የዕዝራ ታሪክ በመሆናቸው በአንደኛ መደብ ነጠላ ቍጥር ተጽፈዋል (7፥27–28፤8፥1–34፤9)። ሌሎቹ ክፍሎች የተጻፉት ደግሞ በሦስተኛ መደብ ነው (7፥1–26፡10 እንዲሁም ነህ 8 ይመ)። ሥነ ልሳናዊ ትንታኔዎች እንዳረጋገጡት፣ በአንደኛና በሦስተኛ መደብ የተጻፉት ክፍሎች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው በመሆኑ ሁለቱም ክፍሎች የተጻፉት በአንድ ሰው እንደ ሆነ ያመለክታል።

በርካታ ሊቃውንት፣ መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፈ ነህምያ የተጻፉት 1ኛ እና 2ኛ ዜና መዋዕልን በጻፈው ሰው እንደ ሆነ ይናገራሉ። ይህ አመለካከት የተመሠረተው መጽሐፈ ዜና መዋዕልም ሆነ ዕዝራ - ነህምያ የሚጋሩት ተመሳሳይ ነገር አላቸው በሚለው እሳቤ ላይ ነው። ይኸውም በመጽሐፈ ዜና መዋዕል መጨረሻና በመጽሐፈ ዕዝራ መጀመሪያ ላይ የሚገኙት ቍጥሮች የያዙት ተመሳሳይ ሐሳብ ነው። መጽሐፈ ዜና መዋዕልም ሆነ ዕዝራ-ነህምያ ስለ ስም ዝርዝሮች፣ ስለ ሃይማኖታዊ በዓሎች፣ ስለ "ቤተ ሰብ መሪዎች"፣ ስለ "እግዚአብሔር ቤት" ትኵረት በመስጠት ጽፈዋል። በመጻሕፍቱ ውስጥ በተለይ ልዩ ትኵረት የተሰጠው ስለ ሌዋውያንና ስለ ቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ነው። "ዘማሪዎች"፣ "በር ጠባቂዎች" እና "የቤተ መቅደስ አገልጋዮች" የሚሉት ቃላት ብዙ ጊዜ የተጠቀሱት በዕዝራ–ነህምያና በዜና መዋዕል መጻሕፍት ውስጥ ነው። የ1ኛ ዜና መዋዕልን መግቢያ ይመ።

### መጽሐፉ የተጻፈበት ጊዜ

መጽሐፈ ዕዝራ በ440 ዓ.ቅ.ክ ገደማ፣ ነህምያ ደግሞ በ430 ዓ.ቅ.ክ ላይ እንደ ተጻፉ ይገመታል።

### የመጽሐፈ ዕዝራና የመጽሐፈ ነህምያ ቅደም ተከተል

በትውፊታዊው አመለካከት መሠረት ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው (ዕዝ 7፥8)፣ ቀዳማዊ አርጤክስስ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት (458 ዓ.ቅ.ክ.) ሲሆን፣ ነህምያ ደግሞ በ20ኛው ዓመት (445 ዓ.ቅ.ክ. ነህ 2፥1) ነው።


አንዳንዶች ይህን ቅደም ተከተል ገልብጠው ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው በ445 ዓ.ቅ.ክ. ሲሆን፣ ዕዝራ ደግሞ ዳግማዊ አርጤክስስ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት (398 ዓ.ቅ.ክ.) ነው ይላሉ። "በሰባተኛው" (ዕዝራ7፥8) የሚለውን "በሃያ ሰባተኛው" ወይም "በሠላሳ ሰባተኛው" በሚለው በማስተካከል ዕዝራን

ከነህምያ በማስከተል ነው:: ሆኖም ሁለቱም በአንድ ዘመን የነበሩ ሰዎች እንደ ሆኑ ይናገራሉ::

እነዚህ አማራጭ አመለካከቶች ከትውፊታዊው አመለካከት ይልቅ ብዙ ችግር አሉባቸው:: መጽሐፉ እንደሚናገረው ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው ከነህምያ በፊት ነው:: በነህ 8፥9 ላይ (የሙሴ ሕግ ሲነበብ፣) እንዲሁም በነህ 12፥26:36 ላይ (የኢየሩሳሌም ቅጥር ሲመረቅ) ሁለቱም አብረው ተገኝተዋል:: በገጽ 675 ላይ ያለውን የዕዝራ-ነህምያ ቅደም ተከተል የሚለውን ይመ::

**መጽሐፉ የተጻፈበት ቋንቋ**

ከዕዝራ 4፥8-6፥18፤7፥12-26 በስተቀር መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፈ ነህምያ የተጻፉት በዕብራይስጥ ቋንቋ ነው:: እነዚህ ክፍሎች የተጻፉት በፋርስ ዘመነ መንግሥት ዓለም አቀፍ ቋንቋ በነበረው በአረማይስጥ ነው::




**አስተዋፅኦ**

1. ከምርኮ በመጀመሪያ የተመለሱትና የቤተ መቅደሱ መታደስ (ምዕ1-6)
   - ሀ. ከምርኮ በመጀመሪያ የተመለሱት ሰዎች (ምዕ1)
     1. የቂሮስ ዐዋጅ (1፥1-4)
     2. ከሰሳብሳር ጋር የተመለሱት ሰዎች (1፥5-11)
   - ለ. ከምርኮ የተመለሱ ሰዎች ስም ዝርዝር (ምዕ2)
   - ሐ. የቤተ መቅደሱ አምልኮ ማንሰራራት (ምዕ3)
     1. የመሠዊያው እንደ ገና መሠራት (3፥1-3)
     2. የዳስ በዓል (3፥4-6)
     3. የቤተ መቅደሱ ሥራ እንደ ገና መጀመር (3፥7-13)
   - መ. ሕንፃው እንዳይሠራ የተደረገ ተቃውሞ (4፥1-23)
     1. በቂሮስ ዘመነ መንግሥት የተነሣው ተቃውሞ (4፥1-5)
     2. በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት የተነሣው ተቃውሞ (4፥6)
     3. በቀዳማዊ አርጤክስስ ዘመነ መንግሥት የተነሣው ተቃውሞ (4፥7-23)
   - ሠ. የቤተ መቅደሱ ሥራ መፈጸም (4፥24-6፥22)
     1. በዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ሥራው እንደ ገና መጀመሩ (4፥24)
     2. በሐጌና በዘካርያስ አነሣሽነት የታየው አዲስ ጅማሬ (5፥1-2)

3. የአገረ ገዥ የተንትናይ ግልቃ ገብነት (5፥3-5)
4. ለዳርዮስ የተላከው ደብዳቤ (5፥6-17)
5. የቂሮስ ዐዋጅ መፈለግ (6፥1-5)
6. ቤተ መቅደሱ እንዲሠራ ዳርዮስ የሰጠው ትእዛዝ (6፥6-12)
7. የቤተ መቅደሱ እንደገና መፈጸም (6፥13-15)
8. የቤተ መቅደሱ ምረቃ (6፥16-18)
9. የፋሲካ በዓል መከበር (6፥19-22)

2. የዕዝራ መመለስና ያከናወነው የተሐድሶ ሥራ (ም7-10)

ሀ. የዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ (ም7-8)
1. መግቢያ (7፥1-10)
2. ከአርጤክስስ የተሰጠው ሥልጣን (7፥11-26)
3. ዕዝራ ያቀረበው ምስጋና (7፥27-28)
4. ከዕዝራ ጋር ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች ስም ዝርዝር (8፥1-14)
5. የሌዋውያን ለአገልግሎት መፈለግ (8፥15-20)
6. ጾምና ጸሎት (8፥21-23)
7. ንዋየ ቅድሳቱን በኀላፊነት መስጠት (8፥24-30)
8. ወደ ኢየሩሳሌም የተደረገ ጕዞ (8፥31-36)

ለ. ዕዝራ ያከናወነው ተሐድሶ ሥራ (ም 9-10)
1. ከባዕዳን ጋር መጋባት ያስከተለው መዘዝ (9፥1-5)
2. የዕዝራ ንስሓና የምልጃ ጸሎት (9፥6-15)
3. የሕዝቡ ምላሽ (10፥1-4)
4. ሕዝባዊ ለጉባኤ መጠራቱ (10፥5-15)
5. የበደለኞቹ መመርመር (10፥16-17)
6. የበደለኞቹ ስም ዝርዝር (10፥18-43)
7 ከባዕዳን ጋር የተደረገው ጋብቻ መፍረሱ (10፥44)

## ቂሮስ ምርኮኞቹ እንዲመለሱ ፈቀደ

1፥1-3 ተጓ ምብ 2ዜና 36፥22-23

1 ቂሮስ የፋርስ ንጉሥ በሆነ በመጀመሪ
ያው ዓመት እግዚአብሔር የቂሮስን
መንፈስ አነሣሥቶ በመንግሥቱ ሁሉ ዐዋጅ
እንዲያስነግርና ይህም በጽሑፍ እንዲሰፍር
አደረገ፤ ይህ የሆነው በኤርምያስ አፍ የተነ
ገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ
ነው::
2 የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ የሚለው ይህ ነው፤
" 'የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድርን መንግ
ሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል፤ በይሁዳ ምድር በም
ትገኘው በኢየሩሳሌምም ለእርሱ ቤተ መቅደስ
እንድሠራ አዞኛል:: 3 ከሕዝቡ መካከል በእና
ንተ ዘንድ የሚኖር ማናቸውም ሰው አምላኩ
ከእርሱ ጋር ይሁን፤ በይሁዳ ወደምትገኘው ወደ
ኢየሩሳሌም ይውጣና በዚያ ለሚኖረው አምላክ፣
ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
ይሥራ፤ 4 ባለበት ስፍራ የሚቀሩ በየትኛውም
አገር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ በኢየሩሳሌም
ለሚገኘው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስጦታ
እንዲሆን በበጎ ፈቃድ ከሚያቀርቡት መባ

1፥1 ዕዝ6፥22፤7፥27፤ ኤር25፥11-12፤ 29፥ 10-14፤ዘካ1፥12-16
1፥2 መሳ4፥10፤ መዝ72፥11ኢሳ41፥2፡ 25፤44፥28፤45፥13፤ 46፥11፤49፥ 7-23፤ 60፥3፡10፤ ሐጌ1፥2
1፥4 ዘፀ3፥22፤ ዘኍ15፥3፤ዕ3፥7፤ 4፥3፤5፥13፤6፥3፡14፤ መዝ50፥14፤54፥6፤ 116፥17፤72፥8-11፤ ኢሳ10፥20-22፤ ራእ21፥24
1፥5 ቊ1፤ ዘፀ35፥20-22፤2ዜና11፥1፡ 3፡10፡12፡23፤15፥2፡8 9፤ 25፥5፤31፥1፤34፥9፤ 36፥22፤ዕዝ4፥1፤10፥9፤ ነህ11፥4፤12፥34፤ መዝ127፥1፤ሐጌ1፥14፤ ፊል2፥13
1፥6 ዘፀ3፥22
1፥7 2ነገ24፥13፤ 2ዜና36፥7፡10፤ዕዝ5፥14፤ 6፥5፤ ኤር52፥17-19
1፥8 1ዜና3፥18

በተጨማሪ ብርና ወርቅ፣ ዕቃና እንስሳ
በመስጠት ይርዷቸው' "
5 ከዚያም እግዚአብሔር መንፈሳቸውን ያነ
ሣሣው የይሁዳና የብንያም ቤተ ሰብ አለቆች
እንዲሁም ካህናቱና ሌዋውያኑ ሁሉ ለመሄድና
በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ ለመሥራት ተዘጋጁ:: 6 ጎረቤቶቻቸውም
ሁሉ በበጎ ፈቃድ ከሰጡት መባ በተጨማሪ
ከብርና ከወርቅ የተሠሩ ዕቃዎችን፣ ቍሳቍስን፣
እንስሶችንና ሌሎች ጠቃሚ የሆኑ ስጦታዎችንም
በመለገስ ረዷቸው:: 7 ከዚህም በላይ ንጉሡ ቂሮስ፣
ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ወስዶ በአማልክቱ
ቤተ ባዖት[ሀ] ያኖራቸውን የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ ንዋያተ ቅድሳት አወጣ:: 8 የፋርስ ንጉሥ
ቂሮስ በግምጃ ቤቱ ኀላፊ በሚትሪዳጡ አማ
ካይነት ንዋያተ ቅድሳቱ እንዲመጡና በይሁ
ዳው ገዢ በሰሳብሳር ፊት እንዲቈጠሩ አደረገ።
9 የዕቃው ዝርዝር ይህ ነበር፤

| | |
|---|---|
| የወርቅ ሳሕን | 30 |
| የብር ሳሕን | 1,000 |
| ዝርግ የብር ሳሕን[ለ] | 29 |

ሀ7 ወይም፣ *አምላኩ*
ለ9 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም::

*1፥1-3፤* ይህ ክፍል ከ2ዜና መጽሐፍ የመጨረሻዎቹ ሁለት ቍጥሮች ጋር አንድ ዐይነት ነው:: ከዚህም የተነሣ መጻሕፍት ዜና መዋዕል፣ ዕዝራና ነህምያ የተጻፉት እና/ወይም የታረሙት፣ በአንድ ሰው ይኸውም ጸሓፊ ዜና መዋዕል እየተባለ በሚጠራው ሰው እንደሆነ በሰፊው ይነገራል:: ይሁን እንጂ እዚህ ላይ ተደግሞ መገኘቱ የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ጸሓፊ ድርጊቶቹን ባፈጸጸማቸው የጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ለማያያዝ ያደረገው ዘዴ ሳይሆን አይቀርም::

1፥1 ***በመጀመሪያው ዓመት፤*** ንጉሥ ቂሮስ ባቢሎንን በጥቅምት ወር 539 ዓ.ቅ.ክ ላይ ማርኮ ከያዘ በኋላ፣ ከመጋቢት ወር 538 ዓ.ቅ.ክ አንሥቶ ባቢሎንን መግዛት እስከ ጀመረበት ጊዜ ነው:: የፋርስ ግዛተ አፄ መሥራች የሆነው ቂሮስ በፋርስ ላይ የነገሠው ከ559-530 ዓ.ቅ.ክ ነበር:: በኢሳ 44፥28፤ 45፥1 ላይ እግዚአብሔር ቂሮስን "እረኛ" እንዲሁም "የቀባሁት" ይለዋል:: ***በኤርምያስ አፍ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ፤*** ኤርምያስ የሰባ ዓመቱን ምርኮ ተንብዮ ነበር (ኤር 25፥11-12፤ 29፥10):: ሕዝቡ በመጀመሪያ ተማርኮ የሄደው በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት በሦስተኛው ዓመት በ605 ዓ.ቅ.ክ ነበር (ዳን 1፥1):: በ538 ዓ.ቅ.ክ ማለትም በግምት ከሰባ ዓመት በኋላ ወደ ገዛ አገሩ መመለስ ጀመረ::

*1፥2-4፤* ይህ በቃል የተነገረው የቂሮስ ዐዋጅ የተጻፈው በምርኮኞቹ በእስራኤላውያን ቋንቋ ማለትም በዕብራይስጥ ነበር፤ በ6፥3-5 ላይ የሚገኘውና ግልባጩም በቤተ መዛግብት እንዲቀመጥ የተደረገው ዋናው የዐዋጅ ቃል የተጻፈው ግን በአረማይስጥ ቋንቋ ነበር።

1፥2 ***የሰማይ አምላክ፤*** ይህ ሐረግ በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰው ሀያ ሁለት ጊዜ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ዐሥራ ሰባቱ የተጠቀሰው በዕዝራ፣ በነህምያና በትንቢተ ዳንኤል መጻሕፍት ውስጥ ነው:: ***በኢየሩሳሌም ለእርሱ ቤተ መቅደስ፤*** ኢየሩሳሌምና የእግዚአብሔር ቤት በዕዝራና በነህምያ መጻሕፍት ውስጥ ጎልተው የሚታዩ አርእስተ ጒዳዮች ናቸው::

*1፥3፤* ቂሮስ ከእርሱ በፊት እንደ ነበሩት አሦራውያንና ባቢሎናውያን ድል ያደረጓቸውን ሕዝቦች አማልክት ምስል በመውሰድ ፈንታ የሚገዟቸውን ሕዝቦች አማልክት የማያስቈጣ መመሪያ አውጥቶ ነበር:: ለአይሁ ድም ሕዝብ ያሳየው ልግስና ለባቢሎናውያን ከነበረው ቅን አመለካከት ጋር የሚነጻጸር ነበር::

1፥4 ***በየትኛውም አገር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ፤*** ምናልባት ከመስጴጦምያ ለመውጣት ያልፈለጉ አይሁዳውያን ሳይሆኑ አይቀርም:: ***በበጎ ፈቃድ ... በመስጠት፤*** የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና ሥርዐቱ እንደ ገና ሊታደስ የሚችለው በዚህ ዐይነት መሆኑን የሚያመለክት አባባል ነው (2፥68፤ 3፥5፤8፥28 ይመ)::

1፥5 ***የይሁዳና የብንያም፤*** ባቢሎናውያን ከማረኳቸው ከይሁዳ መንግሥት ነገዶች ዋናዎቹ እነዚህ ሁለቱ ነበሩ:: ***የቤተ ሰብ አለቆች፤*** በጥንት ዘመን ቤተ ሰብ ሲባል፣ ከአንድ የዘር ግንድ የወረዱትን ብዙ ቤተሰቦች ያጠቃልል ነበር፤ በአጭሩ ጐሣ እንደ ማለት ነው:: የቤተ ሰቡ መሪ "የቤተ ሰብ አለቃ" ነው (10፥16 ይመ፤ በተጨማሪም 2፥59፤ ነህ 7፥61፤ 10፥34 ይመ)::


*1፥7፤* በጥንት ዘመን ድል ያደረጉ ነገሥታት ድል ያደረጓቸውን ከተሞች አማልክት ምስሎች ማርኮ መውሰድ የተለመደ ነበር:: አይሁድ ግን የእግዚአብሔር ምስል የሚባል ነገር ስላልነበራቸው (የዘፀ. 20፥4 ማብ ይመ)፣ ናቡከደነፆር ይዞ የሄደው የቤተ መቅደሱን ዕቃዎች ብቻ ነበር::

1፥8 ***ሚትሪዳጡ፤*** የፋርሶች ስም ሲሆን፣ ትርጒሙም "ለሚትራ የተሰጠ" ማለት ነው፤ "ሚትራ" በሁለተኛው ምእተ ዓ.ቅ.ክ. በሮማውያን ወታደሮች ዘንድ እጅግ የታወቀ የፋርስ ሰዎች ጣዖት ነበር:: ***ሰሳብሳር፤*** የባቢሎኖች ስም ሲሆን፣ ትርጒሙም "ሲን አባትን ይጠብቅ" ወይም "ሸማሽ ሻሹ አባትን ይጠብቅ" ማለት ነው፤ "ሲን" የጨረቃ አምላክ ሲሆን "ሸማሽ" ወይም "ሻሹ" ደግሞ የፀሓይ አምላክ ነው:: ሰሳብሳር ስሙ የባቢሎናውያን ቢሆንም በሰማርያ አስተዳዳሪ ሥር በነበረችው የይሁዳ ምክትል ገዥ የነበረ አይሁዳዊ ባለሥልጣን ሳይሆን አይቀርም (5፥14 ይመ):: አንዳንድ ሰዎች ሰሳብሳርን ዘሩባቤል ነው ይላሉ፤ ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት የሚከተለው ነው፤ (1) ሁለቱም ሰዎች ገዦች ነበሩ (5፥14፤ ሐጌ 1፥1፤ 2፥2)፤ (2) ሁለቱም የቤተ መቅደሱን መሠረት የጣሉ ሰዎች ነበሩ (3፥2-8፤ 5፥16፤ ሐጌ 1፥14-15፤ ዘካ 4፥6-10)፤ (3) በባቢሎን የነበሩ አይሁድ የባቢሎናውያን "የሹመት" ስም ይሰጣቸው ነበር (ከዳን 1፥7 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (4) የሴፍ ወልደ ኮርዮን (ጆሲፈስ) የተባለው ታሪክ ጸሓፊ፣ በመጽሐፉ ውስጥ ሰሳብሳርንና ዘሩባቤልን አንድ ሰው አድርጎ ያቀረባቸው ይመስላል ("አንቲኪውቲስ" 11.1.3):: ሌሎች ደግሞ የአዋልድ መጻሕፍት ሁለት የተለያዩ ሰዎች አድርገው ስለሚያቀርቧቸው (1ዕዝራ ካልዕ 6፥18)፣ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ናቸው ይላሉ:: ከዚህም በላይ ከምርኮ በሚመለሱበት ጊዜ፣ የሰሳብሳር ዕድሜ ትልቅ የዘሩባቤል ደግሞ ትንሽ ሳይሆን አይቀርም:: እንዲሁም ሰሳብሳር የመንግሥት ባለሥልጣን፣ ዘሩባቤል ግን አንድ የታወቀ መሪ ብቻ ሊሆን ይችላል (3፥8-11):: በሌላ በኩል ደግሞ የዘሩባቤል ስም ከሊቀ ካህናቱ ከኢያሱ ስም ጋር አብሮ ሲጠቀስ፣ ከሰሳብሳር ጋር ግን አንድም ካህን አልተጠቀሰም:: የቤተ መቅደሱ መሠረት በ536 ዓ.ቅ.ክ. ሲጣል፣ ሰሳብሳር የሥራው መሪ ቢሆንም፣ የተሠራው ሥራ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ፣ ከዐሥራ ስድስት ዓመት በኋላ የቤተ መቅደሱ መሠረት ለሁለተኛ ጊዜ ሲሠራ ዘሩባቤል ሥራውን መምራት ነበረበት (ሐጌ 1፥14-15፤ዘካ 4፥6-10 ይመ):: ከዚህም በቀር ሰሳብሳርና ሺናጻር (1ዜና 3፥18) የአንድ ሰው ስም መሆኑን የሚናገሩ አሉ፤ ይህ ሼናጻር የተባለው ሰው የንጉሡ የኢኮንያን አራተኛ ወንድ ልጁ ነበር:: ይህ እንዲህ ከሆነ፣ ዘሩባቤል የሰሳብሳር የወንድም ልጅ ነበር ማለት ነው (3፥2 ከ1ዜና 3፥18 ጋር ያነጻጽሩ)::

*1፥9-11፤* አሦራውያንና ባቢሎናውያን ድል ሲያደርጉ፣ ድል ያደረጓቸውን ሕዝቦች ንብረት ዘርፈው ሲሄዱ ጸሐፊዎቻቸው ደግሞ በምርኮ የተበዘበዘውን የዕቃ ዝርዝር በጥንቃቄ ይመዘግቡ ነበር:: በቍ 9-10 ላይ የተዘረዘረው የዕቃ ብዛት 2499 እንጂ፣ በቍ 11 ላይ

## የሁነቶች/የጊዜ ቅደም ተከተል ዕዝራ–ነህምያ

ከዚህ በታች የቀረቡ ቀናት እንደ ዕብራውያኑ አቈጣጠር ነው




| ዓመት | ወር | ቀን 2 | ክስተት | የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል |
|---|---|---|---|---|
| 539 | ጥቅምት | 15<br>2 | የባቢሎን መማረክ | ዳን 5፥30 |
| 538<br>537 | ከመጋቢት<br>እስከ መጋቢት | | የቂሮስ የመጀመሪያ ዓመት | ዕዝ 1፥1-4 |
| 537(?) | | | ከምርኮ መመለስ | ዕዝ 1፥11 |
| 537 | 7ኛ | | የመሠዊያው መሠራት | ዕዝ 3፥1 |
| 536 | 2ኛ | | የቤተ መቅደሱ ሥራ ተጀመረ | ዕዝ 3፥8 |
| 536ጠ530 | | | በቂሮስ ዘመን የተነሣ ተቃውሞ | ዕዝ 4፥1-5 |
| 530ጠ520 | | 24<br>11 | የቤተ መቅደሱ ሥራ መቆም | ዕዝ 4፥24 |
| 520 | 6ኛ<br>= መስከረም | 3<br>3 | በዳርዮስ ዘመን<br>የቤተ መቅደሱ ሥራ ተጀመረ | ዕዝ 5፥2፤<br>ሐጌ 1፥14 |
| 516 | 12ኛ<br>= መጋቢት | 1<br>30 | የቤተ መቅደሱ ሥራ ተጠናቀቀ | ዕዝ 6፥17 |
| 458 | 1ኛ<br>= መጋቢት | 1<br>28 | የዕዝራ ከባቢሎን መውጣት | ዕዝ 7፥6-9 |
| | 5ኛ<br>= ሐምሌ | 20<br>19 | የዕዝራ ኢየሩሳሌም መድረስ | ዕዝ 7፥8-9 |
| | 9ኛ<br>= ታህሳስ | 1<br>19 | የህዝብ ጉባዔ | ዕዝ 10፥9 |
| | 10ኛ<br>= ታህሳስ | 18 | የምርመራው ጅማሬ | ዕዝ 10፥16 |
| 457 | 1ኛ<br>= መጋቢት | 5<br>24 | የምርመራው ፍጻሜ | ዕዝ 10፥17 |
| 445<br>444 | ከሚያዝያ እስከ<br>መጋቢት | | የቀዳማዊ አርጤክስስ 20ኛ ዓመት | ነህ 1፥1 |
| 445 | 1ኛ =<br>ከመጋቢት· ሚያዝያ | | የነህምያ ወደ ንጉሡ መግባት | ነህ 2፥1 |
| | = ነሐሴ (?) | 25<br>11 | የነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም መድረስ | ነህ 2፥11 |
| | 6ኛ<br>= መስከረም | 27<br>25 | የቅጥሩ ሥራ መጠናቀቅ | ነህ 6፥15 |
| | 7ኛ=መስከረም<br>እስከ ጥቅምት | 15 ጠ 22<br>12 ጠ 18 | የሕዝብ ጉባዔ | ነህ 7፥73-8፥1 |
| | 7ኛ<br>= ጥቅምት | 24<br>20 | የዳስ በዓል | ነህ 8፥14 |
| | 7ኛ<br>= ጥቅምት | 23<br>3 | ጾም | ነህ 9፥1 |
| 433<br>432 | መጋቢት<br>እስከ ሚያዝያ | | የአርጤክስስ 32ኛ ዓመት፤<br>የነህምያ በንጉሡ መጠራትና መመለሱ | ነህ 5፥14፤13፥6 |

10ጐድጓዳ የወርቅ ሳሕን 30
ባለ ግጣም የብር
ጐድጓዳ ሳሕን 410
ሌሎች ቈሳቍስ 1000
11ባጠቃላይ አምስት ሺህ አራት መቶ
የወርቅና የብር ዕቃዎች ነበሩ። ሰሳብሳር ምር
ኮኞቹ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ
ይህን ሁሉ ዕቃ ይዞ ወጣ።

### ወደ አገራቸው የተመለሱ ምርኮኞች ዝርዝር

2፥1-70 ተጓ ምብ ነህ 7፥6-73

2 የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ወደ ባቢሎን
ማርኮ ከወሰዳቸው መካከል ከምርኮ ተመል
ሰው ወደየራሳቸው ከተሞች፣ ወደ ይሁዳና ወደ
ኢየሩሳሌም የመጡት የአገሩ ልጆች እነዚህ ናቸው፤
2የመጡትም ከዘሩባቤል፣ ከኢያሱ፣ ከነህምያ፣
ከሠራያ፣ ከረዕላያ፣ ከመርዶክዮስ፣ ከበላሳን፣
ከመሴፋር፣ ከበጉዋይ፣ ከሬሁም፣ ከበዓና ጋር
ነበር።

የተመለሱት የእስራኤል ሰዎች ዝርዝር
የሚከተለው ነው፤

3የፋሮስ ዘሮች 2,172
4የሰፋጥያስ ዘሮች 372
5የኤራ ዘሮች 775
6ከኢያሱና ከኢዮአብ ዘር
የሆኑት የፈሐት ሞዓብ ዘሮች 2,812
7የኤላም ዘሮች 1,254
8የዛቱዕ ዘሮች 945
9የዘካይ ዘሮች 760
10የባኒ ዘሮች 642
11የቤባይ ዘሮች 623
12የዓዝጋድ ዘሮች 1,222
13የአዶኒቃም ዘሮች 666
14የበጉዋይ ዘሮች 2,056
15የዓዲን ዘሮች 454
16የሕዝቅያስ ልጅ የአጤር ዘሮች 98
17የቤሳይ ዘሮች 323
18የዮራ ዘሮች 112
19የሐሱም ዘሮች 223
20የጋቤር ዘሮች 95
21የቤተ ልሔም ሰዎች* 123
22የነጦፋ ሰዎች 56
23የዓናቶት ሰዎች 128
24የዓዝሞት ዘሮች 42
25የቂርያትይዓሪም**፣
የከፊራና የብኤሮት ዘሮች 743
26የራማና የጌባ ዘሮች 621
27የማክማስ ሰዎች 122
28የቤቴልና የጋይ ሰዎች 223
29የናባው ዘሮች 52
30የመጌብስ ዘሮች 156
31የሌላው ኤላም ዘሮች 1,254
32የካሪም ዘሮች 320
33የሎድ፣ የሐዲድና
የኦኖም ዘሮች 725
34የኢያሪኮ ሰዎች 345
35የሴናዓ ዘሮች 3,630
36ካህናቱ፦
ከኢያሱ ቤተ ሰብ
የዮዳኤ ዘሮች 973

2፥1 ቍ70፤ 2ነገ24፥16፤25፥12፤ 1ዜና9፥2፤2ዜና36፥20፤ ነህ7፥73፤11፥3
2፥2 1ዜና3፥19፤ 6፥14፤ዕዝ3፥2፤5፥2፤ 10፥18፤ነህ10፥2፤ 11፥11፤12፥1፡8፤ ሐጌ1፥1፡12፤2፥4፤ ዘካ3፥1-10፤ 6፥9-15፤ ማቴ1፥12፤ሉቃ3፥27
2፥3 ዕዝ8፥3፤ 10፥25፤ ነህ3፥25
2፥13 ዕዝ8፥13
2፥21 ሚክ5፥2
2፥26 ኢያሱ18፥25
2፥28 ዘፍ12፥8
2፥34 1ነገ16፥34፤ 2ዜና28፥15
2፥36 1ዜና24፥7

*21 ወይም *ልጆች፣ ዘሮች*
**25 የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም (እንዲሁም ነህ 7፥29 ይመ)፤ ዕብራ ይስጡ ግን፣ ቂሪያት አሪም ይላል።

እንደ ተገለጸው 5400 አይደለም። ይህ የሆነው ምናልባት ትልቅና ውድ የሆኑትን ዕቃዎች ብቻ ስለመዘገቡ ሊሆን ይችላል።

*1፥11፤* ሰሳብሳር በ537 ዓ.ቅ.ክ ስላደረገው ጉዞ የሚገልጽ ዝርዝር መግለጫ አልተሰጠንም። በኋላ ግን ዕዝራ ካደረገው ጉዞ (7፥8-9) ለመረዳት እንደሚቻለው፣ መንገዱ አራት ወር ያህል ይፈጅ ነበር። በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ካርታ ቁ 7 ይመ።

*2፥1-70፤* በም 2 ላይ የተጠቀሰው ዝርዝር አብዛኛው በነህ 7፥6-73 ላይ ካለው ዝርዝር ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው (በተጨማሪም በአዋልድ መጽሐፍ ላይ 1ኛ ኢድራስ 5፥4-46 ይመ)። የየመንደሩ ስም ዝርዝር እንደሚያመለክተው፣ ሰዎቹ የተወለዱባቸውን ቦታዎች አልረሱም። ከዚህም በላይ ከምርኮ የተመለሱት ከየነገዱ፣ ከየቀበሌውና ከየከተማው እንደ ነበሩ ያመለክታል። በዚህ ክፍል ያለው ዝርዝር ከነህ 7 ጋር ሲነጻጸር ብዙ የስምና የቍጥር ልዩነት እንዳለው ያሳያል። ለምሳሌ በዕዝራና በነህምያ መጻሕፍት መካከል እንኳ ሀያ በመቶ ያህል የቍጥር ልዩነት አለ። እነዚህ ልዩነቶች ሊፈጠሩ የቻሉት ቍጥሮች በምስጢራዊ ትእምርቶች ከመጻፋቸው የተነሣ ነው፤ ይኸውም በመጀመሪያው ቅጆች ላይ አምዳዊ ነቍጣዎችን ለአንድ፣ አግድማዊ ነቍጣዎችን ለዐሥር መጠቀማቸው ቅጆችን የሚገለብጡ ሰዎች ስሕተት እንዲፈጽሙ ሳያደርጋቸው አልቀረም።

2፥1 *የክፍለ አገሩ፤* ምናልባት ይሁዳን ነው (ከ5፥8 ጋር ያነጻጽሩ፤ በተጨማሪም ነህ 1፥3 ይመ)።

2፥2 *ከዘሩባቤል፤* የ3፥2፤ 5፥2 ማብ ይመ። *ከኢያሱ፤* የስሙ ትርጉም፣ "እግዚአብሔር ያድናል" ማለት ነው። በግሪኩ "ኢየሱስ" ማለት ነው (የማቴ 1፥21 አማራጭ ትርጉሙን ይመ)። *ከነህምያ፤* ይህ ነህምያ በነህምያ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው ሰው አይደለም። *ከመርዶክዮስ፤* "ማርዱክ" ከተባለው የባቢሎን ጣዖት የተገኘ ስም ነው (ከኤር 50፥2 ጋር ያነጻጽሩ)። የንግሥት አስቴር አጎትም በዚህ ስም ይጠራ ነበር (አስ 2፥7)።

2፥3 *የፋሮስ፤* "ቍንጫ" ማለት ነው (በእስራኤላውያን ዘንድ በተባዮችና በእንስሳት ስም መጠራት የተለመደ ነበር)። የዚህ ቤተ ሰብ አባላትና ሌሎችም በቍ 6-14 የተጠቀሱት ቤተ ሰቦች ከዕዝራ ጋር ተመልሰዋል (8፥3-14)።

2፥5 *የኤራ፤* ምናልባት፣ "የዱር በሬ" ማለት ይሆናል፤ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እንዲህ ያለው ስም እምብዛም አይታወቅም፤ ነገር ግን በመስጴጦምያ ሰነዶች ላይ ስሙ በመገኘቱ በምርኮ ዘመን የተወረሰ ሳይሆን አይቀርም።

2፥6 *ፈሐት ሞዓብ፤* ትርጉሙ፣ "የሞዓብ ገዥ" ማለት ሲሆን፣ ይህ ስም ምናልባት በአንድ ወቅት የማዕረግ ስም ሆኖ ሳያገለግል አልቀረም።

2፥12 *ዓዝጋድ፤* ከ8፥12 ጋር ያነጻጽሩ፤ የቃሉ ትርጉም፣ "ጋድ ብርቱ ነው" ማለት ሲሆን፣ ይህ ስም ምናልባት 'ጋድ' ከተባለው ከዕድል ወይም ከጋድ አምላክ ጋር (ኢሳ 65፥11) ወይም ከዮርዳኖስ ማዶ ከሰፈረው ከጋድ ነገድ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል።

2፥16 *የአጤር፤* በመሳ 3፥15፤ 20፥16 ላይ እንደተገለጸው የስሙ ትርጉም፣ "ግራኝ" ማለት ነው።

*2፥21-35፤* ከቍ 3-20 ያለው የቤተ ሰብ ስም ዝርዝር ሲሆን፣ ከቍ 21-35 ያለው ግን ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን በብንያም ምድር የሚገኙት የመንደርና የከተማ ስሞች ዝርዝር ነው። ከይሁዳ በስተ ደቡብ በነጌብ የነበሩ ከተሞች አለመጠቀሳቸው አስገራሚ ነገር ነው። ናቡከደነፆር ይሁዳን በ597 ዓ.ቅ.ክ በወረረ ጊዜ (ኤር 13፥19)፣ የኤዶምያስ ሰዎች ሁኔታውን በመጠቀም ያንን ስፍራ ሊይዙ ችለዋል (ትንቢተ አብድዩ ይመ)።

2፥21 *የቤተልሔም ሰዎች፤* ጌታ ኢየሱስ የተወለደው ከእነዚሁ ከምርኮ ከተመለሱት የቤተልሔም ሰዎች ዘር ሊሆን ይችላል።

2፥23 *የዓናቶት፤* የኤር 1፥1 ማብ ይመ።

2፥28 *የቤቴልና፤* የዘፍ 12፥8 ማብ ይመ። እንደ ቤቴል፣ ምጽጳ፣ ገባዖንና ጊብዓን የመሳሰሉት ከተሞች፣ ከባቢሎናውያን ወረራ ያመለጡ ይመስላል፤ ሆኖም ቤቴል፣ የባቢሎን ሰራዊት ለቆ የፋርስ ሰራዊት በእግሩ ሲተካ ወድማለች። በዕዝራ ዘመን በዚሁ ስፍራ አንዲት አነስተኛ መንደር እንደ ተገኘች የታሪክ ቅርሶች ጥናት ያረጋግጣል።

*2፥31፤* ቍ 7 ይመ።

2፥33 *የሎድ፤* የአሁኗ ልዳ ናት።

*2፥35 የሴናዓ፤* ከምርኮ ከተመለሱት ሰዎች ከፍተኛው ቍጥር (3630) ከሴናዓ ጋር የተያያዘ ነው፤ ይህ ቍጥር በነህ 7፥38 ላይ 3930 ተብሎ ተመዝግቧል። ስሙ እንደሚያመለክተው፣ እነዚህ ሰዎች ከአንድ ቦታ የመጡ ወይም ከአንድ ቤተ ሰብ የተገኙ ሳይሆኑ፣ በማኅበራዊ ኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ ስፍራ የነበራቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

*2፥36-39፤* አራት የካህናት ጕሣዎች የተጠቀሱበት ክፍል ነው፤ ቍጥራቸውም 4289 ሲሆን፣ ከጠቅላላው ሕዝብ አንድ ዐሥረ

37 የኢሜር ዘሮች 1,052
38 የፋስኮር ዘሮች 1,247
39 የካሪም ዘሮች 1,017
40 ሌዋውያኑ፡-
በሆዳይዋ በኩል የኢያሱና
የቀድምኤል ዘሮች 74
41 መዘምራኑ፡-
የአሳፍ ዘሮች 128
42 የቤተ መቅደሱ በረኞች፡-
የሰሎም፣
የአጤር፣ የጤልሞን፣
የዓቁብ፣ የሐጢጣና
የሶባይ ዘሮች 139
43 የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች፡-
የሲሐ፣ የሐሡፋና የጠብዖት ዘሮች፤
44 የኬራስ፣ የሲዓ፣ የፋዶን ዘሮች፤
45 የልባና፣ የአጋባ፣ የዓቁብ ዘሮች፤
46 የአጋብ፣ የሰምላይ፣ የሐናን ዘሮች፤
47 የጊዴል፣ የጋሐር፣ የራያ ዘሮች፤
48 የረአሶን፣ የኔቆዳ፣ የጋሴም ዘሮች፤
49 የዖዛ፣ የፋሴሐ፣ የቤሳይ ዘሮች፤
50 የአስና፣ የምዑናውያን፣ የንፉሰሲም ዘሮች፤
51 የበቅቡቅ፣ የሐቁፋ፣ የሐርሑር ዘሮች፤
52 የበስሉት፣ የምሒዳ፣ የሐርሳ ዘሮች፤
53 የበርቆስ፣ የሲሣራ፣ የቴማ ዘሮች፤
54 የንስያና የሐጢፋ ዘሮች፤
55 የሰሎሞን አገልጋዮች ዘሮች፡-
የሶጣይ፣ የሶፌሬት፣ የፍሩዳ ዘሮች፤
56 የየዕላ፣ የደርቆን፣ የጊዴል ዘሮች፤
57 የሰፋጥያስ፣ የሐጢል፣ የፈክራት፣የሐፂ
ቦይም፣ የአሚ ዘሮች፤
58 የቤተ መቅደሱ አገልጋዮችና የሰሎሞን
አገልጋዮች ዘሮች 392
59 ከዚህ የሚከተሉት ደግሞ ከቴልሜላ፣
ከቴላሬሳ፣ ከክሩብ፣ ከአዳንና ከኢሜር ከተሞች
የመጡ ናቸው፤ ነገር ግን ቤተ ሰቦቻቸው የእስ
ራኤል ዘር መሆናቸውን ማስረዳት አልቻሉም፤
60 የዳላያ፣ የጦብያና የኔቆዳ፣ ዘሮች 652
61 ከካህናቱ መካከል የኤብያ፣ የአቆስና የቤ
ርዜሊ ዘሮች፤ ቤርዜሊ በዚህ ስም ሊጠራ የቻ
ለው የገለዓዳዊውን የቤርዜሊን ልጅ አግብቶ
ስለ ነበር ነው።
62 እነዚህ በትውልድ መዝገቡ ውስጥ የቤተ
ሰቦቻቸውን ዝርዝር ፈለጉ፤ ነገር ግን ማግኘት አል
ቻሉም፤ ስለዚህ እንዳልነጹ ተቈጥረው፣ ከክ
ህነት አገልግሎት ተገለሉ። 63 አገረ ገዡውም
በኡሪምና በቱሚም እግዚአብሔርን የሚጠይቅ
ካህን እስኪነሣ ድረስ፣ እጅግ ከተቀደሰው
ምግብ እንዳይበሉ አዘዛቸው።
64 ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች ብዛት 42,360
ነበረ፤ 65 ይህም 7,337 ከሚሆኑት ከወንዶችና
ከሴቶች አገልጋዮቻቸው በተጨማሪ ነው፤ 200

2፥37 1ዜና24፥14
2፥38 1ዜና9፥12
2፥39 1ዜና24፥8
2፥40 ዘፍ29፥34፤ ዘኍ3፥9፤ዘዳ18፥6-7፤ 1ዜና16፥4፤ዕዝ7፥7፤ 3፥9፤8፥15፤ነህ12፥24
2፥41 1ዜና15፥16
2፥42 1ሳሙ3፥15፤ 1ዜና9፥17
2፥43 1ዜና9፥2፤ ነህ11፥21
2፥58 1ዜና9፥2
2፥59 ዘኍ1፥18
2፥61 2ሳሙ17፥27
2፥62 ዘኍ3፥10፤ 16፥39-40
2፥63 ዘፀ28፥30፤ ዘሌ2፥3፡10
2፥65 2ሳሙ19፥35

ኛውን ይይዛሉ።

2፥40 *ሌዋውያኑም፤* በዘሌዋውያን መግቢያ ላይ "አስያየሙ" የሚለውን ይመ። ከምርኮ የተመለሱት ሌዋውያን በቍጥር ከሌላው በጣም አነስተኛ ናቸው (ከ8፥15 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ሌዋውያኑ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበራቸው የሥራ ድርሻ ተራ ስለነበር፣ አብዛኞቹ በምርኮ አገር የነበረውን ኑሮ ወደው፣ እዚያው መቅረቱን ሳይመርጡ አልቀሩም።

2፥41 *የአሳፍ፤* ዳዊት ለቤተ መቅደሱ መዘምራን አለቃ አድርጎ ከሾማቸው (1ዜና 25፥1፤ 2ዜና 5፥12፤ 35፥15) ከሦስቱ ሌዋውያን አንዱ ነው፤ የመዘምራኑ ተግባር በ1ዜና 15፥16-24 ላይ ተዘርዝሮአል።

*2፥42 በረኞች፤* በአብዛኛው ሌዋውያን ናቸው (1ዜና 9፥26፤ 2ዜና 23፥4፤ 35፥15፤ ነህ 12፥25፤ 13፥22)። በዕዝራና በነህምያ መጻሕፍት ውስጥ 16 ጊዜ፣ በመጻሕፍተ ዜና መዋዕል ደግሞ 19 ጊዜ ተጠቅሰዋል። ዋናው ሥራቸው የቤተ መቅደሱን በርና የቅጥር ግቢውን መዝጊያ መክፈትና መዝጋት (1ዜና 9፥17-27) እንዲሁም ሌሎች ተራ ሥራዎችን ማከናወን ነበር (1ዜና 9፥28-32፤ 2ዜና 31፥14)።

*2፥43-57፤* የቤተ መቅደሱ አገልጋዮችና የሰሎሞን አገልጋዮች ዝርያዎች ጠቅላላ ቍጥር 392 ነበር (ቍ 58)፤ ይህም ከመዘምራኑና ከበር ጠባቂዎቹ ሌዋውያን አጠቃላይ ቍጥር (ቍ 40-42) ይበልጣል።

2፥46 *የሐናን፤* የስሙ ትርጕም፣ "(እግዚአብሔር) ቸር ነው" ማለት ሲሆን፣ በብሉይ ኪዳን "ቸር መሆን" የሚለው ግሥና ከዚሁ የተገኙት ቃላት ለብዙ ሰዎች የተጸውዖ ስም ሆነዋል። ለምሳሌ ዮሐናን ("እግዚአብሔር ቸር ነው"፤ 8፥12 ይመ) አንዱ ሲሆን፣ በአማርኛ "ዮሐንስ" የሚለው ስም ከዚሁ የመጣ ነው።

2፥51 *በቅቡቅ፤* የስሙ ትርጕም "ገምቦ" ማለት ሲሆን፣ ለወፍራምና ለቦርጫም ሰው የተሰጠ የቅጽል ስም ሳይሆን አይቀርም። በኤር 19፥1፡10 ላይ "ገምቦ" ተብሎ ከተተረጐመው ጋር ያነጻጸሩ፤ በኤር 19፥7 ላይ "አፈርሳለሁ" ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል ከዚህ (ከበቅቡቅ) ጋር አንድ ነው።

2፥53 *የበርቆስ፤* "የቆስ ልጅ" ማለት ነው (ወይም የዔዶማውያን ጣዖት "ቄስ" ነው።)

2፥55-58፤ *የሰሎሞን አገልጋዮች ዘሮች፤* ይህ አባባል የሚገኘው በዚህ ክፍልና በነህ 7፥57፡60፤ 11፥3 ላይ ብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች ምናልባት ንጉሥ ሰሎሞን ገባሮች ያደረጋቸው የከነዓናውያን ዝርያዎች ሳይሆኑ አይቀሩም (1ነገ 9፥20-21)።

2፥55 *የሶፌሬት፤* ምናልባት፣ "የጸሓፊው ተግባር" ማለት ሊሆን ይችላል፤ በአንድ ወቅት ለጸሓፊዎች የተሰጠ የማዕረግ ስም ሳይሆን አይቀርም።

*2፥59-63፤* የዘር ሐረጋቸውን በትክክል መቍጠር ያልቻሉ ግለሰቦች ናቸው።

2፥59 *ከቴልሜላ፤* የስሙ ትርጕም፣ "የጨው ቍልል" ማለት ነው፤ ምናልባት ጨው የተነሰነሰበት ስፍራ ሊሆን ይችላል (መሳ 9፥45 እና ማብ ይመ)። "ቴል" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ለተቈለለ ነገር የሚውል ሲሆን በከተማ ፍርስራሽ የሚፈጠረውን ስፍራ ያመለክታል (የኢሱ 11፥13 ማብ ይመ)። የተጋዙት አይሁዳውያን ምርኮኞች እንዲሰፍሩ የተደረገው በኮቦር ወንዝ አካባቢ ነበር (ሕዝ 1፥1)፤ ይህ ስፍራ የሚገኘው በደቡብ መስጴጦምያ የዐማፂዎች ምሽግ በነበረችው በኒጱር ከተማ ሳይሆን አይቀርም። የአይሁድ ሕዝብ እንዲሰፍር የተደረገው፣ ባቢሎናውያን የፍርስራሽ ክምር ባደረጓቸው ከተሞች ሊሆን ይችላል። *ከተሞች፤* ባቢሎናውያን የአይሁድን ሕዝብ ያሰፈሩባቸው በመስጴጦምያ የሚገኙ ቦታዎች ናቸው።

2፥61 *ቤርዜሊ፤* የስሙ ትርጕም፣ "የብረት ሰው" ማለት ነው። በዚህ ስም ስለተጠሩ ሰዎች 2ሳሙ 17፥27-29፤ 19፥31-39፤ 1ነገ 2፥7 ይመ።

2፥63 *አገረ ገዡውም፤* ምናልባት ሰሳብሳርን ወይም ዘሩባቤልን ሊሆን ይችላል (የ1፥8 ማብ ይመ)። *ኡሪምና ቱሚም፤* የዘፀ 28፥30 ማብ ይመ።

2፥64 *42360፤* ድምሩ ከተሰጡት ከሌሎቹ ቍጥሮች በላይ ነው፤

| ምድብ | ዕዝራ | ነህምያ | 1ኢስድራስ |
|---|---|---|---|
| የእስራኤል ሰዎች | 24,144 | 25,406 | 25,947 |
| ካህናት | 4,289 | 4,289 | 5,288 |
| ሌዋውያን፣ መዘምራን፣ በር ጠባቂዎች፣ የቤተ መቅደስ አገልጋዮች፣ የሰሎሞን አገልጋዮች ዘሮች | 392 | 392 | 372 |
| ትውልዳቸው የማይታወቅ ሰዎች | 652 | 642 | 652 |
| ድምር | 29,818 | 31,089 | 32,600 |

ከ10,000-12,000 የሚደርሰው ይህ ልዩነት እንዴት እንደመጣ መናገር አስቸጋሪ ነው። ቍጥሩ የሚያመለክተው ስማቸው ያልተጠቀሰውን ከ10,000-12,000 የሚደርሱትን ሴቶችና ሕፃናት ሊሆን ይችላል፤ ከዚህ በተጨማሪ በቍ 61-63 ላይ የተጠቀሱትንና ትውልዳቸው በውል የማይታወቀውን ካህናት እንደሚጨምር ምንም ጥርጥር የለውም። አንዳንድ ሊቃውንት እንደሚናገሩት ቍጥራቸው በግልጽ የተጠቀሰው፣ ከይሁዳና ከብንያም ወገን የሆኑት ተመላሾች ሲሆኑ፣ የቀሩት ደግሞ ከሌሎች ወገን ናቸው።

*2፥65 ከወንዶችና ከሴቶች አገልጋዮቻቸው፤* የአገልጋዮቹ ቍጥር ከሌሎቹ ጋር ሲነጻጸር አንድ ለስድስት ይሆናል፤ ይህም ከፍተኛ

ወንድና ሴት ዘማሪዎችም ነበሯቸው:: [66]736
ፈረሶች፣ 245 በቅሎዎች፣ [67]435 ግመሎችና
6,720 አህዮች ነበሯቸው::
[68]በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ወደ እግዚ
አብሔር ቤት በደረሱ ጊዜ፣ አንዳንድ የቤተ
ሰብ መሪዎች፣ በቀድሞው ቦታ እንደ ገና
ለሚሠራው የእግዚአብሔር ቤት በበጎ ፈቃድ
ስጦታ አደረጉ። [69]እንደየችሎታቸውም 61,000
የወርቅ ዳሪክ[ሠ]፣ 5,000 ምናን[ረ] ብር፣ 100
ልብሰ ተክህኖ ለግምጃ ቤቱ ሰጡ::
[70]ካህናቱ፣ ሌዋውያኑ፣ መዘምራኑ፣ በር ጠባ
ቂዎቹና የቤተ መቅደስ አገልጋዮቹ፣ ከሌ
ሎች ሰዎች ጋር በየራሳቸው ከተሞች ሰፈሩ፤ የቀ
ሩት እስራኤላውያንም በየከተሞቻቸው ተቀመጡ::

## መሠዊያው እንደ ገና ተሠራ

**3** ሰባተኛው ወር በደረሰ ጊዜ፣ እስራኤላ
ውያን በየከተሞቻቸው ሳሉ፣ ሕዝቡ እንደ
አንድ ሰው ሆነው በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ::
[2]ከዚያም የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱና ካህናት
ዘመዶቹ እንዲሁም የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤልና
የሥራ ባልደረቦቹ፣ በእግዚአብሔር ሰው በሙሴ ሕግ
በተጻፈው መሠረት የሚቃጠል መሥዋዕት ለማ
ቅረብ፣ የእስራኤልን አምላክ መሠዊያ መሥራት
ጀመሩ:: [3]በዙሪያቸው ካሉት አሕዛብ የተነሣ
ፍርሀት ቢያድርባቸውም፣ መሠዊያውን በቀድ
ሞው መሠረት ላይ ሠሩ፤ በመሠዊያውም
ላይ ጠዋትና ማታ የሚቀርበውን የሚቃጠል
መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረቡ:: [4]ከዚያም
ለእያንዳንዱ ቀን እንደ ታዘዘው፣ በሚያስፈልገው
ቍጥር ልክ የሚቃጠል መሥዋዕት በማቅረብ
የዳስ በዓልን በተጻፈው መሠረት አከበሩ:: [5]ከዚ
ያም በኋላ መደበኛውን የሚቃጠል መሥዋዕት፣
የወር መባቻን መሥዋዕት፣ በተቀደሱት የእግ
ዚአብሔር በዓላት የሚቀርበውን መሥዋዕትና
በበጎ ፈቃድ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን መባ
አቀረቡ:: [6]የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሠ
ረት ገና ያልተጣለ ቢሆንም፣ በሰባተኛው ወር
በመጀመሪያው ቀን ለእግዚአብሔር የሚቃጠል
መሥዋዕት አቀረቡ::

## ቤተ መቅደሱ እንደገና ተሠራ

[7]ከዚያም ለድንጋይ ጠራቢዎችና ለዐናጢ
ዎች ገንዘብ ሰጡ፤ ከፋርስ ንጉሥ ከቂሮስ
በተፈቀደው መሠረት የዝግባ ዛፎች ከሊባኖስ
ወደ ኢዮጴ በባሕር እንዲያመጡላቸው፣ ለሲ
ዶናና ለጢሮስ ሰዎችም ምግብ፣ መጠጥና
ዘይት ሰጡ::
[8]ኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ወደ እግዚአ
ብሔር ቤት በደረሱ በሁለተኛው ዓመት
በሁለተኛው ወር፣ የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤ
ልና የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱ እንዲሁም
የቀሩት ወንድሞቻቸው (ካህናቱ፣ ሌዋውያኑ፣
ከምርኮ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት ሁሉ)
ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ የሆናቸው ሌዋው
ያን የእግዚአብሔርን ቤት ሕንጻ ሥራ እንዲቈጣጠሩ
ሾሟቸው፤ ሥራውንም ጀመሩ:: [9]ኢያሱ፣ ወንዶች
ልጆቹና ወንድሞቹ፣ የዮሐዳዩ[ሰ] ዘሮች ቀድ
ምኤልና ወንዶች ልጆቹ፣ የኤንሐዳድ ወንዶች
ልጆች፣ ልጆቻቸውና ወንድሞቻቸው፣ ሌዋውያ
ኑም ሁሉ የእግዚአብሔርን ቤት የሚሠሩትን ሰዎች
ለመቈጣጠር በአንድ ላይ ሆኑ::
[10]ግንበኞቹ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ
መሠረት በጣሉ ጊዜ፣ ካህናቱ ልብሰ ተክህኖአ
ቸውን ለብሰውና መለከታቸውን ይዘው፣ ሌዋው
ያኑ የአሳፍ ልጆች ደግሞ ጸናጽል ይዘው፣ በእስራ

2፥66 ኢሳ66፥20
2፥68 ዘፀ25፥2
2፥70 ቍ1፤ 1ዜና9፥2፤ ነህ11፥3-4
3፥1 ዘሌ23፥24፤ ነህ7፥73
3፥2 ዘፀ20፥24፤ ዘዳ12፥5-6፤1ዜና3፥17፤ ዕዝ2፥2፤ሐጌ1፥1፤ ዘካ6፥11
3፥3 ዘፀ29፥39፤ ዘኍ28፥1-8፤ዕዝ4፥4፤ ዳን9፥25
3፥4 ዘፀ23፥16፤ ዘኍ29፥12-38፤ ነህ8፥14-18፤ ዘካ14፥16-19
3፥5 ዘሌ23፥1-44፤ ዘኍ28፥14፤29፥39፤ ቈላ2፥16
3፥7 1ዜና14፥1፤ 22፥15፤ዕዝ1፥2-4፤ ኢሳ35፥2፤60፥13
3፥8 ዘኍ4፥3፤ 1ዜና6፥1፤ዘካ4፥9
3፥9 ዕዝ2፥40
3፥10 ዘኍ10፥2፤ 2ሳሙ6፥5፤1ዜና6፥31፤ 16፥6፤25፥1፤2ዜና5፥13፤ ዕዝ5፥16፤6፥3፤ነህ12፥35፤ ሐጌ2፥15፤ዘካ6፥12

[ሠ]69 500 ኪሎ ግራም ያህል ነው::
[ረ]69 2.9 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው::
[ሰ]9 ዕብራይስጡ፣ ይሁዳ ይላል፤ ምናልባት ከዮሐዳዩ ጋር ተመሳሳይ ነው::

አካዝ ነው፤ ብዙ አገልጋዮች ከጌቶቻቸው ጋር መመለሳቸው የሚያመለክተው የአይሁድ ሕዝቦች ለአገልጋዮቻቸው መልካም ሰዎች መሆናቸውን ነው:: *ዘማሪዎች*፤ እዚህ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሱት ወንዶችና ሴቶች ዘማሪዎች ከክህነት አገልግሎት ውጭ፣ በሰርግና በቀብር ሥነ ሥርዐት ላይ (2ዜና 35፥25) የሚዘፍኑና የሚያቀነቅኑ (2ዜና 35፥25) ሊሆኑ ይችላሉ:: እነዚህም በቍ 41 ላይ ከተጠቀሱት የቤተ መቅደሱ መዘምራን የተለዩ ናቸው፤ የቤተ መቅደሱ መዘምራን ወንዶች ብቻ ናቸው::

2፥66 *ፈረሶች*፤ ንጉሥ ቂሮስ ለአይሁድ መሳፍንትና መኳንንት የሰጣቸው ሳይሆኑ አይቀሩም:: *በቅሎዎች*፤ በእነዚህ እንስሳት የሚጠቀሙት አብዛኛውን ጊዜ ንጉሣውያን ቤተ ሰቦችና ባለጠጎች ብቻ ነበሩ (1ነገ 1፥33፤ ኢሳ 66፥20)::

2፥67 *አህዮች*፤ ዕቃን ለመጫን የሚጠቅሙ ሲሆን፣ ልጆችና ሴቶችም ይቀመጡባቸዋል:: በጎችና ፍየሎች እንዲሁም ሌሎች የቀንድ ከብቶች አልተጠቀሱም፤ ጕዞውን ስለሚያስተጓጕሉ ትተዋቸው ሊሆን ይችላል::

*2፥69*፤ የዚህ ክፍል ተጓዳኝ (ነህ 7፥70-72) በዕዝራ ላይ ከተገለጸው ይልቅ የተሟላ መግለጫ አለው:: በዕዝራ መጽሐፍ ስጦታዎቹን ያቀረቡት የቤተ ሰብ አለቆች ናቸው (ቍ 68)፤ በነህምያ መጽሐፍ ግን ስጦታዎቹን ያበረከቱት አገረ ገዢው፣ የቤተ ሰብ አለቆችና የተቀሩት ሰዎች በሙሉ ናቸው:: *ዳሪክ*፤ ከጥሬ ብር የተሠራ የግሪኮች ሳንቲም ነበር:: አንዳንዶች ግን እዚህ ላይ የተጠቀሰው የግሪኩ ሳይሆን፣ የፋርሱ የወርቅ ሳንቲም ነው ይላሉ:: *ምናን*፤ ለመጀመሪያ ጊዜ በሥራ ላይ የዋለው በመስጴጦምያ ነው:: 60 ሰቅል አንድ ምናን፣ 60 ምናን አንድ ታላንት ነበር:: አንድ ሰቅል የአንድ ወር አማካይ ደመወዝ ነበር፤ ስለዚህ አንድ ምናን የአምስት ዓመት ደመወዝ፣ አንድ ታላንት ደግሞ የሦስት መቶ ዓመት ደመወዝ ነው::

*2፥70*፤ በኋላ ግን ነህምያ (11፥1-2)በኢየሩሳሌም የሚኖረውን ሕዝብ ቍጥር ለመጨመር ሲል ሌሎች ሰዎችን በዕጣ ለመውሰድ ተገዶ ነበር::

3፥1 *ሰባተኛው ወር*፤ በወርሃ ጢሽሪ (ከመስከረም - ጥቅምት) ማለትም ምርኮኞቹ ይሁዳ ከደረሱ ከሦስት ወር በኋላ ነው (በ537 ዓ.ቅ.ክ):: ጢሽሪ በአይሁድ እጅግ የተቀደሱ በዓላት ከሚከበርባቸው ወራት አንዱ ነው (ዘሌ 23፥23-43 እና ማብ ይመ)::

3፥2 *ኢያሱ ... ዘሩባቤል*፤ ከወቅቱ ሁኔታ የተነሣ ከሕዝቡ መሪ ይልቅ ካህኑ ቅድሚያ አግኝቶአል (ከ3፥8፤4፥3፤5፥2፤ ከሐጌ 1፥1 ጋር ያነጻጽሩ)::

3፥4 *የዳስን በዓል*፤ ዘሌ 23፥33 – 43 እና ማብ ይመ::

3፥5 *የወር መባቻ*፤ የ1ሳሙ 20፥5 ማብ ይመ:: *በተቀደሱት ... በዓላት*፤ የዘሌ 23፥2 ማብ ይመ:: *በበጎ ፈቃድ ... የሚቀርበውን*፤ የ1፥4 ማብ ይመ:: እዚህ ላይ ከቤተ መቅደሱ መሠራት አስቀድሞ መሥዋዕት የቀረበ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል::

3፥7 *የዝግባ ግንድ*፤ ቤተ መቅደሱ መጀመሪያ ሲሠራ እንዳደረጉት ሁሉ፣ የፊንቂ ሰዎች አሁንም ዕንጨትና ሠራተኛ በመላክ ተባብረዋል (1ነገ 5፥6-12)::

3፥8 *በሁለተኛው ዓመት*፤ የአይሁድ ሕዝብ ወደ ምድራቸው የተመለሱት በበልግ ወራት በ537 ዓ.ቅ.ክ አካባቢ ስለ ነበር፣ የተባለው ሁለተኛ ዓመት፣ በ536 ዓ.ቅ.ክ በበልግ ወራት ውስጥ ማለት ነው:: *በሁለተኛው ወር*፤ ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ማሠራት ከጀመረበት ወር (1ነገ 6፥1) ጋር አንድ ነው (ሚያዝያ - ግንቦት):: *ሀያ ዓመት*፤ በቀድሞ ዘመን ሌዋውያን አገልግሎት የሚጀምሩበት ዝቅተኛው ዕድሜ 30 ዓመት (ዘኍ 4፥3) ወይም 25 ዓመት (ዘኍ 8፥24) ነበር፤ በኋላ ግን ወደ 20 ዓመት ዝቅ ብሎአል (1ዜና 23፥24፡27፤ 2ዜና 31፥17)፤ ይህ የሆነው ሌዋውያኑ በቍጥር አነስተኛ ስለነበሩ ሊሆን ይችላል::

3፥10 *መለከታቸውን*፤ ከብር ነጥሮ የተሠራ ነው (ዘኍ 10፥2 እና ማብ ይመ):: ዮሴፍ ወልደ ኩሪዮን ስለመለከት ሲናገር "ርዝመቱ ከአንድ ክንድ ትንሽ የሚያንስ፣ እንደ መቃ ውስጠ ክፍት፣ ከዋሽንት ትንሽ የሚወፍር ነው" ይላል:: መለከት ሁልጊዜ የሚነፋው በካህናት ነው፤ ይሁንና በኢዮአስ ሥርዐተ ንግሥ ጊዜ ብቻ መለከቶቹን ሌሎች ሰዎች ነፍተዋቸዋል (2ነገ 11፥14፤ 2ዜና 23፥13):: መለከት

ኤል ንጉሥ በዳዊት መመሪያ መሠረት እግዚአ
ብሔርን ለመወደስ ስፍራቸውን ያዙ። [11]በውዳ
ሴና በምስጋናም ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲሉ
ዘመሩ፤
"ቸር ነውና፤ ለእስራኤልም ምሕረቱ ለዘላ
ለም ነውና።" የእግዚአብሔር ቤት መሠረት ስለ
ተጣለ፣ ሕዝቡ ሁሉ በታላቅ ድምፅ እልል እያሉ፣
ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ። [12]የቀድሞ
ውን ቤተ መቅደስ ያዩ በዕድሜ የሸመገሉ ብዙ
ካህናት፣ ሌዋውያንና የቤተ ሰብ አለቆች የዚህ
ቤተ መቅደስ መሠረት ሲጣል ባዩ ጊዜ፣ ድምጻ
ቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ፤ ሌሎቹ ግን የደ
ስታ ጩኸት አሰሙ። [13]የሕዝቡ ጩኸት ድብ
ልቅልቅ ያለ ስለ ነበር፣ የደስታውን እልልታ
ከልቅሶው ጩኸት መለየት የሚችል ማንም
አልነበረም፤ ድምፁም ከሩቅ ይሰማ ነበር።

3፥11 ኢሱ6፥5፡10፤ 1ዜና16፥34፡41፤ 2ዜና7፥3፤መዝ30፥5፤ 107፥1፤118፥1፤138፥8፤ ሐጌ2፥18፤ዘካ4፥9፤8፥9
3፥12 ኤር31፥9፤ 50፥4፤ሐጌ2፥3፡9
3፥13 አዩ8፥21፤ 33፥26፤ መዝ27፥6፤ 42፥4፤ኢሳ16፥9፤ ኤር48፥33
4፥1 ነህ2፥20
4፥2 2ነገ17፥24፡41

### ቤተ መቅደሱ እንዳይሠራ የተነሣ ተቃውሞ

4 የይሁዳና የብንያም ጠላቶች ከምርኮ የተ
መለሱት ሰዎች የእስራኤልን አምላክ የእግዚ
አብሔርን ቤተ መቅደስ በመሥራት ላይ
መሆናቸውን ሲሰሙ፣ [2]ወደ ዘሩባቤልና ወደ ቤተ
ሰቡ አለቆች መጥተው፣ "እኛም እንደ እናንተ
አምላካችሁን የምንፈልግ ነን፤ የአሦር ንጉሥ አስ
ራዶን ወደዚህ ካመጣን ጊዜ ጀምሮ ለእርሱ ስንሠዋ
ለት ቈይተናል፤ ስለዚህ አብረን ከእናንተ ጋር
እንሥራ" አሏቸው።

አብዛኛውን ጊዜ የሚነፋው በደስታ ጊዜ ብቻ ነው፤ ይኸውም እዚህ ላይ እንደ ተገለጸው፣ የኢየሩሳሌም ቅጥር እንደ ገና ተሠርቶ ባለቀ ጊዜ፣ በምረቃው ሥርዐት ላይ (ነህ 12፥35፤ ከ2ዜና 5፥13፤ ከመዝ 98፥6 ጋር ያነጻጽሩ)እንዲነፋ ተደርጓል። ጸናጽል፤ ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ዐሥራ ሦስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል፤ እዚህ ላይ ከተጠቀሰውና ከነህ 12፥27 በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ የሚገኙት በዜና መዋዕል መጻሕፍት ውስጥ ነው።

*3፥11 ዘመሩ፤* እየተቀባበሉ ዘመሩ ማለት ሊሆን ይችላል፤ ምናልባት መዘምራኑ ሁለት ቦታ ተከፍለው አንዱ አንዱን ክፍል ሲዘምር፣ ሌላው ደግሞ ሌላውን ክፍል እየተቀባበሉ እንደሚዘምሩ ያመለክታል። *ቸር ነውና ...ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤* ለምሳሌ 1ዜና 16፥34፤ 2ዜና 5፥13፤ መዝ 100፥5 ይመ። *እልል እያሉ፤* ኢሱ 6፥5፡20፤ 1ሳሙ 4፥5፤ መዝ 95፥ 1 ይመ።


3፥13 *የደስታውን እልልታ ከልቅሶው ጩኸት፤* የእስራኤል ሕዝብ ስሜቱን በደስታና በእልልታ መግለጽ የተለመደ ነበር (10፥1፤ ነህ 1፥4፤ 8፥9)። ፍርድ እንዲመጣባቸው የፈቀደው አምላክ አሁን ደግሞ ወደ ምድራቸው መለሳቸው፤ ያቀዱትንም እንዲፈጽሙ ረዳቸው። በአንድ የባቢሎን የማእዘን ድንጋይ ላይ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎ ይገኛል "ሥራዬን እያለቀስሁ ጀመርሁ፣ የጨረስሁት ግን በደስታ ነው"፤ ከመዝ 126፥5-6 ጋር ያነጻጽሩ።

*4፥1-23* ይህ ክፍል የአይሁድን ሕዝብ ዕቅድና ጥረት ለማ ሰናከል ስለ ተደረገው ሙከራ ባጭሩ ይናገራል፤ ከቍ 1-5 ባለው ክፍል ጸሓፊው፣ በቂሮስ ዘመነ መንግሥት (ከ559-530 ዓ.ቅ.ክ) የተከናወኑትን ድርጊቶች ይገልጻል፤ በቍ 6 ላይ በጠረክሲስ ዘመነ መንግሥት (486-465 ዓ.ቅ.ክ) እንዲሁም ከቍ 7-23 ባለው ክፍል በቀዳማዊ አርጤክስስ ዘመነ መንግሥት (ከ465-424 ዓ.ቅ.ክ) የተፈጸመውን ድርጊት ያወሳል። ከዚያም ቍ 24 ላይ ወደ ቀዳማዊ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት (522-486 ዓ.ቅ.ክ) ይመለሳል፤ የቤተ መቅደሱ ሥራ የተፈጸመው በዚሁ ንጉሥ ዘመነ መንግሥት ነበር (5፥1-2፤ 6፥13-15፤ ትንቢተ ሐጌ፤ ዘካ 1፥1-17፤ 4፥9 ይመ)።

4፥1 *የይሁዳና የብንያም፤* የ1፥5፤ የ1ነገ 12፥21 ማብ ይመ። *ጠላቶች፤* "ከእናንተ ጋር እንሥራ" (ቍ 2) ያሏቸው ሰዎች የሰማርያ ሰዎች ናቸው።

*4፥2፤* የሰማርያ መንግሥት በ722-721 ዓ.ቅ.ክ ላይ ከወደቀ በኋላ፣ የአሦር ነገሥታት የመስጴጦምያንና የሶርያን ሰዎች ወደ አገራቸው ያፈልሱ ነበር። እነዚህ ሰዎች የሚያመልኩት የራሳቸው

## የዘሩባቤል ቤተመቅደስ




ሁለተኛው ቤተ መቅደስ የመጀመሪያው በባቢሎናውያን ከፈረሰ ግማሽ ምዕተ ዓመት በኋላ በ536 ዓ.ቅ.ክ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ መሠረት ላይ መሠራት ተጀመረ። የቀድሞውን ቤተ መቅደስ ያስታወሱ ሰዎች ከአሁኑ ጋር በማነጻጸር አለቀሱ (ዕዝ 3:12)። በፋርስ ንጉሥ በዳርዮስ (522 - 486) በ6ኛው ዓመት በ516 ተጠናቀቀ።

የሥነ ጥንት ማስረጃዎች እንደሚያረጋግጡት በፋርስ ዘመን በፍልስጥኤም ምድር ከቁሳዊ ነገሮች ባሕል አኳያ የበለጸገ አልነበረም። በኋላም በላይኛው የግብፅ ምድር የተገኙ የአራማይክ መዛግብት አይሁዶች የአምልኮ ስፍራ ለመገን ባት ከመንግሥት ፈቃድ ያገኙበትን ሂደትና በዚህ ጊዜ የነበሩትን የተለያዩ ጠላቶች ይገልጻሉ።

ስለ ቤተመቅደሱና ስለ ግንባታው ብዙ የሚታወቅ የለም። በጊዜው ከነበሩ ጥቂት ሕንጻዎች በሱሲስ ያለው የፋርስ ቤተ መንግሥትና በኢራቅ ኤልአሚር የነበረው ቶቢያድ በሕንጻ ቴክኒክ የሚጠቀሱ ናቸው።

በ586 ዓ.ቅ.ክ. እና በ70 ዓ.ም. እንደ ወደሙት ታላላቅ ሕንጻዎች በዘሩባቤል የተጀመረው ቤተ መቅደስ ያለ ምንም አስከፊ ውድመት ቀስ በቀስ በረጅም ጊዜ ውስጥ ታድሷል። በኋላም በሄሮድስ አስደናቂ ኀ ን ጻ ሙሉ በሙሉ ተተክቷል/ተስፋፍቷል።

3ዘሩባቤል፣ ኢያሱና ሌሎቹ የእስራኤል
ቤተ ሰቦች አለቆች ግን፣ 'ከሕምላካችን ቤተ መቅ
ደስ እንድትሠሩ ከእኛ ጋር የሚያገናኛችሁ
ምንም ነገር የለም። የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ ባዘዘን
መሠረት ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ የምንሠራው እኛ ብቻ ነን' ሲሉ
መለሱላቸው።
4ከዚያም የምድሪቱ ነዋሪዎች የይሁዳን
ሕዝብ ተስፋ ማስቈረጥና ሥራውንም እንዳይቀጥሉ
ማስፈራራት ጀመሩ[*]። 5ከፋርስ ንጉሥ ከቂሮስ
ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስከ ፋርስ ንጉሥ
እስከ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ድረስ ዕቅዶቻ
ቸውን የሚያሰናክሉ መካሪዎችን በገንዘብ ገዙ
ባቸው።

## በጠረክሲስና በአርጤክስስ ዘመን የተደረገ ሌላው ተቃውሞ

6በጠረክሲስ ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ
በይሁዳና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ላይ የጽሑፍ
ክስ መሠረቱባቸው።
7በፋርስ ንጉሥ በአርጤክስስ ዘመን ቢሽ
ላም፣ ሚትሪዳጡ፣ ጣብኤልና ተባባሪዎቹ ወደ
አርጤክስስ ደብዳቤ ጻፉ። ደብዳቤው የተጻ
ፈው በአረማይስጥ ፊደል፣ በአረማይስጥ ቋንቋ
ነበረ[†][‡]።
8አገረ ገዡ ሬሁምና ጸሓፊው ሲምሳይ
በኢየሩሳሌም ላይ ለንጉሡ ለአርጤክስስ እን
ዲህ የሚል ደብዳቤ ጻፉ፤
9ደብዳቤው የተጻፈው፣ ከአገረ ገዡ ሬሁም፣
ከጸሓፊው ሲምሳይ በትሪፖሊስ፣ በፋርስ፣ በኦ
ርክ፣ በባቢሎን፣ እንዲሁም በሱሳ ማለትም
በኤላማውያን ላይ ዳኞችና ገዦች ከሆኑት ከተ
ባባሪዎቻቸው፣ 10ደግሞም ታላቁና ኀያሉ አስና
ፈር[§] አፍልሶ በሰማርያ ከተማና ከኤፍራጥስ ወንዝ
ማዶ እንዲሰፍሩ ካደረጋቸው ሌሎች ሕዝቦች ነው።
11የላኩለት ደብዳቤ ቅጅ ይህ ነው፤

ለንጉሥ አርጤክስስ፣

በኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ከሚኖሩት አገል
ጋዮችህ የተላከ፤

12ከአንተ ዘንድ ወደ እኛ የመጡት አይሁ
ዳውያን ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ዐመፀኛና
ርኩስ ከተማ እንደ ገና በመሥራት ላይ ናቸው፤
ቅጥሮቿንም እንደ ገና በመሥራትና መሠረ
ቶቿንም በመጠገን ላይ መሆናቸው በንጉሡ
ዘንድ የታወቀ ይሁን።
13ከዚህም በላይ ይህች ከተማ ከተሠራች፣
ቅጥሮቿም እንደ ገና ከተገነቡ፣ ቀረጥና እጅ
መንሻ ወይም ግብር እንደማይከፍሉ፣ የቤተ
መንግሥቱም ገቢ እንደሚቀንስ በንጉሡ ዘንድ
የታወቀ ይሁን። 14አሁንም እኛ ስለ ቤተ መንግ

4፥3 ዕዝ1፥1-4
4፥4 ዕዝ3፥3
4፥6 አስ1፥1፤3፥13፤ 9፥5፤ዳ9፥1
4፥7 2ነገ18፥26፤ ዕዝ7፥1፤ነህ2፥1፤ ኢሳ36፥11፤ዳ1፥4፤2፥4
4፥9 ቍ23፤ ዘፍ10፥10፤ዕዝ5፥6፤ 6፥6፤13፤ነህ1፥1፤ አስ1፥2፤ዳ8፥2
4፥10 ቍ17፤ 2ነገ17፥24፤ነህ4፥2
4፥12 ዕዝ5፥3፡9
4፥13 ዕዝ7፥24፤ ነህ5፥4

[*]4 ወይም፣ *ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ሲነሡ አወኳቸው።*
[†]7 ወይም፣ *በአረማይስጥ ቋንቋ ተጽፎ በዚያው ቋንቋ የተተረጐመ።*
[‡]7 ዕዝ 4፥8-6፥18 ያለው ክፍል የተጻፈው በአረማይስጥ ቋንቋ ነው።
[§]10 በአረማይስጥ ቋንቋ "አሸርባኒጳል" ማለት ነው።

አምላክ ቢሆንም፣ እግዚአብሔርንም እንደ ምድሪቱ ባዕድ አምላክ በመቍጠር በተጨማሪ ያመልኩ ነበር (2ነገ 17፥24-41) *አስራዶን*፤ የ2ነገ 19፥37 ማብ ይመ።

4፥4 *የምድሪቱ ነዋሪዎች*፤ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ("አንቲኪውቲስ" 11.2.1) እነዚህ ሰዎች በተለይ ኩታውያን (2ነገ 17፥24፡30) መሆናቸውን ይገልጻል። *ማስፈራራት*፤ ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ግሥ በጦርነት ጊዜ የሚፈጠረውን ብርክ የሚገልጽ ነው (መሳ 20፥41፤ 2ሳሙ 4፥1፤ 2ዜና 32፥18)።

4፥5 *በገንዘብ ገዙባቸው*፤ በለዓም በገንዘብ የተቀጠረበትን (ዘዳ 23፥4-5፤ ነህ 13፥2) እንዲሁም አንድ ነቢይ ነህምያን እንዲያስፈራራ የተቀጠረበትን ሁኔታ (ከነህ 6፥12-13) ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

4፥6 *ጠረክሲስ*፤ መጽሐፈ አስቴርን ይመ። ንጉሥ ዳርዮስ በ486 ዓ.ቅ.ክ በሞተ ጊዜ፣ የግብፅ ሰዎች ዐምፀው ስለ ነበር፣ የዳርዮስ ልጅ ጠረክሲስ ይህን ዐመፅ ለመቈጣጠር ወደ ምዕራብ መጓዝ ነበረበት።

4፥7 *አርጤክስስ*፤ በዚህ ስም የተጠሩት ሦስት የፋርስ ነገሥታት ናቸው፤ እነርሱም ቀዳማዊ አርጤክስስ (ከ465-424 ዓ.ቅ.ክ)፣ ዳግማዊ አርጤክስስ (ከ404-358 ዓ.ቅ.ክ) እንዲሁም ሣልሳዊ አርጤክስስ (ከ358-338 ዓ.ቅ.ክ) ናቸው። እዚህ ቍጥር ላይ የተጠቀሰው ግን ቀዳማዊ አርጤክስስ ነው። *ሚትሪዳጡ*፤ 1፥8 እና ማብ ይመ። *ጣብኤል*፤ የአረማይስጥ ስም ነው (ኢሳ 7፥6 እና ማብ ይመ)፡ *ደብዳቤ ጻፉ*፤ የጥንት መካከለኛው ምሥራቅ ነገሥታት፣ በሚገባ የተዋቀር የወሬ አቀባዮችና የሰላዮች ቡድን ነበራቸው። ከግብፅ የተገኙ ሰነዶች የፈርዖን "ጆሮችና ዐይኖች" የሚል ቃል ይዘዋል። የአሦር ንጉሥ የነበረው ዳግማዊ ሳርጎን ዑራቱ በተባለ አካባቢ ለነበሩት እንደራሴዎቹ፣ "ያያችሁትንና የሰማችሁትን ሁሉ ጻፉልኝ" በማለት አዞአቸው ነበር። "የንጉሥ ዐይን" እንዲሁም "የንጉሥ ጆሮ" የሚባሉ ሁለት ባለሥልጣናት ለፋርስ ንጉሥ መረጃ ያቀብሉ ነበር።

*4፥8-6፥18*፤ ጸሐፊው ይህን ክፍል የወሰደው በአረማይስጥ ቋንቋ ከተጻፉ መዛግብት ላይ ነው። ከ7፥12-26 ያለውም ክፍል የተጻፈው በአረማይስጥ ቋንቋ ነው።

4፥8 *አገረ ገዡ*፤ የጠቅላይ ሚኒስትር ወይም የአንድ ሚኒስ ትር ያህል ሥልጣን የነበረው ሹም ሳይሆን አይቀርም። ምናልባት ሬሁም በቃል እየነገረው ደብዳቤውን በአረማይስጥ ቋንቋ የጻፈው ሲምሳይ ሊሆን ይችላል (በሌላ በኩል ደግሞ ሲምሳይ አንድ ትልቅ ባለሥልጣን እንጂ ጸሐፊት ላይሆን ይችላል)፡ ከዚያም ደብዳቤው ወደ ፋርስ ቋንቋ ተተርጕሞ በንጉሡ ፊት ይነበባል (ቍ 18)፤ ሄሮድቶስ እንደ ዘገበው፣ ለእያንዳንዱ ግዛ የቤተ መንግሥት ጸሐፊ ተመድቦለት በቀጥታ ለፋርስ ንጉሥ መረጃ ያስተላልፍ ነበር።

4፥9 *ከተባባሪዎቻቸው*፤ ቍ 17፡23፤5፥3፡6፤6፥6፤6፥13 ይመ። በፋርሶች ቢሮክራሲያዊ አገዛዝ ውስጥ ከሚታዩት አስደናቂ ነገሮች አንዱ በሥራ ባልደረቦች መካከል የሚታየው የኃላፊነት ክፍፍል ነው። *በኦርክ*፤ የዘፍ 10፥10 ማብ ይመ። *ባቢሎን*፤ በአሦራውያን ንጉሥ በአስናፈር ዘመነ መንግሥት (ከ669-627 ዓ.ቅ.ክ) አንድ ከፍተኛ የሕዝብ ዐመፅ ተነሥቶ ነበር (652-648 ዓ.ቅ.ክ)፤ በዚህ ዐመፅ ላይ የባቢሎን ገዥ የነበረው የንጉሡ ወንድም ሸማሽ-ሹም-ዑኪን ተሳትፎ ነበር። የንጉሡ ወንድም ብዙ ጊዜ ተከቦ በመቆየቱ ራሱን፣ እሳት ውስጥ ወርውሮ ገድሏል። እዚህ ላይ የተጠቀሱት የባቢሎን ሰዎች፣ አሦራውያን በስተ ምዕራብ ወደሚገኘው የአገሪቱ ክፍል ያጋዟቸው የዐማፅያኑ ዝርያዎች እንደ ነበሩ ምንም ጥርጥር የለውም። *ሱሳ*፤ ሱሳ የዔላም (በኢራን ደቡብ ምዕራብ) ዋነኛ ከተማ ናት። የሱሳ ነዋሪዎች በዐመፁ ተከፋይ ስለ ነበሩ፣ ንጉሥ አስናፈር በ640 ዓ.ቅ.ክ ላይ (ሬሁም ከጻፈው ደብዳቤ ሁለት ምዕተ ዓመት በፊት) ክፉኛ መትቶ አጥፍቶአቸዋል።

4፥10 *አስናፈር*፤ የመጨረሻው ታላቅ የአሦር ንጉሥ ሲሆን፤ በነነዌ ከተማ ባቋቋመው ቤተ መጻሕፍት ይታወቃል። ይህ ሰው ስሙ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ቦታ አልተጠቀሰም፤ ምናልባት ምናሴን ከግዞት ነጻ የለቀቀው ይህ ንጉሥ ሳይሆን አይቀርም (2ዜና 33፥11-13)። *ሰማርያ*፤ የይሁዳ ንጉሥ አሞን የተገደለው (ከ642-640 ዓ.ቅ.ክ፤ 2ነገ 21፥23፤ 2ዜና 33፥24 ይመ) በዔላምና በባቢሎን በተቀሰቀሰው ፀረ አሦር ዐመፅ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም። የአሦር ሰዎች እነዚህን ዐመፀኛ የሰማርያ ሰዎች ከዚያ በማንሣት፣ ከዐመፀኞቹ ከዔላምና ከባቢሎን ሰዎች ጋራ አግዘው አስፍረዋቸው ይሆናል። *ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ*፤ በቀጥታ "ከወንዙ ማዶ" ይኸውም ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ማለት ነው። ከፓለስቲና ሆኖ ሲታይ "ከወንዙ ማዶ" የተባለው አገር መስጴጦምያ ነው (ኢሱ 24፥2-3፡ 14፤15፤ 2ሳሙ 10፥16)። ከመስጴጦምያ ሆኖ ሲታይ ግን "ከወንዙ ማዶ" የሚባለው አገር የሶርያ፣ የፊንቄንና የፓለስቲናን ምድር ሁሉ የሚያካትት ክፍል ነው (1ነገ 4፥24)። የፋርስ ሰዎች ይህን ስፍራ አጡራ ብለው ይጠሩታል። *አፍልሶ*፤ በ2ነገ 17፥24 መሠረት ሰዎችን ወደ ሰማርያ ያመጣው ስሙ ያልተጠቀሰው የአሦር ንጉሥ አስናፈር ሊሆን ይችላል። በዚህ መልክ ተማርከው የሄዱት ሰዎች ዝርያዎች ከሁለት ምእተ ዓመት በኋላ እንኳን የትውልድ ስፍራቸውን አልረሱም።

4፥12 *ቅጥሮቿን እንደ ገና በመሥራትና መሠረቶቿንም በመጠገን*፤ ነቢዩ ኢሳይያስ አስቀድሞ እንደ ተናገረው ማለት ነው (ኢሳ 58፥13-14)።

*4፥13*፤ ወደ ፋርስ ግምጃ ቤት የሚገባው አብዛኛው የወርቅና የብር ሳንቲም የሚቀመጠው ቀልጦና ተጠፍጥፎ ነበር። በቀረጥ መልክ ከሚገባው ውስጥ ለአውራጃዎቹ ጥቅም የሚውለው እጅግ አነስተኛው ነበር።

4፥14 *ስለ ቤተ መንግሥቱ ስለሚገደንና*፤ በቀጥታ "የቤተ

ሥቱ ስለሚገደን፣ የንጉሡም ክብር ሲነካ ዝም
ብሎ ማየት ተገቢ ሆኖ ስላላገኘነው፣ ይህ ነገር
በንጉሡ ዘንድ የታወቀ እንዲሆን ይህን መልእ
ክት ልከናል፤ [15]ስለዚህ በአባቶችህ ቤተ መዛግ
ብት ምርመራ ይደረግ፤ በእነዚህ መዛግብት
ውስጥ ይህች ከተማ ዐመፀኛ ከተማ እንደ
ሆነች፣ ነገሥታትንና አውራጃዎችን የጐዳችና
ከጥንት ጀምሮ የዐመፅ ጐሬ ስለ መሆኗ
ማስረጃ ታገኛለህ፤ እንግዲህ ከተማዪቱ የተደ
መሰሰችው በዚህ ምክንያት ነው:: [16]ይህች
ከተማ ተመልሳ የምትሠራና ቅጥሮቿም እንደ
ገና የሚገነቡ ከሆነ፣ ከኤፍራጥስ ማዶ ምንም
ነገር እንደማይኖርህ ንጉሥ ታውቅ ዘንድ
እንወዳለን::

[17]ንጉሡም ይህን መልስ ላከ፤

ለአገረ ገዡ ሬሁም፣ ለጸሓፊው ሲም
ሳይ፣ በሰማርያና በኤፍራጥስ ማዶ ለሚኖሩ
ተባባሪዎቻቸው፤

ሰላም ለእናንተ ይሁን፤

[18]የላካችሁልኝ ደብዳቤ በፊቴ ተተርጒሞ
ተነቧል:: [19]እኔም ትእዛዝ ሰጥቼ ምርመራ
ተደርጎአል፤ በምርመራውም መሠረት ይህች
ከተማ ከጥንት ጀምሮ በነገሥታት ላይ ስታምፅ
የኖረች የዐመፅና የወንጀል መናኸሪያ እንደ
ሆነች ማስረጃ ተገኝቶአል:: [20]ኢየሩሳሌም ከኤፍ
ራጥስ ማዶ ያለውን አገር ሁሉ የገዙ፣ ቀረጥ፣
ግብርና እጅ መንሻም ይቀበሉ የነበሩ ኀያላን
ነገሥታት ነበሩት:: [21]አሁንም እኔ ትእዛዝ
እስከምሰጥበት ድረስ ይህች ከተማ እንደ ገና
እንዳትሠራ ሥራውን ያቆሙ ዘንድ ለእነዚህ
ሰዎች ትእዛዝ አስተላልፉ::

[22]ይህን ነገር ቸል እንዳትሉ ተጠንቀቁ፤
በነገሥታቱ ላይ የሚደርሰው ኪሣራ ለምን
እየበዛ ይሄዳል?

4፥15 ዕዝ5፥17፤
6፥1፤አስ3፥8
4፥17 ቍ10
4፥19 2ነገ18፥7
4፥20 ዘፍ15፥18-21፤
ዘፀ23፥31፤ኢሱ1፥4፤
1ነገ4፥21፤1ዜና18፥3፤
መዝ72፥8-11
4፥22 ዳን6፥2
4፥23 ቍ9
4፥24 ነህ2፥1 8፤
ዳን9፥25፤ሐጌ1፥1:15፤
ዘካ1፥1
5፥1 ዕዝ6፥14፤
ሐጌ1፥1:3:12:14፤
2፥1:9:10:20፤ዘካ1፥1፤
4፥9-10፤7፥1፤8፥9
5፥2 ቍ8 1ዜና3፥19፤
ዕዝ2፥2፤ሐጌ1፥14፤
2፥2:5:21፤ዘካ4፥6-10
5፥3 ዕዝ4፥12፤6፥6
5፥5 2ነገ25፥28፤
ዕዝ7፥6:9:28፤8፥18፡
22:31፤ነህ2፥8:18፤
መዝ33፥18፤ኢሳ66፥14

[23]የንጉሡ የአርጤክስስ ደብዳቤ ቅጅ በሬ
ሁም፣ በጸሓፊው በሲምሳይና ,በተባባሪዎ
ቻቸው ፊት እንደ ተነበበ፣ ወዲያውኑ በኢ
የሩሳሌም ወደሚገኙት አይሁድ ሄደው ሥራ
ውን እንዲያቆሙ አስገደዷቸው::

[24]ስለዚህም በኢየሩሳሌም የሚሠራው የእግ
ዚአብሔር ቤት ሥራ እስከ ፋርስ ንጉሥ እስከ
ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ሁለተኛ ዓመት
ድረስ ተቋረጠ::

## *ለዳርዮስ የተላከ የተንትናይ ደብዳቤ*

5 በዚያን ጊዜ ነቢዩ ሐጌና የአዶ ልጅ ነቢዩ
ዘካርያስ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ
አይሁድ ከእነርሱ በላይ በሆነው በእስራኤል
አምላክ ስም ትንቢት ተናገሩላቸው:: [2]ከዚያም የሰ
ላትያል ልጅ ዘሩባቤልና የኢዮሴዴቅ ልጅ
ኢያሱ በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ እንደ ገና ለመሥራት ተነሡ፤ የሚያግዟ
ቸውም የእግዚአብሔር ነቢያት አብረዋቸው ነበሩ::

[3]በዚህ ጊዜ በኤፍራጥስ ማዶ ገዥ የነበ
ረው ተንትናይ፣ ሰተርቡዝናይና ተባባሪዎቻቸው
ሄደው፣ “ይህን ቤተ መቅደስ እንደገና ለመሥራ
ትና ውቅሩንም ለመጠገን የፈቀደላችሁ ማን
ነው?” ሲሉ ጠየቋቸው:: [4]ደግሞም፣ “ይህን
ሕንጻ የሚገነቡት ሰዎች ስም ማን ይባላል?” በማለት
ጠየቋቸው+:: [5]የአምላካቸው ዐይን ግን በአይሁድ
መሪዎች ላይ ነበረ፤ ነገሩ ወደ ዳርዮስ ደርሶ
የጽሑፍ መልስ እስኪያገኙ ድረስ አልተከለከሉም::

[6]በኤፍራጥስ ማዶ ገዥ የነበረው ተንትናይ፣
ሰተርቡዝናይ፣ ተባባሪዎቻቸውና በኤፍራጥስ
ማዶ የነበሩ ሹማምንት ለንጉሥ ዳርዮስ የላኩት
ደብዳቤ ቅጅ ይህ ነው፤ [7]የላኩትም ደብዳቤ

+4 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ይመ፤ የአረማይስጡ ትርጒም
እንዲህ ይላል፣ *ይህን ሕንጻ የሚገነቡትን ሰዎች ስም ነገር ናቸው::*

*መንግሥቱን ጨው የምንበላ ነን*” ማለት ነው:: ጨውን ማምረትም
ሆነ ማከፋፈል የንጉሣውያን ሥራ እንዲሆን የግብፅ ጥሊሞሶች
ምናልባትም የፋርስ መንግሥት ወስነው ሊሆን ይችላል::

4፥15 *ቤተ መዛግብት*፤ 5፥17፤ 6፥1፤ አስ 2፥23፤ 6፥1-2 ይመ::
የነዚህ ዐይነት ሰነዶች በዋና ዋና ከተሞች ባሉ ግምጃ ቤቶች ይገኙ
ነበር:: በነገሥታቱ ቤተ መዛግብት ውስጥ ለምእተ ዓመታት የተቀ
መጡ ሰነዶች ይኖሩ:: ከክርስቶስ ልደት በፊት በሦስተኛው ምእተ ዓመት
ላይ ቤርሶስ የተባለ የባቢሎናውያን ካህን ከአሦራውያን ዘመን ጀምሮ
እስከ ግሪካውያን (ታላቁ እስክንድር በ330 ዓ.ቅ.ክ. ላይ ባቢሎንን
ድል አድርጎ እስኪያዘበት) ዘመን ድረስ ያለውን የባቢሎናውያንን ዜና
መዋዕሎች ተጠቅሞአል::

4፥18 *ተነቧል*፤ ንጉሡ በአረማይስጥ ቋንቋ የተጻፈውን ማን
በብ ስለማይችል ቋንቋውን የሚችሉ ሰዎች አንብበውለት ሊሆን
ይችላል:: *ተተርጒሞ*፤ ከአረማይስጥ ወደ ፋርስ ቋንቋ ነው (የቍ 7
አማራጭ ትርጒም ይመ፤ ነህ 8፥8 ይመ)::

4፥19 *ስታምፅ*፤ ውንጀላው እውነትነት አለው:: ኢየሩሳሌም
በ701 ዓ.ቅ.ክ በአሦራውያን ላይ ስታምፅ (2ነገ 18፥7) በባቢሎናውያን
ላይ ደግሞ በ600 እና በ589 ዓ.ቅ.ክ (2ነገ 24፥1:20) ዐምፃ ነበር::

*4፥21-23*፤ የየአውራጃዎቹ ባለሥልጣናት ጣልቃ ስለገቡ፣
ቀዳማዊ አርጤክስስ (ቍ 11 እና የቍ7 ማብ ይመ) አይሁድ የኢየሩ
ሳሌምን ቅጥር እንደ ገና እንዳይሠሩ ትእዛዝ አወጣ (የነህ 1፥3 ማብ
ይመ):: በቍ7-23 ላይ የተጠቀሰው ሁኔት የተፈጸመው ከ445 ዓ.ቅ.ክ
በፊት ሊሆን ይችላል:: ለነህምያ የተነገረው ናቡከደነፆር ያፈረሰው
ቅጥር ሳይሆን፣ በዚህ ጊዜ በጉልበት የፈረሰውና እንደ ገና የተሠ
ራው ቅጥር ነው (ነህ 1፥3)::

*4፥24*፤ ጸሓፊው አርእስቱን ለቆ ስለ አይሁድ ሕዝብ ጥረት ሲናገር
ብዙ ከቆየ በኋላ፣ ወደ ቀድሞው ርእስ ጉዳዩ ይኸውም ወደ ቤተ መቅደሱ
መገንባት ይመለሳል (ቍ 1-5):: *እስከ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት
ሁለተኛው ዓመት*፤ በፋርሶች አቈጣጠር መሠረት የቀዳማዊ ዳርዮስ
ዘመነ መንግሥት የጀመረው በኒሳን 1 (ሚያዝያ 3 ቀን) በ520 ዓ.ቅ.ክ
ላይ ሲሆን፣ የተፈጸመው ደግሞ የካቲት 21 ቀን 519 ዓ.ቅ.ክ. ላይ ነው:: ነቢዩ
ሐጌ የቤተ መቅደሱ ሥራ በስድስተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን (ነሐሴ
29 ቀን) እንደ ገና እንዲጀመር (ሐጌ 1፥1-5) ዘሩባቤልን የመከረው
በዚያኑ ዓመት ነበር፤ የቤተ መቅደሱም ሥራ የተጀመረው በወሩ በሃያ አራ
ተኛው ቀን ነበር፤ ይህም መስከረም 21 ቀን ነው (ሐጌ 1፥15):: ቢሶስቱን
በተባለው ጽሑፍ ላይ እንደ ተገለጸው፣ ዳርዮስ ሥልጣን በጨበጠ በመጀ
መሪያዎቹ ሁለት ዓመታት ውስጥ ብዙ ዐማፅያንን ተዋግቶ ድል በማድ
ረግ ዘሩፉን ማረጋገጥ ነበረበት:: ቤተ መቅደሱን እንደ ገና ለመገንባት
ፈቃድ ማግኘት የተቻለው፣ የፋርስ መንግሥት ከተረጋጋ በኋላ ነው::

5፥1 *ሐጌና ... ዘካርያስ*፤ ነቢዩ ሐጌ ከነሐሴ 29 ቀን 520 ዓ.ቅ.ክ
ጀምሮ (ሐጌ 1፥1) እስከ ታህሣሥ 18 ቀን ድረስ (ሐጌ 2፥1:10:20)
የቤተ መቅደሱን ሥራ በትጋት እንዲቀጥሉ ለማድረግ፣ ተከታታይ መልእ
ክቶችን ለሕዝቡ አስተላልፎ ነበር፤ ሐጌ የመጀመሪያ መልእክቱን
ካስተላለፈ ከሁለት ወር በኋላ፣ ዘካርያስም አብሮት ሕዝቡን ማበረታ
ታት ጀመረ (ዘካ 1፥1)::

5፥2 *ዘሩባቤልና*፤ የባቢሎናውያን ስም ሲሆን፣ ትርጒሙም
“የባቢሎን ልጆች” ማለት ነው፤ ይህ የሚያሳየው በምርኮ አገር መወለ
ዱን ነው:: አባቱ ሰላትያል ሲሆን፣ አያቱ ደግሞ የይሁዳ ሁለተኛው
የመጨረሻ ንጉሥ ኢኮንያን ነበር (1ዜና 3፥17):: ዘሩባቤል ከዳዊት
ቤት/ዘር ከወጡትና ፖለቲካዊ ሥልጣን ከነበራቸው ሰዎች መካከል
የመጨረሻ ሰው ነው:: ጌታ ኢየሱስ የመጣው ከዚሁ ሰው የዘር ሐረግ
ነው (ማቴ 1፥12-13፤ ሉቃ 3፥27):: *ኢያሱ*፤ የ2፥2 ማብ ይመ::

5፥3 *ተንትናይ*፤ የባቢሎናውያን ስም ሳይሆን አይቀርም::
*ሰተርቡዝናይ*፤ የፋርስ ባለሥልጣን ሊሆን ይችላል::

5፥5 *አልተከለከሉም*፤ የፋርስ አገረ ገዥ በአይሁድ ሕዝብ
ላይ የቀረበው ክስ ተጣርቶ መልስ እስኪያገኝ ድረስ የጀመሩትን
ሥራ እንዳያቋርጡ አድርጎ ነበር::

5፥6-7 *ለንጉሥ ዳርዮስ የላኩት ... የላኩትም*፤ ጽርስጳሲስ

እንዲህ የሚል ነበር፤
ለንጉሥ ዳርዮስ፣
የከበረ ሰላምታ እናቀርባለን::
8የታላቁ ስዋካ ቤተ መቅደስ ወደሚገኝበት
ወደ ይሁዳ አውራጃ ሄደን እንደ ነበር በንጉሡ
ዘንድ የታወቀ ይሁን:: ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን
በታላላቅ ድንጋዮች እየገነቡና ቅጥሩንም በወፍ
ራም ምሰሶዎች እየሠሩ ነው፤ ሥራው በትጋት
በመከናወንና በእነርሱም አመራር በመፋጠን
ላይ ይገኛል::
9እኛም መሪዎቹን፣ "ይህን ቤተ መቅደስ
እንደ ገና ለመሥራትና ይህንም ውቅር ለመጠገን
የፈቀደላችሁ ማን ነው?" ብለን ጠየቅናቸው::
10የመሪዎቻቸውን ስም በጽሑፍ እናሳውቅህ
ዘንድ ስማቸውን ደግሞ ጠየቅን::
11የሰጡን መልስ ይህ ነው፤
"እኛ የሰማይና የምድር ስዋካ አገልጋዮች
ነን፤ አሁንም እንደ ገና የምንሠራው ቤተ መቅ
ደስ፣ ከብዙ ዘመናት በፊት ታላቁ የእስራ
ኤል ንጉሥ ሠርቶ የጨረሰውን ነው:: 12ነገር
ግን አባቶቻችን የሰማይን ስዋካ አስቈጥተውት
ስለ ነበር፣ ለባቢሎኑ ንጉሥ ለከለዳዊው ናቡከደ
ነፆር አሳልፎ ሰጣቸው፤ እርሱም ይህን ቤተ
መቅደስ አፈራርሶ ሕዝቡን ወደ ባቢሎን አፈለሰ::
13"ይሁንና ቂሮስ፣ የባቢሎን ንጉሥ በሆነ በመጀ
መሪያው ዓመት ይህን የእግዚአብሔር ቤት እንደ
ገና እንዲሠሩ ንጉሥ ቂሮስ ትእዛዝ ሰጠ::
14ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ አው
ጥቶ ባቢሎን በሚገኘው ቤተ መቅደስ* ውስጥ
ያኖራቸውን የእግዚአብሔርን ቤት የወርቅና
የብር ዕቃዎች ከባቢሎን ቤተ መቅደስ አስመጣ::
"ከዚያም ንጉሥ ቂሮስ አገረ ገዥ አድርጎ
ለሾመውና ሰሳብሳር ተብሎ ለሚጠራው ሰው
ሰጠው፤ 15'ቀጥሎም፣ እነዚህን ዕቃዎች ይዘህ
ሂድና በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ
አኑራቸው፤ የእግዚአብሔር ቤት ቀድሞ በነበ
ረበት ቦታ እንደ ገና ይሠራ አለው:: 16ስለዚህ
ይህ ሰሳብሳር መጥቶ በኢየሩሳሌም የሚገኘውን
የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ መሠረት ጣለ፤
ከዚያን ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እነሆ
በመሠራት ላይ ነው፤ ሆኖም ገና አላለቀም::
17አሁንም ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው ቢሆን፣
ይህ የእግዚአብሔር ቤት በኢየሩሳሌም እንዲሠራ
ንጉሥ ቂሮስ በእርግጥ ትእዛዝ ሰጥቶ እንደ
ሆነ በባቢሎን ቤተ መንግሥት ግምጃ ቤት
የተቀመጡት መዛግብት እንዲመረመሩ ያድ
ርግ፤ ከዚያም ንጉሡ ስለዚህ ጉዳይ የወሰነ
ውን ይላክልን::"

5፥8 ቍ2
5፥9 ዕዝ4፥12
5፥11 1ነገ6፥1፤ 2ዜና3፥1-2
5፥12 ዘዳ21፥10፤ 28፥36፤2ነገ24፥1፤ 2ዜና36፥16፤ኤር1፥3
5፥13 ዕዝ1፥2-4
5፥14 1ዜና3፥18፤ ዕዝ1፥7
5፥16 ዕዝ3፥10
5፥17 ዕዝ4፥15
6፥1 ዕዝ4፥15
6፥3 ዕዝ3፥10፤ ሐጌ2፥3
6፥4 ቍ8፤ 1ነገ6፥36፤ዕዝ7፥20

## *የዳርዮስ ዐዋጅ*

6 ከዚያም ንጉሥ ዳርዮስ በባቢሎን ግምጃ
ቤት የተቀመጡት መዛግብት እንዲመረ
መሩ ትእዛዝ ሰጠ:: 2በሜዶን አውራጃ በሚገኘው
በአሕምታ ከተማ አንድ ጥቅልል ብራና ተገኘ፤
በውስጡም እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎበት ነበር፤

ማስታወሻ፤

3በንጉሥ ቂሮስ የመጀመሪያው ዓመት
በኢየሩሳሌም ስለሚገኘው የእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ንጉሡ የሰጠው ትእዛዝ ይህ ነው፤
ቤተ መቅደሱ መሥዋዕት የሚቀርብበት
ቦታ ሆኖ እንደ ገና ይሠራ፤ መሠረቱም ይጣል፤
ቁመቱ ሥልሳ ክንድ†፣ ወርዱም ሥልሳ ክንድ
ይሁን፤ 4በሦስት ዙር ታላላቅ ድንጋዮችና
በአንድ ዙር ዕንጨት ይሠራ፤ ውጪም ከቤተ

*14 ወይም፣ *ቤተ መንግሥት*
†3 27 *ሜትር ያህል ነው::*

ቡተባለች የነገሥታት ከተማ የተገኙ ጽሑፎች፣ እንደነዚህ ያሉ ጥያቄዎች በቀጥታ ወደ ንጉሡ ይላኩ እንደ ነበር ያረጋግጣሉ፤ ይህም ንጉሡ ጥቃቅን ጉዳዮችን ሳይቀር በቅርብ ይከታተል እንደ ነበር ያመለክታል::

5፥8 *በወፍራም ምሰሶዎች*፤ በቅጥሩ ውስጥ ለሚሠሩ ቤቶች እንደ ድጋፍ የሚውል ሊሆን ይችላል (1ነገ 6፥15-18)፤ ወይም በቅጥሩ ግድግዳ ውስጥ በጡብና በጡብ መካከል ወይም በድንጋይና በድንጋይ ንጣፎች መካከል የሚደረደሩ ሳንቃዎችን ሊሆን ይችላል (የ6፥4 ማብ ይመ)::

5፥11 *ታላቁ የእስራኤል ንጉሥ፤* በ1ነገ 6፥1 ላይ እንደ ተገለጸው፣ ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን መሥራት የጀመረው፣ በነገሠ በአራተኛው ዓመት በ(966 ዓ.ቅ.ክ) ላይ ነው፤ ሥራውም ሰባት ዓመት ፈጅቶአል (1ነገ 6፥38)::

5፥12 *ለከለዳዊው፤* ከለዳውያን በደቡብ መስጴጦምያ በሚገኘው ምድር የሚኖሩ ሕዝቦች ሲሆኑ፣ አዲሱን የባቢሎን መንግሥት የመሠረቱት እነርሱ ናቸው (ከ612-539 ዓ.ቅ.ክ):: ሥረ መሠረታቸው ግን በውል አይታወቅም:: ከክርስቶስ ልደት በፊት በሰባተኛው ምእተ ዓመት መገባደጃ ላይ፣ ከለዳውያን በንጉሥ ናቡከደነፆር አባት በናቦፖላሳር መሪነት የአሦራውያንን መንግሥት ገልብጠው ሥልጣን ይዘው ነበር::

5፥14 *ለሾመውና ... ለሰሳብሳር፤* የ1፥8 ማብ ይመ::

6፥1 *በባቢሎን ግምጃ ቤት የተቀመጡት መዛግብት፤* በጸርስጶሊስ አካባቢ በሚገኝ "ግምጃ ቤት" ውስጥ በርካታ ሰነዶች ተገኝተዋል::

6፥2 *በአሕምታ፤* በፋርስ ግዛተ አፄ ውስጥ ከሚገኙት አራት ዋና ዋና ከተሞች (ባቢሎንን፣ ጰርስጶሊስን፣ ሱሳን ጨምሮ) አንዱ ነበር:: ይህ ከተማ በነበረበት ቦታ ላይ፣ በአሁኑ ጊዜ ሐማዳን የተባለው የኢራን ከተማ ተሠ ርቶበታል፤ ሆኖም የዚህ ከተማ ፍርስራሽ እስካሁን ተቈፍሮ አልወጣም:: የዚህ ቦታ ስም በብሉይ የአዋልድ መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ቦታ ላይ የተጠቀሰ ቢሆንም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን የሚገኘው በዚህ ክፍል ብቻ ነው (ዮዲት 1፥1-4፤ ጦቢት 3፥7፤7፥1፤14፥12-14፤ 2መቃብያን 9፥3):: *በሜዶን*፤ በሰሜን ምዕራብ ኢራን የሜድ ሰዎች የሚኖሩበት አካባቢ ነበር፤ የሜድ ሰዎች የሕንድና የአውሮፖ ዝርያ ያላቸው ነገዶች ሲሆኑ፣ ከፋርስ ሰዎችም ጋር ይዛመዳሉ:: ንጉሥ ቂሮስ በ550 ዓ.ቅ.ክ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ በፋርሶች አገዛዝ ሥር ወድቀዋል:: እስከ አዲስ ኪዳን ዘመን ድረስ ይህ ስፍራ የሚጠራው በዚህ ስም ነበር (ሐሥ 2፥9)::

6፥3-5፤ በዚህ ክፍል በአረማይስጥ ቋንቋ የተጻፈውን የንጉሥ ዳርዮስን ዐዋጅ በ1፥2-4 ላይ በዕብራይስጥ ቋንቋ ከተጻፈው ተመሳሳይ ዐዋጅ ጋር ያነጻጽሩ:: በአረማይስጥ ቋንቋ የተጻፈው *የእግዚአብሔርን* (የያህዌን) ስም ባይዝም፣ ዐዋጁ የተጻፈው ሥርዐት ባለው አስተዳደራዊ ቋንቋ ነው:: በላይኛው ግብፅ ኤሌፋንታይ በሚባል ስፍራ የአይሁድ ቤተ መቅደስ እንደ ገና እንዲሠራ ፈቃድ የሚሰጥ "ማስታወሻ" ከክርስቶስ ልደት በፊት በአምስተኛው ምእተ ዓመት ላይ በአረማይስጥ ቋንቋ በተጻፉ ፓፒረሶች ላይ ተገኝቷል፡፡

6፥3 *ቁመቱ ሥልሳ ክንድ ወርዱም ሥልሳ ክንድ፤* ይህ ስፍር (አማራጭ ትርጕሙን ይመ) የሚገልጸው ተመልሶ የሚሠራው ቤተ መቅደስ ጠቅላላ ስፋቱ ምን ያህል እንደ ሆነ ሳይሆን፣ የፋርስ ሰዎች ለግንባታው ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑበትን የሕንጻውን ውጫዊ መጠን ሊሆን ይችላል፤ ሁለተኛው ቤተ መቅደስ እንደ መጀመሪያው ቤተ መቅደስ ትልቅና ግርማ ሞገስ ያለው አልነበረም (3፥12፤ ሐጌ 2፥3)፡፡

6፥4 *ታላላቅ ድንጋዮችና ... ዕንጨት፤* 5፥8 ይመ:: በ1ነገ 6፥36፤ 7፥12 ላይ ተመሳሳይ የሕንጻ አሠራር ተጠቅሶአል:: የዚህ ዐይነቱ የሕንጻ አሠራር ያስፈለገበት ምክንያት በመሬት መንቀጥቀጥ የሚደርሰውን አደጋ ለመቋቋም ታስቦ ሳይሆን አይቀርም:: *ለዚህ የሚሆነው ወጭ ከቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤት ይከፈል፤* በቱርክ ደቡባዊ ምዕራብ ዛንጦስ በተባለ ስፍራ በፋርስ ዘመን የነበረውን የአምልኮ ሥርዐት የሚገልጽ አንድ ጽሑፍ በ1973 ዓም ላይ በሥነ ቅርስ ሊቃውንት ተገኝቶአል፤ ይህ ጽሑፍ ንጉሥ ቂሮስ እዚህ ላይ ካወጀው ዐዋጅ ጋር ተመሳሳይነት አለው:: በዕዝራ መጽሐፍ ውስጥ እንደ ተገለጸው ሁሉ በዚህም ጽሑፍ ውስጥ ስለ መሥዋዕት ዐይነቶች፣ ስለ ካህናት ስሞችና ሥርዐተ አምልኮውን ለመጠበቅ ስለሚያ

መንግሥቱ ግምጃ ቤት ይከፈል። [5]እንዲሁም
ናቡከደነፆር በኢየሩሳሌም ከሚገኘው ቤተ መቅ
ደስ አውጥቶ ወደ ባቢሎን የወሰዳቸው የእግዚ
አብሔር ቤት የወርቅና የብር ዕቃዎች፣ በኢየሩ
ሳሌም ወዳለው ቦታቸው ወደ ቤተ መቅደሱ
እንዲመለሱ ይሁን፤ በእግዚአብሔርም ቤት ይቀ
መጡ።
[6]አሁንም በኤፍራጥስ ማዶ አገረ ገዥ
የሆንኸው ተንትናይ፣ ሰተርቡዝናይና እናንተም
በዚያ አውራጃ የምትገኙ ተባባሪዎቻቸው ሁሉ
ወደዚያ አትድረሱ። [7]በዚህም በእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ሥራ ጣልቃ አትግቡ፤ ይህን የእግዚአ
ብሔርን ቤት የአይሁድ አገረ ገዥና የአይሁድ
መሪዎች በቀድሞው ቦታ ላይ መልሰው ይሥሩት።
[8]በተጨማሪም የአይሁድ መሪዎች ይህን
የእግዚአብሔር ቤት እንደ ገና ሲሠሩ፣ እናንተ ምን
እንደ ምታደርጉላቸው ይህን ትእዛዝ ሰጥቻለሁ፤
ሥራውም እንዳይቋረጥ የእነዚህ ሰዎች ወጪ
በሙሉ ከመንግሥት ግምጃ ቤትና ከኤፍራጥስ
ማዶ ከሚገኘው ግብ ላይ ይከፈል። [9]ለሰማይ አም
ላክ የሚቃጠል መሥዋዕት ይሆን ዘንድ የሚያስ
ፈልጋቸውን ነገር፣ ማለት ወይፈኖችን፣ አውራ
በጎችንና ተባዕት ጠቦቶችን ስጧቸው፤ እንዲሁም
ስንዴው፣ ጨው፣ የወይን ጠጅና ዘይቱ በኢየሩ
ሳሌም ያሉት ካህናት በሚጠይቋችሁ መሠረት
ያለማቋረጥ በየቀኑ ይሰጧቸው። [10]ይህ የሚሆነው
የሰማይ አምላክን ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት እንዲ
ያቀርቡ፣ ለንጉሡና ለወንድ ልጆቹም ደኅን
ነት እንዲጸልዩ ነው።
[11]ደግሞም ይህን ትእዛዝ የሚለውጥ ማንም
ሰው ቢኖር፣ ከቤቱ ምሰሶ ተነቅሎ በምሰሶው
ላይ እንዲሰቀል፣ ስለ ወንጀሉም ቤቱ የቈሻሻ
መጣያ እንዲሆን አዝዣለሁ። [12]ይህን ትእዛዝ
ለማፍረስ ወይም በኢየሩሳሌም የሚገኘውን ቤተ
መቅደስ ለማጥፋት እጁን የሚያነሣ ማንኛው
ንም ንጉሥ ወይም ሕዝብ፣ ስሙን በዚያ እንዲ
ኖር ያደረገ አምላክ ያጥፋው።
እኔ ዳርዮስ በትጋት እንዲፈጸም ይህን
ትእዛዝ ሰጥቻለሁ።

### የቤተ መቅደሱ ሥራ ፍጻሜና ምረቃ

[13]ከዚያም ንጉሡ ዳርዮስ ባዘዘው መሠረት
በኤፍራጥስ ማዶ አገረ ገዥ የነበረው ተንት
ናይ፣ ሰተርቡዝናይና ተባባሪዎቻቸው ሥራው
በትጋት እንዲፈጸም አደረጉ። [14]ስለዚህ የአይ
ሁድ መሪዎች በነቢዩ በሐጌና በአዶ ልጅ
በዘካርያስ ትንቢት እየተጽናኑ ሥራውን ቀጠሉ፤
የቤተ መቅደሱንም ሥራ በእስራኤል አምላክ
ትእዛዝ እንዲሁም የፋርስ ነገሥታት ቂሮስ፣
ዳርዮስና አርጤክስስ በሰጡት ትእዛዝ መሠ
ረት ሠርተው ጨረሱ። [15]ይህም ቤተ መቅደስ
ንጉሥ ዳርዮስ በነገሠ በስድስተኛው ዓመት
አዳር ተብሎ በሚጠራው ወር በሦስተኛው
ቀን ተጠናቀቀ።
[16]ከዚያም የእስራኤል ሕዝብ፣ ካህናቱ፣
ሌዋውያኑና የቀሩትም ምርኮኞች የእግዚአብሔርን

6፥5 ኒሕ29፥2፤ ዕዝ1፥7
6፥6 ዕዝ5፥3
6፥8 ቍ4፤ሳሙ9፥20
6፥9 ዘሌ1፥3፡10
6፥10 ዕዝ7፥23፤ 1ጢሞ2፥1-2
6፥11 ዘዳ21፥22-23፤ አስ2፥23፤5፥14፤ 9፥14፤ዕዝ7፥26፤ ዳን2፥5፤3፥29፤
6፥12 ቍ14፤ ዘፀ20፥24፤ዘዳ12፥5፤ 2ዜና6፥2
6፥13 ዕዝ4፥9
6፥14 ቍ12፤ ዕዝ1፥2-4፤5፥1፤ 7፥1፤ ነህ2፥1
6፥15 ዘካ1፥1፤4፥9
6፥16 1ነገ8፥63

ስፈልገው ኅላፊነት በዝርዝር ተጽፎ ይገኛል። የዚያን ሥርዐተ አምልኮ ዝርዝር ሁኔታ የፋርስ ንጉሥ በቅርብ የሚያውቅ ይመስላል።

6፥8 *ከመንግሥት ግምጃ ቤት ... ይከፈል*፤ የፋርስ ነገሥታት በግዛታቸው ውስጥ የሚገኙ ቤተ መቅደሶች እንደ ገና ሲሠሩ መርዳት ቋሚ መመሪያቸው ነበር፤ ለምሳሌ በኤሌፋንታይ የነበረውን የአይሁድ ቤተ መቅደስ እንደ ገና እንዲሠራ በይሁዳና በሰማርያ የነበሩት የፋርስ ገዢ ዎች፣ ይህንኑ በተመለከተ ማስታወሻ ጽፈዋል። እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ከሚገኙ ምንጮች መረዳት እንደሚቻለው ቂሮስ በዑሩክና በዑር የነበሩትን ቤተ መቅደሶች አድሶ ነበር። ከቂሮስ በኋላ የነገሠው ቃምቢሲ የተባለ ሰው በግብፅ አገር ሲደስ በተባለ ስፍራ ለነበረው ቤተ መቅደስ ዕርዳታ ሰጥቶአል። ካርጋ በተባለ ለምለም ቦታ ላይ የነበረው የአሞን ቤተ ጣዖት እንደገና የተሠራው በዳርዮስ ትእዛዝ ነበር።

6፥9 የፋርስ ነገሥታት ከእነርሱ ሥርዐተ አምልኮ ውጭ ለነበሩ የተለያዩ የአምልኮ ሥርዐቶች ትኩረት ይሰጡ እንደ ነበር ቃምቢሲና ቀዳማዊ ዳርዮስ በግብፅ የነበሩትን ቤተ መቅደሶችና ካህናት ለመቈጣጠር ባወጡት ድንጋጌ ላይ ጐልቶ ይታያል። በኤሌፋንታይ ለነበሩት አይሁድ የቂጣን በዓል አከባበር በተመለከተ በዳግማዊ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት (ከ423-404 ዓ.ቅ.ክ) ደብዳቤ ተጽፎላቸው ነበር።

6፥10 *ለንጉሡና ለወንድ ልጆቹ ደኅንነት እንዲጸልዩ*፤ በቂሮስ ስም ከሸክላ በተሠራ ዕቃ ላይ፣ "በተቀደሱ ከተሞቻቸው መልሼ ያስቀመጥኋቸው አማልክት ሁሉ ዕድሜዬ እንዲረዝም በየዕለቱ ቤልን ናናባውን ይለምኑልኝ" በማለት የጠየቀው ተጽፎ ይገኛል። በኤሌፋንታይ የነበሩት አይሁድ፣ ለይሁዳው የፋርስ ገዥ ይጸልዩለት ነበር። በየዕለቱ በምኩራብ በሚደረገው አገልግሎት ለንጉሣውያን ቤተሰቦች መጸለይ የተለመደ ነበር (ከ1ጢሞ 2፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)።

6፥11 *ይህን ትእዛዝ የሚለውጥ ማንም ሰው ቢኖር*፤ በዐዋጆች ወይም በውሎች መጨረሻ ላይ የዐዋጁን ወይም የውሉን ቃል በሚያቃልል ሰው ላይ ይህ ይውረድበት የሚሉ ረጅም የርግማን ቃሎች ይገኛሉ። *እንዲሰቀል*፤ ሄሮደተስ የተባለ ሰው (3.159) እንደዘገበው፣ ቀዳማዊ ዳርዮስ የባቢሎንን ከተማ በያዘ ጊዜ 3000 የባቢሎን ሰዎችን ሰቅሎ ገድሏል። (አስ 2፥23 ማብ ይመ)።

6፥12 *ማንኛውንም ንጉሥ ወይም ሕዝብ ... አምላክ ያጥፋው*፤ "ቢሾቱን" በመባል በሚታወቀው በቀዳማዊ ዳርዮስ የድንጋይ ጽሑፍ ላይ እንዲህ የሚል ቃል በስተ መጨረሻው ተጽፎ ይገኛል፣ "ይህን ጽሑፍ ወይም እነዚህን ምስሎች አይተህ በተቻለህ መጠን ሳትን ከባከባቸው ብትቀርና ቢጠፉ፣ አሑራማዝዳ ይቀሥፍህ፤ ዘርም አይወ ጣልህ፤ የምትሠራውም እንዳይከናወንልህ ... አሑራማዝዳ ፈጽሞ ያጥፋብህ።" *ስሙ በዚያ እንዲኖር ያደረገ* የዘዳ 12፥5 ማብ ይመ።

*6፥13-14*፤ የቤተ መቅደሱ ሥራ የተጓተተው ተቃውሞ ስለ ተነሣባቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች ለየግል ኑሮአቸው ቅድሚያ ስለሰጡ ጭምር ነበር (ሐጌ 1፥2-9)። የገዛ ፍላጐታቸውንና ዕቅዳቸውን ስላስቀደሙ እግዚአብሔር በራብና በጥማት እንዲቀጡ ፈረደባቸው (ሐጌ 1፥5-6፡10-11)። በኋላ ግን በሐጌ እና በዘካርያስ ስብከት አነሣሽነት እንዲሁም በዘሩባቤልና በኢያሱ መሪነት አዲስና የተለየ የሥራ ጥረት ማሳየት ጀመሩ (ሐጌ 1፥12-15)።

6፥14 *አርጤክስስ*፤ ቤተ መቅደሱ እንደገና እንዲሠራ ያደረገው አስተዋጽኦ ስላልነበረ፣ እዚህ ላይ ስሙ መወሳቱ ትክክል አይደለም። ነገር ግን ስሙ እዚህ ላይ የተጠቀሰበት ምክንያት፣ በዕዝራ መሪነት ለተደረገው የቤተ መቅደስ ሥራ በኋላም ስላደረገው እገዛ ሊሆን ይችላል (7፥21-24)።

6፥15 *ቤተ መቅደሱ ... ተጠናቀቀ*፤ ይህ የሆነው ቤተ መቅደሱ ከፈረሰ ከ70 ዓመታት በኋላ መጋቢት 12 ቀን 516 ዓ.ቅ.ክ ላይ ነበር። የቤተ መቅደስም ሥራ እንደገና የተጀመረው መስከረም 21 ቀን 520 ዓ.ቅ.ክ ላይ ነበር (ሐጌ 1፥15)፤ ይህም ሥራ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ያህል ቀጥሎ አል። የጥንቱን የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ግዙፍነትና ውበት የሚያስታውሱ አረጋውያን፣ ዘሩባቤል ያሠራውን መለስተኛ ቤተ መቅደስ ባዩ ጊዜ፣ በጣም እንዳዘኑ በሐጌ 2፥3 ላይ ተጽፎ ይገኛል (ከዕዝ 3፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ቤተ መቅደስ መጠኑ ሰሎሞን ካሠራው ቤተ መቅደስ ቢያንስም እንኳ፣ ከሰሎሞን ቤተ መቅደስ ይበልጥ ብዙ ዘመን አገልግሎአል። የቤተ መቅደሱም ጠቅላላ ንድፍ ሰሎሞን ካነጸው ቤተ መቅደስ ጋር ይመሳሰላል፤ ሆኖም የኪዳኑ ታቦት ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን በተማረከችበት ጊዜ ስለጠፋ፣ ቅድስተ ቅዱሳኑ ባዶ ነበር። ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን በስርየት ቀን ሊቀ ካህናቱ ቀድሞ ታቦቱ በነበረበት ቦታ ላይ ጥናውን ያስቀምጥ እንደ ነበር ይናገራል። በቅድስቱ ውስጥ ገጸ ኅብስቱ የሚቀመጥበት ጠረጴዛ፣ የዕጣን መሠዊያና አንድ መቅረዝ (የብሉይ አዋልድ ከሆነው ከ1መቃብያን 1፥21-22፤ 4፥49-51 ጋር ያነጻጽሩ) ይገኛል፤ ሰሎሞን ባሠራው ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚቀመጡት ዐሥር መቅረዞች ነበሩ (1ነገ 7፥49)።

6፥16 *ምርኮኞች ... ምረቃ በዓል*፤ ከዚህ ጋር (1ነገ 8) የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ የምረቃ በዓል ያነጻጽሩ። ለቤተ መቅደሱ

ቤት ምረቃ በዓል በደስታ አከበሩ:: 17ስለዚህ
ለእግዚአብሔር ቤት ምረቃም አንድ መቶ ወይፈ
ኖችን፣ ሁለት መቶ አውራ በጎችንና አራት መቶ
ተባዕት ጠቦቶችን ሰጡ፤ ለመላው እስራኤል
የኃጢአት መሥዋዕትም ዐሥራ ሁለት ተባዕት
ፍየሎችን በእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ ልክ
አቀረቡ። 18በሙሴ መጽሐፍ በተጻፈው መሠረት
በኢየሩሳሌም ላለው ለእግዚአብሔር አገልግሎት
ካህናቱን በየማዕረጋቸው፣ ሌዋውያኑንም በየክ
ፍላቸው መደቧቸው::

*የፋሲካ በዓል*

19ምርኮኞቹ በመጀመሪያው ወር በዐሥራ
አራተኛው ቀን የፋሲካን በዓል አከበሩ::
20ካህናቱና ሌዋውያኑ ራሳቸውን አነጹ፤ ሁሉም
በሥርዐቱ መሠረት ንጹሕ ነበሩ:: ሌዋውያ
ኑም የፋሲካውን በግ ለምርኮኞቹ ሁሉ፣ ለካህናት
ወንድሞቻቸውና ለራሳቸው ዐረዱ:: 21ስለዚህ
ከምርኮ የተመለሱት እስራኤላውያን የእስራ
ኤልን አምላክ *እግዚአብሔርን* በአምልኮ ይፈል
ጉት ዘንድ ራሳቸውን ከአረማውያን ጎረቤቶቻ
ቸው ርኵሰት ከለዩት ሁሉ ጋር በሉ:: 22እግዚ
*አብሔር* ደስ እንዲሰኙ ስላደረጋቸው የቂጣን
በዓል ሰባት ቀን በደስታ አከበሩ፤ ምክንያቱም
*እግዚአብሔር* የአሦርን ንጉሥ ልብ ለውጦ
በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ቤት ሥራ
እንዲያግዛቸው አድርጎ ነበር::

*ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ*

7 ከእነዚህም ነገሮች በኋላ በፋርስ ንጉሥ
በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት፣ ዕዝራ
የሠራያ ልጅ፣ የዓዛርያስ ልጅ፣ የኬልቅያስ
ልጅ፣ 2የሰሎም ልጅ፣ የሳዶቅ ልጅ፣ የአኪጦብ
ልጅ፣ 3የአማርያ ልጅ፣ የዓዛርያስ ልጅ፣ የመ
ራዮት ልጅ፣ 4የዘራእያ ልጅ፣ የኦዚ ልጅ፣
የቡቂ ልጅ፣ 5የአቢሱ ልጅ፣ የፊንሐስ ልጅ፣
የአልዓዛር ልጅ፣ የታላቁ ካህን የአሮን ልጅ፣
6ይህ ዕዝራ ከባቢሎን መጣ:: እርሱም የእስራ
ኤል አምላክ *እግዚአብሔር* ለሙሴ የሰጠውን
ሕግ በሚገባ የሚያውቅ የሕግ መምህር ነበር::
የአምላኩ *የእግዚአብሔር* እጅ በእርሱ ላይ ስለ
ነበረች፣ የጠየቀውን ሁሉ ንጉሡ ፈቀደለት::
7እንደዚሁም አንዳንድ እስራኤላውያን፣ ከካህናት፣
ከሌዋውያን፣ ከመዘምራን፣ ከበር ጠባቂዎችና

6፥17 2ሳሙ6፥13፤ 2ዜና29፥21፤30፥24
6፥18 ዘኍ3፥6-9፤ 8፥9-11፤18፥1-32፤ 1ዜና24፥1፤ 2ዜና35፥4፤ሉቃ1፥5
6፥19 ዘፀ12፥11፤ ዘኍ28፥16
6፥20 2ዜና30፥17
6፥21 ዘዳ18፥9፤ 1ዜና22፥19፤ዕዝ9፥1፤ ነህ9፥2፤መዝ14፥2፤ ሕዝ36፥25
6፥22 ዘፀ12፥17፤ ዕዝ1፥1
7፥1 2ነገ22፥4፤ 25፥18፤ ዕዝ4፥7፤6፥14
7፥2 1ነገ1፥8፤ 2፥35፤1ዜና6፥8፤ ነህ11፥11፤ሕዝ40፥46፤ 43፥19፤44፥15
7፥5 1ዜና6፥4
7፥6 2ነገ25፥28፤ ዕዝ5፥5፤ነህ12፥36፤ ኢሳ41፥20

---

*ሥራ መጠናቀቅ* ዋናዎቹ ተጠሪዎች ከምርኮ የተመለሱት የሕዝብ አለቆች ነበሩ:: የምረቃ በዓሉ በአረማይስጥ ቋንቋ "ሐኑካ" ይባላል:: አይሁድ ቤተ መቅደሳቸውን ከሰሉሲድ ሥርወ መንግሥት መልሰው የያዙበትና እንደ ገና መርቀው የከፈቱበትን ዕለት (በ165 ዓ.ቅ.ክ) የሚያከብሩት በታኅሣሥ ወር ሲሆን፣ እነርሱም ይህን ክብረ በዓል "ሐኑካ" ይሉታል::

6፥17 *አንድ መቶ ... ሁለት መቶ ... አራት መቶ*፤ በሰሎሞን (1ነገ 8፥5:63)፣ በሕዝቅያስና (2ዜና 30፥24) በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ከቀረበው (2ዜና 35፥7) መሥዋዕት ጋር ሲነጻጸር በጣም አነስተኛ ነው፤ በዚያን ዘመን በመቶዎች ሳይሆን በሺዎች የሚቈጠር መሥዋዕት ይቀርብ ነበር::

6፥18 *በሙሴ መጽሐፍ በተጻፈው መሠረት*፤ ምናልባት በዘፀ 29፤ በዘሌ 8፤ በዘኍ 3፤ 8፥5-26፤ 18 ላይ የተጻፈውን ሊሆን ይችላል:: *በየማዕረጋቸው*፤ ካህናት በሀያ አራት ማዕረግ ተከፍለው ያገለግሉ ነበር (1ዜና 24፥1-19)፤ እያንዳንዱ ማዕረግ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ለአንድ ሳምንት በየተራ ያገለግል ነበር (ከሉቃ 1፥5:8 ጋር ያነጻጽሩ):: በ1962 ዓ.ም ቂሣርያ ተብሎ በሚጠራ ስፍራ የሀያ አራቱንም ማዕረጐች ዝርዝር የያዘ በመኰራብ ጸሐፍት የተዘጋጀ አንድ ጽሁፍ ተገኝቷል::

6፥19 *በመጀመሪያው ወር ... በዐሥራ አራተኛው ቀን ... የፋሲካ በዓል*፤ ምናልባት ጊዜው ሚያዝያ 21 ቀን 516 ዓ.ቅ.ክ ሊሆን ይችላል::

6፥20 *ራሳቸውን አነጹ ... በሥርዐቱ መሠረት ንጹሐ*፤ የዘሌ 4፥12 ማብ ይመ:: ካህናትና ሌዋውያን የአምልኮ ሥርዐቱን መፈጸም የሚችሉት ሥርዐቱን መፈጸም የሚችሉ ሲገኙ ብቻ ነው::

6፥21 *ራሳቸውን ... ከለዩት ሁሉ ጋር*፤ ከምርኮ የተመለሱት አይሁድ በአሦር አገዛዝ ምክንያት ወደ ምድራቸው ገብቶ ከነበረው የጣዖት አምልኮ ራሳቸውን ጠብቀው የቆዩትን ወገኖቻቸውን ተቀብለው፣ አብረው ለመኖር ፈቃደኞች ነበሩ::

6፥22 *የአሦር ንጉሥ*፤ ለንጉሥ ዳርዮስ የተሰጠ ያልተለመደ መጠሪያ ነው፤ ዳርዮስ የፋርስ ንጉሥ ነበርና:: ነነዌ በ612 ዓ.ቅ.ክ ከወደቀች በኋላ እንኳ "አሦር" የሚለው ቃል ቀድሞ የአሦር መንግሥት ገዝቶአቸው ለነበሩት አገሮች ሁሉ መጠሪያ ሆኖ ቈይቶአል (ሶርያ የሚለው ስም እንኳ የዚሁ ስም ምሕጻረ ቃል ነው):: የፋርስ ነገሥታት ብዙ የማዕረግ ስሞች ነበሯቸው፤ ከእነዚህም አንዱ፣ "የባቢሎን ንጉሥ" የሚል ነው (ከ5፥13፤ ከነህ 13፥6 ጋር ያነጻጽሩ)::

*7፥1-5*፤ እዚህ ላይ የተዘረዘረው የዕዝራ የዘር ሐረግ እስከ ሙሴ ወንድም እስከ አሮን ድረስ ሲቈጠር ዐሥራ ስድስት ነው::

7፥1 *ከእነዚህም ነገሮች በኋላ*፤ ቀደም ባለው ምዕራፍ የተነገረው ታሪክ በ516 ዓ.ቅ.ክ ላይ በተጠናቀቀው የቤተ መቅደሱ ሥራ ይደመደማል:: *አርጤክስስ*፤ በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሰው የዚህ ንጉሥ ማንነት አከራካሪ ነው:: ይህ ሰው ቀዳማዊ አርጤክስስ ከሆነ (ነገሩም ይመስላል)፣ ዕዝራ ወደ ይሁዳ ምድር የመጣው በ458 ዓ.ቅ.ክ ላይ ነው ማለት ነው፤ በምዕራፍ 6 እና በምዕራፍ 7 መካከል የሥልሳ ዓመት ልዩነት አለ:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ተፈጽሞአል ተብሎ የተመዘገበ ድርጊት ቢኖር፣ በጠረክሲስ ዘመነ መንግሥት (ከ486-465 ዓ.ቅ.ክ) ኢየሩሳሌም ዳግም እንዳትሠራ ተነሥቶ የነበረው ተቃውሞ ብቻ ነው (4፥6):: *ዕዝራ*፤ ምናልባት ዓዛርያስ ለሚለው ስም አጭር መጠሪያ ሊሆን ይችላል፤ በዕዝራ የዘር ሐረግ ውስጥ ዓዛርያስ የሚለው ስም ሁለት ጊዜ ተጠቅሶአል:: ዕዝራ የሚለውን ስም ግሪኩ "ኢስድራስ" ይለዋል፤ በአዋልድ መጻሕፍት ውስጥ የምናገኘው "ኢስድራስ" የሚለው መጠሪያ ነው:: *የሠራያ*፤ የስሙ ትርጉም፣ እግዚአብሔር ልዑል ነው" ማለት ነው:: ዕዝራ ወደ ይሁዳ ምድር ከመምጣቱ ከ128 ዓመት በፊት በ586 ዓ.ቅ.ክ ላይ በናቡከደነፆር በተገደለው (2ነገ 25፥18-21) በንጉሥ ሴዴቅያስ ዘመን ሊቀ ካህን ነበረ:: ስለዚህ ይህ ሰው የዕዝራ ወላጅ አባት ሳይሆን፣ ከቅድመ አያቶቹ አንዱ ነበር ማለቱ ይቀላል፤ በብሉይ ኪዳን "ልጅ" ማለት ሲልባል "ዘር" ማለት ነው (1ዜና 6፥14-15 ይመ):: *ዓዛርያስ*፤ የስሙ ትርጉም፣ "እግዚአብሔር ይረዳል" ማለት ነው:: *የኬልቅያስ*፤ ትርጉሙ "ዕድል ፈንታዬ እግዚአብሔር ነው" ማለት ነው:: በኢዮስያስ ዘመን ሊቀ ካህን ነበር (2ነገ 22፥4)::

7፥2 *የሳዶቅ*፤ የስሙ ትርጉም፣ "ጻድቅ" ማለት ነው:: በንጉሥ ዳዊት ዘመን ካህን ነበረ (2ሳሙ 8፥17):: አብያታር ዐመፀኛውን አዶንያስን ይደግፍ ስለ ነበር፣ ንጉሥ ሰሎሞን እርሱን ሽሮ በምትኩ ሳዶቅን ሊቀ ካህን አድርጎ ሾመው (1ነገ 1፥7-8፤ 2፥35:: ሕዝቅኤል የሳዶቅ ወገኖች ከጣዖት አምልኮ የራቁ እንደ ነበሩ ተናግሯል (ሕዝ 44፥15):: የሊቀ ካህናቱንም ሥልጣን እስከ 171 ዓ.ቅ.ክ ድረስ ይዘው ነበር:: የሰዱቃውያን ስም ከሳዶቅ የመጣ ሳይሆን አይቀርም፤ የኩምራንም ኅብረተሰብ፣ ከሳዶቅ ወገኖች የሆነው ክህነት እንዲመለስ ይፈልጉ ነበር:: አኪጦብ፤ የዚህ ስም ትርጉም፣ "ወንድሜ መልካም ነው" ማለት ነው:: የሳዶቅ አያት ነው (ነህ 11፥11)::

7፥5 *የአልዓዛር*፤ የስሙ ትርጉም፣ "እግዚአብሔር ይረዳል" ማለት ነው:: በግሪክ ቋንቋ "ላዛሮስ" ተብሎአል፤ በአማርኛ ግን አልዓዛር የሚለው ስም እንደተጠበቀ ነው (ዮሐ11፥1)::

7፥6 *የሕግ መምህር*፤ በቁሙ "ጸሓፊ" ማለት ነው (ለምሳሌ በነህ 8፥1:4:9:13፤12፥26:36 ይመ):: በጥንት ዘመን "ጸሐፍት" የነገሥታት "ጸሐፌ ትእዛዝ" በመሆን ያገለግሉ ነበር፤ ለምሳሌ ሳፋን የኢዮስያስ ጸሐፌ ትእዛዝ ነበረ (2ነገ 22፥3):: አንዳንድ ጸሐፍት ደግሞ በቃል የሚነገረውን በጽሑፍ ያስፍሩ ነበር፤ ለምሳሌ ባሮክ የኤርምያስ ጸሓፊ ነበር (ኤር 36፥32):: ከምርኮ ዘመን ወዲህ ግን እነዚህ "ጸሐፍት" ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያጠኑና የሚያስተምሩ ምሁራን ነበሩ (በአዲስ ኪዳን፣ "የሕግ መምህራን" ከተባሉት ጋር ያነጻጽሩ፤ የማቴ 2፥4፤ የሉቃ 5፥17 ማብ ይመ):: በአዲስ ኪዳን፣ "ረቢ" ተብለው ይጠሩ ነበር (ከማቴ 23፥7 ጋር ያነጻጽሩ):: *በሚገባ የሚያውቅ*፤ ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ሐረግ በመዝ 45፥1 ላይ "ባለሞያ"፣ በምሳ 22፥29 ደግሞ "የሠለጠነ" ተብሉ ተተርጉሞአል:: *የእግዚአብሔር እጅ*፤ ይህን ታላቅ የእግዚአብሔርን ሞገስ ለመግለጽ የገባውን አባባል ከቍ 9:28፤ 8፥18:22:31፤ ከነህ

ከቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ጋር በመሆን በን
ጉሡ በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት በሰባ
ተኛው ዓመት ወደ ኢየሩሳሌም መጡ።
8ዕዝራ በንጉሡ ሰባተኛ ዓመት በአምስተ
ኛው ወር ኢየሩሳሌም ደረሰ። 9መልካሚቱ
የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ስለ ነበረች፣
ከባቢሎን በመጀመሪያው ወር በመጀመሪያው
ቀን ተነሥቶ በአምስተኛው ወር በመጀመሪ
ያው ቀን ኢየሩሳሌም ደረሰ። 10ዕዝራ የእግዚአብ
ሔርን ሕግ በማጥናትና በማድረግ፣ ለእስራኤልም
ሥርዐቱንና ሕጉን በማስተማር ራሱን ፈጽሞ
ሰጥቶ ነበር።

## *ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ደብዳቤ*

11እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠውን
ሕግና ትእዛዝ ዐዋቂ ለነበረው ለካህኑና ለመ
ምህሩ ዕዝራ ንጉሥ አርጤክስስ የሰጠው የደ
ብዳቤ ቅጅ ይህ ነው፤
12ከንጉሠ ነገሥት አርጤክስስ[']፤ ለሰማይ
አምላክ ሕግ መምህር ለሆነው ለካህኑ ለዕዝራ፤

ሰላም ለአንተ ይሁን፤

13ካህናቱንና ሌዋውያኑን ጨምሮ በመንግ
ሥቴ ውስጥ የሚኖርና ከአንተ ጋር ወደ
ኢየሩሳሌም ለመሄድ የሚፈልግ ማንኛውም
እስራኤላዊ መሄድ እንዲችል ይህን ትእዛዝ
ሰጥቻለሁ። 14በእጅህ በሚገኘው በአምላክህ ሕግ
መሠረት፣ ስለ ይሁዳና ስለ ኢየሩሳሌም እንድ
ትመረምር በንጉሡና በሰባት አማካሪዎቹ ተልከ
ሃል። 15ከዚህም በላይ፣ ንጉሡና አማካሪዎቹ
መኖሪያው በኢየሩሳሌም ለሆነው ለእስራ
ኤል አምላክ በፈቃዳቸው የሰጡትን ብርና

7፥7 ዕዝ8፥1
7፥9 ቍ6
7፥10 ዘዳ33፥10
7፥12 ሕዝ26፥7፤
ዳን2፥37
7፥14 አስ1፥14
7፥15 ዘዳ12፥5፤
1ዜና29፥6፤2ዜና6፥2
7፥16 ዘፀ3፥22፤
ዘካ6፥10
7፥17 ዘኍ15፥5-12፤
ዘዳ12፥5-11፤ 2ነገ3፥4
7፥19 ዕዝ5፥14፤
ኤር27፥22
7፥20 ዕዝ6፥4
7፥23 ዕዝ6፥10

ወርቅ ይዘህ ሂድ፤ 16እንዲሁም ከመላው ባቢሎን
አውራጃ የምታገኘውን ብርና ወርቅ በሙሉ፣
ሕዝቡና ካህናቱም በኢየሩሳሌም ላለው ለአምላካ
ቸው ቤተ መቅደስ በፈቃዳቸው የሚሰጡትን
መባ ሁሉ ይዘህ ሂድ። 17በዚህም ገንዘብ ወይፈ
ኖችን፣ አውራ በጎችንና ጠቦቶችን፣ ከእህል
ቍርባኖቻቸውና ከመጠጥ ቍርባኖቻቸው
ጋር መግዛት እንዳለብህ አትርሳ፤ እነዚህንም
በኢየሩሳሌም በሚገኘው በአምላካችሁ ቤተ
መቅደስ መሠዊያ ላይ አቅርብ።
18ከዚህ የሚቀረውንም ብርና ወርቅ አንተና
ወንድሞችህ አይሁድ እንደ አምላካችሁ ፈቃድ
ደስ ለሚላችሁ ነገር ሁሉ አውሉት። 19ለአምላክህ
ቤተ መቅደስ በዐደራ የተሰጠህንም ዕቃ ሁሉ
በኢየሩሳሌም አምላክ ፊት አቅርብ። 20ከዚህም
በላይ ለአምላክህ ቤተ መቅደስ ለማስጠት የምትፈ
ልገውን ነገር ሁሉ ከንጉሡ ግምጃ ቤት መውሰድ
ትችላለህ።
21በኤፍራጥስ ማዶ የምትገኙ በጅሮን
ዶች ሁሉ፣ የሰማይ አምላክ ሕግ መምህር
የሆነው ካህኑ ዕዝራ የሚጠይቃችሁን ሁሉ
በትጋት እንድትሰጡት እኔ ንጉሥ አርጤ
ክስስ እነሆ አዝዣለሁ፤ 22እስከ አንድ መቶ
መክሊት[ፕ] ብር፣ እስከ አንድ መቶ ቆሮስ ስንዴ፣
እስከ አንድ መቶ ባዶስ[ኣ] መስፈሪያ ወይን ጠጅ፣
እስከ አንድ መቶ ባዶስ የወይራ ዘይትና የሚፈ
ለገውን ያህል ጨው ስጡት። 23የሰማይ አምላክ

[']12 በዕዝ 7፥12-26 ላይ የሚገኘው ክፍል የተጻፈው በአረማይስጥ
ቋንቋ ነው።
[ፕ]22 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
[ኣ]22 22 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።
[ከ]22 2.2 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።

2፥8፡18 ጋር ያነጻጽሩ።
7፥7-9 *በሰባተኛው ዓመት … በመጀመሪያው ወር በመጀ
መሪያው ቀን … በአምስተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን፤* ዕዝራ
ጉዞውን የጀመረው በኒሳን ወር በመጀመሪያው ቀን (ሚያዝያ 8
ቀን 458 ዓ.ቅ.ክ) ሲሆን፣ ኢየሩሳሌም የደረሰው ደግሞ በዓብ ወር
በመጀመሪያው ቀን (ነሐሴ 4 ቀን በ458 ዓ.ቅ.ክ) ነው። ጕዞው አራት
ወር ፈጅቶአል፤ (ቍ 9 ከ8፥31 ጋር ያነጻጽሩ)። የበልጉ ወራት
ለእንዲህ ዐይነቱ ጕዞ የተመቸ ነበር። ብዙ ሰራዊቶች ወረራ ለማካ
ሄድ የሚዘምቱት በዚህ ጊዜ ነው። በባቢሎንና በኢየሩሳሌም
መካከል ያለው ርቀት 800 ኪ.ሜ. ያህል ቢሆንም፣ ተጓዦች
የኤፍራጥስን ወንዝ ተከትለው ወደ ሰሜን ምዕራብ ከዚያም ወደ
ደቡብ በመሄድ በአጠቃላይ 1440 ኪ.ሜ. ያህል ርቀት መጓዝ ነበረ
ባቸው። ጕዞው አዝጋሚ የሆነበትም ምክንያት በመካከላቸው አዛውን
ትና ሕጻናት ስለ ነበሩ ነው። በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን
ካርታ ቍ 7 ይመ።
7፥10 *በማጥናትና በማድረግ … በማስተማር፤* ነህ 8 ይመ።
7፥11 *የደብዳቤ፤* ብዙዎች ይህን የቀዳማዊ አርጤክስስን
ደብዳቤ፣ ዳንኤል በትንቢቱ የተናገረው የሰባው ሱባዔ መጀመሪያ
ነው ብለው ያምናሉ (ዳን 9፥24-27)፤ ሌሎች ደግሞ ይኸው ንጉሥ
ነህምያን መላኩ፣ የዚሁ ትንቢት ፍጻሜ መጀመሪያ ነው ይላሉ (ነህ
1፥1፡11፤2፥1-8)። የፀሐይን አቈጣጠር ይዞ ከመጀመሪያው ዘመን
(ከ458 ዓ.ቅ.ክ) ጋር በማገናዘብ ወይም የጨረቃን አቈጣጠር ይዞ
ከኋለኛው ዘመን (ከ445 ዓ.ቅ.ክ) ጋር በማገናዘብ ክርስቶስ የማ
ስተማር ሥራውን የጀመረበትን ጊዜ ማወቅ ይቻላል።
*7፥12፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። *ከንጉሠ ነገሥት፤* አሦራ
ውያን በዚህ ስም የተጠሩት በሥራቸው ብዙ ነገሥታት ስለ ነበሩ
ነው፤ በኋላም የባቢሎንና (ሕዝ 26፥7፤ ዳን 2፥37) የፋርስ
ነገሥታት በዚሁ ስም ተጠርተዋል። ከ1ጢሞ 6፥15፤ ከራእ 17፥14፤
19፥16 ጋር ያነጻጽሩ።
7፥13 *እስራኤላዊ፤* ከ"ይሁዳ" ይልቅ "እስራኤል" የሚለው
መጠሪያ እዚህ ላይ ለምን እንዳስፈለገ ማስተዋል ይገባል፤ ከምርኮ
ከተመለሱት ወገኖች ሁሉ አንዲት እስራኤልን መመሥረት ዋናው
የዕዝራ ዓላማ ነበር። ይህ ዐዋጅ የአይሁድን የሥነ ጽሑፍ አሻራ
ያሳያል፤ ይህም ሊሆን የቻለው ንጉሡ በዕብራውያን ባለሥልጣናት
በመጠቀሙ ሳይሆን አይቀርም፤ ምናልባትም ራሱ ዕዝራ ጽሑፉን በማ
ቀነባበር ረገድ ረድቶት ሊሆን ይችላል።
7፥14 *በአምላክህ ሕግ፤* ምናልባት አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት
በሙሉ አሁን ባለው መልኩ ለማለት ይሆናል (ቍ 6 ይመ)።
*ሰባት አማካሪዎቹ፤* ይህን በአስ 1፥14 ላይ፣ "ቀዳሚዎች ሆነው
የሚቀመጡ" ከተባሉት ሰባት ባለሟሎች ጋር ያነጻጽሩ። የጥንት
የግሪክ ታሪክ ሊቃውንት የነበሩት ሄሮዶተስና ዜኖፎን ይህ በፋርስ
ነገሥታትም ዘንድ የተለመደ አሠራር እንደ ነበር ጽፈዋል።
7፥15 *በፈቃዳቸው የሰጡትን፤* የፋርስ ግምጃ ቤት በቂ
የገቢ ምንጭ ነበረው፤ ቸርነት ማድረግ የፋርስ ነገሥታት መመሪያ
ነበረ። *ብርና ወርቅ፤* ከሐጌ 2፥8 ጋር ያነጻጽሩ።
7፥16 *ሕዝቡ … የሚሰጡትን … መባ፤* ከእስራኤል ምድር ውጪ
ይኖሩ የነበሩ አይሁድ ስጦታዎችን ወደ ኢየሩሳሌም የመላክ ልማድ
ነበራቸው፤ ይህም አይሁድና ሮማውያን በተዋጉ ጊዜ፣ ወደ ኢየሩ
ሳሌም በመላክ ፈንታ ወደ ጁፒተር ቤተ ጣዖት እንዲልኩ ሮማ
ውያን አይሁድን እስካስገደዱበት ጊዜ ድረስ ቀጥሏል። ይህንንም እስ
ራኤላዊው ታሪክ ጸሓፊ የሴፍ ወልደ ከርዮን "አንቲኪዊቲስ" ቡተባለው
መጽሐፉ አስፍሮታል። በግብፅ አገር ኤሌፋንታይ በተባለው አይሁድ
በሚኖሩበት ስፍራ የተገኙ ደብዳቤዎች ከዚሁ ጋር እጅግ ተቀራራቢ
የሆኑ ትእዛዞችና መመሪያዎች ይዘዋል፤ ከእነዚህም ውስጥ ዳግማዊ
ዳርዮስ እንዲህ ሲል ትእዛዝ ያስተላለፈበት የፓፒረስ ጽሑፍ ይኛል፤ ያሑ
በተባለው አምላክ መሠዊያ ላይ፣ "የእህል፣ የዕጣንና የሚ
ቃጠል መሥዋዕት ቁርባን (በያሑ) ስም ይቅረብ"።
7፥20 *ከቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤት መውሰድ ትችላለህ፤*
ከጳርስጳሊስ ግምጃ ቤት በተገኙ ሰነዶችም ላይ የእርዳታ ስጦታዎች
ከቤተ መንግሥቱ ወጪ ይደረጉ እንደ ነበር ተመዝግቦ ይገኛል።
7፥22 *መቶ መክሊት፤* እጅግ ብዙ ሀብት ነው። *መቶ ቆሮስ፤*
ይህ ከሌላው ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ነው። ስንዴው ለእህል ቍርባን
የሚያገለግል ነው። *የሚፈልገውን ያህል ጨው፤* የ4፥14 ማብ
ይመ።
7፥23 *በልጆቹ፤* በዚህ ጊዜ ንጉሡ ስንት ወንዶች ልጆች

የሚያዘው ሁሉ፣ ለሰማይ አምላክ ቤተ መቅ
ደስ በፍጹም ትጋት ይደረግ፤ በንጉሡና በል
ጆቹ መንግሥት ላይ ለምን ቍጣ ይውረድ?
24ደግሞም በካህናቱ፣ በሌዋውያኑ፣ በመዘም
ራኑ፣ በበር ጠባቂዎቹ፣ በቤተ መቅደሱ አገ
ልጋዮች ወይም በሌሎቹ በዚህ በእግዚአብሔር
ቤት ሠራተኞች ላይ ቀረጥ፣ ግብርና እጅ መንሻ
ለመጣል ሥልጣን እንደ ሌላችሁ ይህን ዕወቁ::
25አንተም ዕዝራ ከአምላክህ እንደ ተሰጠህ
ጥበብ መጠን፣ ከኤፍራጥስ ማዶ ለሚገኙት
ሕዝቦች ሁሉ የአምላክህን ሕግ የሚያውቁ
ዳኞችንና ፈራጆችን ሹምላቸው፤ ሕጉን የማያ
ውቅ ሰው ቢኖር፣ አንተ ራስህ አስተምረው::
26ለአምላክህ ሕግና ለንጉሡ ሕግ የማይታዘዝ
ማንኛውም ሰው፣ የሞት ወይም የስደት
ወይም የንብረት መወረስ ወይም የእስራት
ቅጣት ይፈጸምበት::

27በኢየሩሳሌም የሚገኘው *የእግዚአብሔር*
ቤት በዚህ ሁኔታ እንዲከበር ይህን በንጉሡ
ልብ ያኖረ የአባቶቻችን አምላክ *እግዚአብሔር*
ቡሩክ ይሁን፤ 28እንዲሁም በንጉሡ፣ በአማ
ካሪዎቹና በኀያላን ሹሞቹ ፊት ሁሉ ሞገ
ስን የሰጠኝ አምላክ የተመሰገነ ይሁን፤ የአም
ላኬ *የእግዚአብሔር* እጅ በእኔ ላይ ስለ ነበረች፣
አብረውኝ እንዲሄዱ ከእስራኤል መካከል የታ
ወቁ ሰዎችን ለመሰብሰብ ብርታት አገኘሁ::

### *ከዕዝራ ጋር የተመለሱት የየቤተ ሰቡ አለቆች ስም ዝርዝር*

8 በንጉሡ በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት
ከባቢሎን አብረውኝ የወጡት የየቤተ
ሰቡ አለቆችና አብረዋቸው የተመዘገቡት
እነዚህ ናቸው፤
2ከፊንሐስ ዘሮች ጌርሶን፤
ከኢታምር ዘሮች ዳንኤል፤
ከዳዊት ዘሮች ሐጡስ፤ 3እርሱም ከሴኬንያ
ዘሮች ነው፤
ከፋሮስ ዘሮች ዘካርያስና ከእርሱም ጋር
150 ወንዶች ተመዝግበው ነበር፤
4ከፋሐት ሞዓብ ዘሮች የዘራእያ ልጅ
ኤሊሆዔናይና ከእርሱም ጋር 200 ወንዶች፤
5ከዛቱ[5] ዘሮች የየሕዚኤል ልጅ ሴኬንያና
ከእርሱም ጋር 300 ወንዶች፤
6ከዓዲን ዘሮች የዮናታን ልጅ ዔቤድና
ከእርሱም ጋር 50 ወንዶች፤
7ከኤላም ዘሮች የጎቶልያ ልጅ የሻያና
ከእርሱም ጋር 70 ወንዶች፤
8ከሰፋጥያስ ዘሮች፣ የሚካኤል ልጅ ዝባ
ድያ፣ ከ80 ወንዶች ጋር፤
9ከኢዮአብ ዘሮች የይሒኤል ልጅ አብ
ድዩና ከእርሱ ጋር 218 ወንዶች፤
10ከባኒ[10] ዘሮች የዮሲፍያ ልጅ ሰሎ
ሚትና ከእርሱም ጋር 160 ወንዶች፤
11ከቤባይ ዘሮች የቤባይ ልጅ ዘካርያስ
ከእርሱም ጋር 28 ወንዶች፤
12ከዓዝጋድ ዘሮች የሃቃጣን ልጅ ዮሐ
ናንና ከእርሱም ጋር 110 ወንዶች፤

7፥24 ዕዝ4፥13፤ 8፥36
7፥25 ዘፀ18፥21:26፤ ዘሌ10፥11
7፥26 ዕዝ6፥11
7፥27 ዕዝ1፥1፤ 1ዜና29፥12
7፥28 2ነገ25፥28፤ ዕዝ5፥5
8፥1 ዕዝ7፥7
8፥3 1ዜና3፥22፤ ዕዝ2፥3
8፥4 ዕዝ2፥6
8፥6 ዕዝ2፥15፤ ነህ7፥20፤10፥16

[5] 5 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች (እንዲሁም መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል 8፥22) ይህን ስም ይጨምራሉ፤ ዕብራይስጡ ግን ዛቱ የሚለውን አይጨምርም::
[10] 10 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች (እንዲሁም መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል 8፥36) ይህን ስም ይጨምራሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ባኒ የሚለውን አይጨምርም::

እንደ ነበሩት አይታወቅም፤ ይሁን እንጂ የፋርስን ታሪክ በስፋት የጻፈው ግሪካዊ ሐኪም ኪቲስያስ፣ ንጉሡ ዐሥራ ስምንት ልጆች እንደ ነበሩት ገልጾአል:: *መንግሥት ላይ...ቍጣ* ግብፅ በ460 ዓ.ቅ.ክ በፋርስ መንግሥት ላይ ዐምፃ ነበር፤ በ459 ዓ.ቅ.ክ በአቴና ሰዎች በመታገዝ፣ የፋርስን ሰዎች ከምድሯ ለማስወጣት ችላለች:: በ458 ዓ.ቅ.ክ ላይ ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም በተጓዘበት ዘመን የፋርስ መንግሥት ይህን ዐመፅ በመቋቋም ላይ ነበር::

7፥24 *በካህናቱ ... በቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ... ቀረጥ ... ለመጣል ሥልጣን እንደ ሌላችሁ፤* አብዛኛውን ጊዜ ካህናትና ሌሎች የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ከማናቸውም የግዴታ ሥራና የግብር ክፍያ ነጻ ነበሩ:: ቀዳማዊ ዳርዮስ በምዕራብ ቱርክ አገረ ገዥ ለነበረ አንድ ሰው በላከው ደብዳቤ ላይ የአጶሎን ቤተ ጣዖት የሚያገለግሉ ካህናት ከአንዳንድ ግዴታዎች ነጻ መሆናቸውን የሚገልጽ ጽሑፍ ሰፍሮአል:: ሣልሳዊ አንጥያኮስም የአይሁድን ሕዝብ ከግዴታ ነጻ የሚያደርግ ተመሳሳይ መብት ሰጥቶአቸው ነበር፣ "ካህናት፣ የቤተ መቅደሱ ጸሐፍትና የቤተ መቅደሱ መዘምራን ከሚከፍሉት ከማኅበራዊ ቀረጥ፣ ከንጉሣዊ ቀረጥና ከጨው ቀረጥ ነጻ ይሆናሉ":: (ዮሴፍ ወደ ኮርዮን፣ "አንቲኩዊቲስ 12.3.3)::

7፥26 *የማይታዘዝ ማንኛውም ሰው፣ ... ቅጣት ይፈጸምበት፤* ለዕዝራ የተሰጠው ሥልጣን ትልቅ ነው፤ ከመንፈሳዊ ጒዳይ አልፎ እስከ ሕዝባዊ አስተዳደር የሚደርስ ነበር፤ ምናልባትም ዕዝራ ይህን የተሰጠውን ሥልጣን ሥራ ላይ ለማዋል ብዙ ውጣ ውረድ ደርሶበት ሊሆን ይችላል፤ ይህም እርሱ ኢየሩሳሌም ከገባበት ጊዜ አንሥቶ፣ ነህምያ ከዐሥራ ሦስት ዓመት በኋላ እስከ መጣበት ጊዜ ድረስ ምን ሲሠራ እንደቆየ በግልጽ ያልታወቀውን ሁኔታ ለመገመት የሚያስችል ነው:: ንጉሡ ለዕዝራ የሰጠው ሥልጣንና ተልእኮ ቀዳማዊ ዳርዮስ ቀደም ሲል ዑጃሖርሰኔት የተባለውን ካህንና ምሁር ወደ ግብፅ መልሶ በላከው ጊዜ፣ ከሰጠው ሥልጣንና ድጋፍ ጋር የሚቀራረብ ነው:: እርሱም የግብፅን ሕግ በጽሑፍ እንዲያሰፍሩ የግብፅን ታላላቅ ሰዎች አዝዞ ነበር፤ ይህም ታላቅ ኀላፊነት ከ518 እስከ 503 ዓ.ቅ.ክ ፈጅቶአል::

7፥28 በእኔ፤ ዕዝራ በአንደኛ መደብ ነጠላ ቍጥር ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን ሲጠራ እናያለን፤ ይህም ከቍ 27 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 9 መጨረሻ ድረስ የሚዘልቀውን "የዕዝራ የግል ማስታወሻ" የተባለውን ክፍል ልዩ የሚያደርገው ነው::

*8፥1-21፤* ዕዝራ ከቁ 1-14 ከመስጴጦምያ ሲመለስ አብረውት የተመለሱትን ሰዎች ስም ዝርዝር አስፍሮአል፤ ከእነዚህም ውስጥ፣ የዐሥራ አምስት ግለሰብ ዘሮች ይገኙባቸዋል፤ ስማቸው ከተጠቀሰው ሌላ፣ የወንዶቹ ቁጥር በድምር 1496 ይሆናል፤ እንዲሁም ሴቶችና ሕጻናት ነበሩ (ቍ 21 ማብ ይመ) 40 የሚሆኑ ሌዋውያንና (የቍ 18-19):: 220 "የቤተ መቅደስ አገልጋዮች" ነበሩ (ቍ 20)::

8፥2 *ጌርሶን፤* የስሙን ትርጒም በተመለከተ የዘፀ 2፥22 አማራጭ ትርጒም ይመ፤ የሙሴና የሲፖራ የመጀመሪያው ወንድ ልጅ ስም ጌርሶን ነው:: *ኢታምር፤* የአራተኛው የአሮን ወንድ ልጅ ስም ነው (ዘፀ 6፥23)::

8፥3 *ዘካርያስና፤* ከቍ 11 ጋር ያነጻጽሩ:: የስሙም ትርጒም፣ "እግዚ አብሔር ያስታውሳል" ማለት ነው፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደ ሠላሳ የሚደርሱ ሰዎች በዚህ ስም ተጠርተዋል፤ ከእነዚህም መካከል የብሉይ ኪዳኑ ነቢይና የመጥምቁ ዮሐንስ አባት ይገኙበታል (ሉቃ 1፥5-67)::

8፥4 *ኤሊሆዔናይ፤* የስሙ ትርጒም፣ "ዐይኖቼ በእግዚአብሔር ላይ ናቸው" ማለት ነው፤ ይህ ስም የሚገኘው በዚህ ቦታና በ1ዜና 26፥3 ላይ ብቻ ነው፤ ከመዝ 25፥15 ጋር ያነጻጽሩ::

8፥6 *ዮናታን፤* የስሙ ትርጒም፣ "እግዚአብሔር ይሰጣል" ማለት ነው፤ በብሉይ ኪዳን ዐሥራ አምስት ሰዎች በዚህ ስም ተጠርተዋል:: *ዔቤድ፤* ምናልባት አብድዩ የሚለውን ስም የሚተካ አጭር ስም ሊሆን ይችላል፤ የስሙ ትርጒም፣ "የእግዚ አብሔር አገልጋይ" ማለት ነው (ከቍ 9 ጋር ያነጻጽሩ)::

8፥7 *ጎቶልያ፤* ዝነኛዋ ንግሥት የአክዓብ ሴት ልጅም፣ በዚሁ ስም ትጠራ ነበር (2ነገ 11)::

8፥8 *ሚካኤል፤* የስሙ ትርጒም፣ "እንደ እግዚአብሔር ያለ ማን አለ?" ማለት ነው፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዚህ ስም ሌሎች ዘጠኝ ሰዎችና ሊቀ መልአኩ ተጠርተዋል (ዳን 10፥13፤ ይሁ 9፤ ራእ 12፥7)::

8፥10 *ሰሎሚት፤* እንስታዊ ባሕርይ ቢኖረውም (በተጨማሪ የማሕ 6፥13 ማብ ይመ)፣ እዚህ ላይ እንደተገለጸው ሁሉ ወንዶችም ሳይቀሩ ይጠሩበታል፤ የግሪክ አቻው ሰሎሜ የሚለው ስም ነው::

8፥12 *ዓዝጋድ፤* የ2፥12 ማብ ይመ:: *ሃቃጣን፤* የስሙ

[13]ከአዶኒቃም ዘሮች፣ የመጨረሻዎቹ ስማ
ቸው ይህ ነው፤ ኤሊፋላት፣ ይዑኤልና ሸማያ፣
ከእነርሱም ጋር 60 ወንዶች፤
[14]ከበጉዋይ ዘሮች ዑታይና ዘቡድ፣ ከእነ
ርሱም ጋር 70 ወንዶች።

*ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ*

[15]እኔም ወደ አኅዋ በሚፈሰው ወንዝ አጠ
ገብ ሰዎቹን ሰበሰብኋቸው፤ በዚያም ሦስት ቀን
ቈየን፤ ሕዝቡንና ካህናቱን ስመለከት፣ ከሌዊ
ወገን የሆነ አንድም ሰው በዚያ አላገኘሁም።
[16]ስለዚህ መሪሕያኑን ኤልዓዛርን፣ አርኤልን፣
ሸማያን፣ ኤልናታንን፣ ያሪብን፣ ኤልናታን፣
ናታንን፣ ዘካርያስንና ሜሱላምን እንዲሁም
መምህራኑን ዮያሪብንና ኤልናታንን አስጠ
ራኋቸው፤ [17]እነርሱንም ካሲፍያ በሚባል ስፍራ
አለቃ ወደ ሆነው ወደ አዶ ላክኋቸው፤ በአም
ላካችን ቤት የሚያገለግሉ ሰዎችን ያመጡልን
ዘንድ በካሲፍያ የቤተ መቅደስ አገልጋዮች ለሆ
ኑት ለአዶና ለሥጋ ዘመዶቹ የሚናገሩትን
አስታወቅኋቸው። [18]መልካሚቱ የአምላካችን እጅ
በእኛ ላይ ስለ ነበረች፣ ከሞሖሊ ዘሮች የእስ
ራኤል ልጅ የሌዊ ልጅ የሆነውን ሰራብያ
ተብሎ የሚጠራውን አስተዋይ ሰው፣ ከእር
ሱም ጋር ዐሥራ ስምንት የሚሆኑ ወንዶች ልጆ
ቹንና ወንድሞቹን አመጡልን፤ [19]እንዲሁም
ሐሸብያንና ከሜራሪ ዘሮች የሻያን፣ ከወንድ
ሞቹና ከአጎቶቹ ወንዶች ልጆች ጋር 20 ወን
ዶችን አመጡልን። [20]በተጨማሪም ዳዊትና
ሹማምቱ ሌዋውያኑን እንዲረዳ ካቋቋሙት
ከቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ቡድን 220 አመጡ፤
እነዚህም ሁሉ በየስማቸው ተመዘገቡ።
[21]ራሳችንን በአምላካችን ፊት ዝቅ እንድ
ናደርግ፣ ጕዞውም ለእኛና ለልጆቻችን፣ ለንብ
ረታችንም ሁሉ የተቃና እንዲሆንልን፣ እዚ
ያው በአኅዋ ወንዝ አጠገብ ጾም ዐወጅሁ።
[22]"መልካሚቱ የአምላካችን እጅ በሚፈልጉት
ሁሉ ላይ ናት፤ እርሱን በሚተዉ ሁሉ ላይ
ግን ቍጣው ትወርድባቸዋለች" ብለን ለንጉሡ
ነግረነው ስለ ነበር፣ በመንገድ ላይ ከጠላት
የሚጠብቁን ወታደሮችንና ፈረሰኞችን እንዲ
ሰጠን ንጉሡን ለመጠየቅ ዐፍሬ ነበር። [23]ስለዚህ
ጾምን፤ ወደ አምላካችንም ስለዚህ ነገር ልመና
አቀረብን፤ እርሱም ጸሎታችንን ሰማ።
[24]እኔም ከዋና ዋናዎቹ ካህናትም ዐሥራ
ሁለት ሰዎችን፣ ከእነርሱም ጋር ሰራብያን፣
ሐሸቢያንና ከወንድሞቻቸውም መካከል ዐሥር
ሰዎችን ለየሁ፤ [25]ንጉሡ፣ አማካሪዎቹ፣ ሹሞ
ቹና በዚያ የነበሩ እስራኤል ሁሉ ለአምላካችን
ቤት የሰጡትን ብር፣ ወርቅና ዕቃ ሁሉ
መዝኜ ሰጠኋቸው። [26]ስድስት መቶ አምሳ
መክሊት[o] ብር፣ አንድ መቶ መክሊት[u] የብር
ዕቃዎች፣ አንድ መቶ መክሊት ወርቅ፣
[27]አንድ ሺህ ዳሪክ[w] የሚያወጡ ሃያ የወርቅ
ወጭቶችና እንደ ወርቅ ነጥረው ከሚያብረቀርቅ

8፥13 ዕዝ2፥13
8፥15 ቍ21:31፤ ዕዝ2፥40
8፥17 ዕዝ2፥43
8፥18 ቍ24፤ዕዝ5፥5
8፥20 1ዜና9፥2
8፥21 ቍ15፤መዝ5፥8፤ 27፥11፤107፥7
8፥22 ዘጸ31፥17፤ ዕዝ5፥5፤ነህ2፥9፤ ኤር41፥16
8፥23 2ዜና20፥3፤ ሐሥ14፥23
8፥24 ቍ18
8፥25 ቍ33

[o]26 22 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
[u]26 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
[w]27 8.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

ትርጉም፣ "ትንሹ" ማለት ነው፤ የሚገኘውም እዚህ ላይ ብቻ ነው። *ዮሐናን*፤ የ2፥46 ማብ ይመ።

8፥15 *ወደ አኅዋ በሚፈሰው ወንዝ፤* ምናልባት ወደ ኤፍራጥስ ወይም ወደ ጤግሮስ የሚፈስ ወንዝ ሊሆን ይችላል፤ (በሕዝ 1፥1 የተጠቀሰውም የኮቦር "ወንዝ" የቦይ ውሃ ነበር)። *ሦስት ቀን፤* ምናልባት ኒሳን በተባለው ወር ውስጥ ከዘጠነኛው እስከ ዐሥራ ሁለተኛው ቀን ያለውን ጊዜ ሊሆን ይችላል፤ ጕዞው የተጀመረው በዐሥራ ሁለተኛው ቀን ነው (ቍ 31 ይመ)። *ከሌዊ ወገን ... አላገኘሁም፤* ቀድሞ የሚሠሩት ተራ ሥራ ስለ ነበር፣ ምናልባት በምርኮ አገር የተሻለ ሥራ ስላገኙ ከዚያ ለመውጣት አልፈለጉ ይሆናል። በመዝ 137 ላይ የአይሁድ ረቢናት የሰጡት ትርጓሜ (ሚድራሽ) ከዚህ የሚከተለውን አፈ ታሪክ መሠረት ያደረገ ነበር፤ በተጋዡ ሕዝብ መካከል ሌዋውያን ቢኖሩም አገልግሎቱን ግን ማከናወን አልቻሉም፤ ምክንያቱም ናቡከደነፆር የጽዮንን መዝሙር እንዲዘምሩለት በጠየቃቸው ጊዜ፣ "እምቢ ስላሉት በገና መጫወት እንዳይችሉና እንዳ ይዘምሩ የጣቶቻቸውን አጽቆች (ሜፎች) እየቈረጠ ስለጣለው" የክህነት ሥራቸውን በሙሴ ሕግ መሠረት ማከናወን አልቻሉም። በግሪኮች ዘመነ መንግሥትም (ታላቁ እስክንድር በ33 ዓ.ቅ.ክ ላይ መካከለኛውን ምሥራቅ ድል አድርጎ ከያዘ በኋላ) የሌዋውያን አገልግሎት ከስሞ ነበር፤ ሆኖም በሙት ባሕር አካባቢ ኩምራን በሚባል ስፍራ የተገኙት "የቤተ መቅደሱ ጥቅልል መጽሐፍ"፣ ሌዋውያን ትልቅ የአገልግሎት ሚና እንደ ነበራቸው ይናገራል። በገጽ 1422 ላይ በሁለቱ ኪዳናት መካከል የነበረው ዘመን የሚለውን ይመ።

8፥16 *አርኤልን፤* የስሙ ትርጉም፣ "የእግዚአብሔር አንበሳ" ወይም "የመሠዊያ ማንደጃ" ማለት ነው (የኢሳ 29፥1፡ 2:7 ማብ ይመ)። የሰው መጠሪያ ስም ሆኖ የሚገኘው እዚህ ላይ ብቻ ነው። *ሜሱላምን፤* ምናልባት የስሙ ትርጉም፣ "የተሸለመ" ማለት ሊሆን ይችላል፤ አንዳንድ ሰዎች በዕዝ 10፥15 ላይ እንደ ተጻፈው፣ ባዕዳን ሚስቶችን መፍታት አይገባንም ብለው የዕዝራን ሐሳብ ከተቃወሙት ሰዎች መካከል አንዱ ሜሱላም ነው ይላሉ። *መምህራኑን፤* በቁሙ ሲተረጎም "አስተዋይ የሚያደርጉ" የሚል ፍቺ አለው፤ በ1ዜና 25፥8 ላይ "አስተማሪ" የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፤ እንዲሁም በ2ዜና 35፥3፤ በነህ 8፥7:9 ላይ ደግሞ "ያስተምሩ" ወይም "የሚያስተምሩ" ተብሎአል።

8፥17 *ካሲፍያ፤* አንዳንዶች ይህ ቦታ ከጊዜ በኋላ የጳርቴ ግዛት ዋና ከተማ የሆነው ቀሲፎን በተመሠረተበት ስፍራ ላይ እንደ ነበረ ይናገራሉ፤ ይህም ከባቢሎን በስተሰሜን በጤግሮስ ወንዝ አጠገብ ነበር።

8፥18-19 *ዐሥራ ስምንት የሚሆኑ ወንዶች ... ሃያ ወንዶች፤* ከዕዝራ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፈቃደኞች ሆነው የተገኙት ከሁለት ቤተ ሰብ የተገኙ 40 ያህል ሌዋውያን ብቻ ነበሩ።

8፥20 *ከቤተ መቅደሱ አገልጋዮች፤* የ2፥43-57 ማብ ይመ።

8፥21 *ጕዞውም ... የተቃና፤* በቁሙ "ቀጥ ያለ መንገድ" ማለት ሲሆን፣ መሰናክልና አደጋ የሌለበት ማለት ነው (ቍ 31 ይመ፤ ከምሳ 3፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። *ለልጆቻችን፤* አባባሉ በሌላ ቦታ (ለምሳሌ በዘፍ 43፥8 ላይ) አዛውንትንና ሴቶችን ጨምሮ ለመግለጽ ገብቶ ይገኛል። *ንብረታችን፤* የያዙት በርከት ያለ ሀብት ወንበዴዎችን ለዝርፊያ የሚያነሣሣ ነበር።

8፥22 *ዐፍሬ ነበር፤* ቅዱስ ስላልሆነ ዕፍረት መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ይናገራል (ኤር 48፥13፤ 49፥23፤ ሚክ 3፥7)፤ አልፎ አልፎ ደግሞ እዚህ ላይ ስለተወሣው ዐይነት ዕፍረት ይናገራል። ዕዝራ በእዚህ ዐይነቱ ጉዳይ ዐይነ ዐፋር ነበር (በተጨማሪ 9፥6 ይመ)። እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ከእርሱ ጋር በመሆን እንደሚጠብቀው፣ በእምነት በሕዝብ ፊት ተናግሮ ስለ ነበር፣ አሁን ከሰው ዘንድ ጥበቃ መሻቱ አሳፋሪው። በመስጴጦምያና በፓለስቲና መካከል በሚደረገው ጕዞ በብዙ ሰዎች ላይ ከባድ አደጋ ይደርስ ነበር። ከዐሥራ ሦስት ዓመት በኋላ ግን ነህምያ የተጓዘው በታጠቁ ሰዎች ታጅቦ ነበር። ይሁን እንጂ የነህምያ እምነት ትንሽ ነበር ማለት አንችልም (የነህ 2፥9 ማብ ይመ)።

8፥23 *ጾምን ... ልመና፤* ጾምና ጸሎት አብረው እንደ ሚሄዱ ነህ 1፥4፤ ዳን 9፥3፤ ማቴ 17፥21፤ ሐሥ 14፥23 ይመ።

8፥25 *የሰጡትን፤* በቁሙ "ወደ ላይ ያነሡትን" ማለትም የሠውትን የሚል ትርጕም አለው (ከዘፀ 25፥2፤ 35፥5፤ ዘሌ 7፥14 ጋር ያነጻጽሩ)። በዘዳ 12፥6 ላይ ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል፣ "ልዩ ስጦታ" ተብሎ ተተርጕሞአል።

8፥26 *ስድስት መቶ አምሳ መክሊት ... መቶ መክሊት፤* እጅግ ብዙ ስጦታ ነው፤ በአሁኑ ጊዜ በብዙ ሚሊዮን ይገመታል። በተጨማሪ የ7፥22 ማብ ይመ።

8፥27 *ዳሪክ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ ቃሉ ተጽፎ የሚገኘው እዚህ ላይና በ1ዜና 29፥7 ላይ ብቻ ነው (ነገር ግን የ2፥69 ማብ ይመ)። *ከሚያብረቀርቅ፤* የዚህ ዐይነቱ ናስ ብሩህ የሆነ ቢጫ መልክ ያለውና ከመዳብ ጋር የተቀየጠ ሊሆን ይችላል፤

ናስ የተሠሩ ሁለት ዕቃዎችን መዝኜ በእጃ
ቸው አስረከብኳቸው::
28እንዲህም አልኳቸው፤ "እናንተና እነ
ዚህ ዕቃዎች *ለእግዚአብሔር* ተቀድሳችኋል፤
ብሩና ወርቁ ለአባቶቻችሁ ስምባክ *ለእግዚ
አብሔር* በበጎ ፈቃድ የቀረበ መባ ነው::
29ኢየሩሳሌም በሚገኘው *በእግዚአብሔር* ቤት
ክፍሎች ውስጥ በዋና ዋናዎቹ ካህናት፣
በሌዋውያኑና በየቤተ ሰቡ የእስራኤል አለ
ቆች ፊት እስክትመዝኗቸው ድረስ በጥን
ቃቄ ጠብቋቸው::" 30ከዚያም ካህናቱና ሌዋ
ውያኑ ኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ወደ ስም
ባካችን ቤት እንዲሄድ የተመዘነውን ብር፣
ወርቅና ንዋያተ ቅድሳት ተረከቡ::
31እኛም በመጀመሪያው ወር ዐሥራ
ሁለተኛው ቀን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ
ከአኅዋ ወንዝ ተነሣን:: የስምባካችን እጅ በላያ
ችን ነበረች፤ እርሱም ከጠላቶቻችንና በመን
ገድ ላይ ከሚሸምቁ አዳነን:: 32ኢየሩሳሌምም
ደረስን፤ በዚያም ሦስት ቀን ዐረፍን::
33በአራተኛው ቀን ብሩን፣ ወርቁንና
ንዋያተ ቅድሳቱን በስምባካችን ቤት መዝነን
ለኦሪዮ ልጅ ለካህኑ ለሜሪሞት በእጁ አስረ
ከብነው፤ ከእርሱም ጋር የፊንሐስ ልጅ አልዓ
ዛር፣ ሌዋውያኑ የኢያሱ ልጅ ዮዛባትና የቢ
ንዊ ልጅ ኖዓድያ ነበሩ:: 34ሁሉም ነገር
ተቈጠረ፤ ተመዘነም፤ የተመዘነውም ሁሉ
በዚያኑ ጊዜ ተመዘገበ::

8፥28 ዘሌ21፥6፤ 22፥2-3
8፥31 ቍ15፤ዕዝ5፥5
8፥32 ዘፍ40፥13
8፥33 ቍ25፤ነህ3፥4፡21፡24፤11፥16
8፥35 ዘሌ1፥3፤ 2ዜና29፥21፡24፤30፥24፡
8፥36 ዕዝ7፥21-24፤ ነህ2፥7፤አስ9፥3
9፥1 ዘፍ10፥16፤ 19፥37፡38፤ዘፀ13፥5፤ 23፥28፤ዘዳ20፥17፤ ኢሱ3፥10፤15፥8፤ መሳ3፥5፤1ነገ9፥20፤ 2ዜና8፥7፤ዕዝ6፥21፤ ነህ9፥8
9፥2 ዘፀ22፥31፤ 34፥16፤ዘሌ27፥30፤ ዘዳ14፥2፤ሩት1፥4፤ ዕዝ10፥2፤መዝ106፥35
9፥3 ዘፀ32፥19፤ 33፥4፤ዘኍ14፥6
9፥4 ዕዝ10፥3፤ነህ1፥4፤ መዝ119፥120፡136፤ ኢሳ66፥2፡5፤ዳን10፥2

35ከዚያም ከምርኮ የተመለሱት፣ ለእስራ
ኤል ሁሉ ዐሥራ ሁለት ወይፈኖችን፣ ዘጠና
ስድስት አውራ በጎችን፣ ሰባ ሰባት ተባዕት ጠቦ
ቶችን፣ ለእስራኤል ስምባክ የሚቃጠል መሥ
ዋዕት አቀረቡ፤ ለኀጢአት መሥዋዕት ደግሞ
ዐሥራ ሁለት ተባዕት ፍየሎችን አቀረቡ፤
ይህም ሁሉ *ለእግዚአብሔር* የቀረበ የሚ
ቃጠል መሥዋዕት ነበር:: 36የንጉሡንም ትእ
ዛዝ ለንጉሡ እንደራሴዎችና በኤፍራጥስ
ማዶ ለሚገኙት አገረ ገዦች ሰጡ፤ እነር
ሱም ሕዝቡንና የእግዚአብሔርን ቤት ረዱ::

### *ከባዕዳን ጋር ስለተደረገው ጋብቻ የዕዝራ ጸሎት*

9እነዚህ ነገሮች ከተፈጸሙ በኋላ መሪዎቹ
ወደ እኔ መጥተው እንዲህ አሉኝ፤ "ካህናቱ
ንና ሌዋውያኑን ጨምሮ የእስራኤል ሕዝብ
ከጎረቤቶቻቸው ከከነዓናውያን፣ ከኬጢያው
ያን፣ ከፌርዛውያን፣ ከኢያቡሳውያን፣ ከአሞና
ውያን ርኩሰት ራሳቸውን አልለዩም:: 2ሴቶቻ
ቸውን ለራሳቸውና ለልጆቻቸው ሚስት አድር
ገው ወስደዋል፤ የተቀደሰውንም ዘር ከምድር
ሕዝቦች ጋር ደባልቀዋል፤ በዚህ በደል ዋነኛ
የሆኑትም መሪዎቹና ሹማምንቱ ናቸው::
3እኔም ይህን በሰማሁ ጊዜ፣ መጐናጸፊያ
ዬንና ካባዬን ቀደድሁ፤ የራሴን ጠጕርና
ጢሜን ነጨሁ፤ እጅግ ደንግጬም ተቀመጥሁ::
4በደል ከፈጸሙት ምርኮኞች የተነሣም በእስራ
ኤል ስምባክ ቃል የተንቀጠቀጡት ሁሉ በዙሪ

ከብሩህነቱም የተነሣ ወርቅ ስለሚመስል፣ በጥንት ዘመን ትልቅ ዋጋ ነበረው:: (በዕብራይስጥ "ቢጫ" ለማለት የገባው ቃል እዚህ ላይ "ንጹሕ" ለተባለው ቃል ከገባው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተቀራራቢ ነው፤ ይህም የሚገኘው በዘሌ 13፥30፡32፡36 ላይ ነው::)

8፥31 *በዐሥራ ሁለተኛው ቀን፤* የቍ 15፤ የ7፥7-9 ማብ ይመ::

8፥32 *ሦስት ቀን ዐረፍን፤* ነህምያም ኢየሩሳሌም ከደረሰ በኋላ ይህንኑ ያህል ጊዜ ዐርፎ ነበር (ነህ 2፥11)::

8፥33 *ለኦርዮ ልጅ ... ለሜሪሞት፤* ምናልባት የቅጥሩን ሁለት ክፍሎች የጠገነው ይህ ሰው ሊሆን ይችላል (ነህ 3፥4፡21)::

8፥34 *ተመዘገበ፤* በባቢሎናውያን ልማድ (ለምሳሌ ቤሐሙራቢ ሕግ) መሠረት ማንኛውም ስምምነቶች፣ (የሽያጭም ሆነ የጋብቻ) በጽሑፍ ተመዝግቦ መቀመጥ ነበረበት:: ዕዝራ ከግምጃ ቤት ለወጣው ንብረት ማስረጃ እንዲሆነው የንጉሡን የአርጤክስስን ፊርማ ጠይቆ ይሆናል::

8፥35 *መሥዋዕት አቀረቡ፤* የተባዕት ፍየሎች ቍጥር አንድ ዐይነት ከመሆኑ በስተቀር፣ እዚህ ላይ ለመሥዋዕት የቀረቡት እንስሳት ብዛት በዘሩባቤል መሪነት ከምርኮ የተመለሰው ሕዝብ (6፥17) ካቀረበው የእንስሳት ቍጥር በጣም ያነሰ ነው፤ ሆኖም ዘሩባቤል ይዞት የወጣው የቤተ ሰብ ብዛት እዚህ ላይ ከተጠቀሱት እጅግ ይበልጥ ነበር::

9፥1 *እነዚህ ነገሮች ከተፈጸሙ በኋላ ... ራሳቸውን አልለዩም፤* ዕዝራ ኢየሩሳሌም የደረሰው በአምስተኛው ወር ነበር (7፥9):: እስራኤላውያን ከባዕዳን ሴቶች ጋር ስለ መጋባታቸው መነገር የተጀመረው፣ ዕዝራ ኢየሩሳሌም ከደረሰ ከአራት ወር በኋላ በዘጠነኛው ወር ነበር (10፥9):: ጒዳዩን ወደ ዕዝራ ያቀረቡት የሕዝቡ መሪዎች ሳይሆኑ፣ ራሱ ሕዝቡ ነበር፤ መሪዎቹ ግን ራሳቸው በዚህ ዐይነቱ በደል ውስጥ ተዘፍቀው ነበር (ቍ 2):: ዕዝራ በነበረበት ጊዜ ትንቢት የተናገረው ነቢዩ ሚልክያስ፣ አንዳንድ አይሁድ ትዳራቸውን አፍርሰው የአረማውያንን ሴት ልጆች እንዳገቡ ተናግሯል (ሚል 2፥10-16)፤ ምናልባትም ያገቡአቸው የታወቁ ባለ መሬቶችን ሴት ልጆች ሊሆን ይችላል:: ለዚህ ዐይነቱ ጋብቻ ምክንያት የሚሆነው ምርኮኞቹ ወደ አገራቸው በሚመለሱበት ጊዜ፣ አብረዋቸው የመጡት የአይሁድ ሴቶች ቍጥር፣ አነስተኛ በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም:: በዕዝራና በነህምያ ዘመን፣ ስለ ጋብቻ የተሰጣቸውን መመሪያ ወደ ጐን ትተው፣ ከሌላ ወገን ጋር በመጋባት የተጀመረው፣ በግብፅ አገር ኤሌፋንታይን በተባለው ስፍራ ነበር:: በአይሁድ ማኅበረ ሰብ ላይ የደረሰው ነገር እንደ አንድ ምሳሌ የሚታይ ጒዳይ ነው፤ በዚያ ቦታ የነበሩት አይሁድ፣ የአሕዛብን ሴቶች በማግባታቸው፣ ከእግዚአብሔር በተጨማሪ ሌሎችንም አማልክት ሲያመልኩ ተገኝተዋል፤ ከዚህም የተነሣ በኤሌፋንታይ የነበረው የአይሁድ ማኅበረ ሰብ ቀስ በቀስ በአሕዛብ እየተዋጠ ጠፋ:: *ከጎረቤቶቻቸው፤* በዚህ ስፍራ ላይ የተጠቀሱት ስምንት ነገዶች፣ እስራኤላውያን ከነዓንን ከመውረራቸው በፊት በዚያ የነበሩ የአገሩ ተወላጆች ናቸው (የዘፀ 3፥8 ማብ ይመ):: ከምርኮው ዘመን በኋላ በዚያ የቀሩት አሞራውያን፣ ሞዓባውያንና ግብፃውያን ብቻ ናቸው (ከ2ዜና 8፥7-8 ጋር ያነጻጽሩ):: *ከነዓናውያን፤* የዘፍ 10፥6 ማብ ይመ:: *ኬጢያውያን፤* የዘፍ 10፥15 ማብ ይመ:: *ፌርዛውያን፤* የዘፍ 13፥7 ማብ ይመ:: *ኢያቡሳውያን፤* የዘፍ 10፥16 ማብ ይመ:: *አሞናውያን፤ ሞዓባውያን፤* የዘፍ 19፥36-38 ማብ ይመ:: *አሞራውያን፤* የዘፍ 10፥16 ማብ ይመ::

9፥2 *የተቀደሰውን ዘር፤* በኢሳ 6፥13 ላይ ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ሐረግ "ቅዱሱንም ዘር" ተብሎ ተተርጕሞአል:: *ዋነኛው የሆኑትም፤* የክፉ ምሳሌ የሆኑ ማለት ነው (10፥18 ይመ):: *በዚህ በደል፤* 10፥6፤ ኢያ 22፥16፤ ዳን 9፥7 ይመ:: ከእግዚአብሔር ወገን ያልሆኑ ሰዎችን ማግባት ማለት ለእስራኤል ሕዝብ ታማኝ አለመሆን ማለት ነው::

9፥3 *መጐናጸፊያዬንና ካባዬን ቀደድሁ፤* ጥልቅ የሆነ ኀዘንና ጭንቀት የሚገለጽበት ዐይነተኛ መንገድ ነው (ቍ 5፤ ዘፍ 37፥29፡34፤ ኢሱ 7፥6፤ መሳ 11፥35፤ 2ሳሙ 13፥19፤ 2ዜና 34፥27፤ አስ 4፥1፤ ኢዮ 1፥20፤ ኢሳ 36፥22፤ ኤር 41፥5፤ ማቴ 26፥65 ይመ):: *የራሴን ጠጕርና ጢሜን ነጨሁ፤* እንዲህ ያለው ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተለመደም፤ በሌላ ቦታ የምናየው ሰው ጠጕሩን ወይም ጢሙን ወይም ሁለቱንም መላጨቱን ነው (ኢዮ 1፥20፤ ኤር 41፥5፤ 47፥5፤ ሕዝ 7፥18፤ አሞ 8፥10):: ነህምያ እንዲህ ያለው ሕገ ወጥ ጋብቻ ባጋጠመው ጊዜ፣ የራሱን ጠጕር በመንጨት ፈንታ ይህን በደል የፈጸሙትን ሰዎች ጠጕር ነጨ (ነህ 13፥25)::

9፥4 *የተንቀጠቀጡት ሁሉ፤* ከዘፀ 19፥16፤ ከኢሳ 66፥2፤ ከዕብ 12፥21 ጋር ያነጻጽሩ:: *እጅግ እንደ ደነገጥሁ፤* ቍ 3 ይመ፤ ከዳን 4፥19፤ 8፥27 ጋር ያነጻጽሩ:: *ሠርክ መሥዋዕት፤* ዘፀ 12፥6 ይመ:: ነገሩን ከዕዝራ ጆሮ እንዲደርስ ያደረጉ ሰዎች፣ ብዙ ሰዓት በድንጋጤ እንዲቀመጥ በጠዋት ሳይነግሩት አልቀሩም:: የሠርክ ወይም የምሽት መሥዋዕት ብዙውን ጊዜ የሚቀርበው በዘጠኝ ሰዓት ገደማ ነው፤ ጸሎትና ንስሓ የሚቀርበውም በዚሁ ሰዓት ነበር (ሐሥ 3፥1)::

ያዬ ተሰበሰቡ፤ እኔም እስከ ሠርክ መሥዋዕት
ድረስ እጅግ እንደ ደነገጥሁ በዚያው ተቀ
መጥሁ።
5ከዚያም፣ የሠርክ መሥዋዕት በሚቀር
ብበት ጊዜ፣ የተቀደደውን መጐናጸፊያዬንና
ካባዬን እንደ ለበስሁ በሐዘን ከተቀመጥሁ
በት ተነሣሁ፤ በጕልበቴም ተንበርክኬ ወደ
አምላኬ ወደ *እግዚአብሔር* እጆቼን በመዘር
ጋት፣ 6እንዲህ ስል ጸለይሁ፤
"አምላኬ ሆይ፤ ኀጢአታችን ከራሳችን በላይ
ሆኖአል፤ በደላችንም እስከ ሰማያት ደርሶአል፤
አምላኬ ሆይ፤ ፊቴን ወደ አንተ ቀና ለማድረግ
ዐፈርሁ፤ እጅግም ፈራሁ። 7ከአባቶቻችን ዘመን
ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በደላችን ታላቅ ነው።
ከኀጢአታችንም የተነሣ፣ ዛሬ እንደ ሆነው ሁሉ
እኛምሆንን ነገሥታቶቻችንና ካህናቶቻችን
በባዕዳን ነገሥታት እጅ ወድቀን ለሰይፍ፣
ለምርኮ፣ ለብዝበዛና ለውርደት ተዳርገናል።
8"አሁን ግን *እግዚአብሔር* አምላካችን ቅሬታ
ይተውልን ዘንድ በመቅደሱም ውስጥ ጽኑ
ስፍራ ይሰጠን ዘንድ፣ ለጥቂት ጊዜ ቸርነቱን
አሳይቶናል፤ ስለዚህ አምላካችን ለዐይናችን
ብርሃን ሰጠን፤ በባርነትም ሳለን ለጥቂት ጊዜ
ዕረፍት ሰጠን። 9ባሮች ብንሆንም፣ አምላ
ካችን ግን ባሮች ሆነን እንድንቀር አልተወ
ንም፤ ነገር ግን በፋርስ ነገሥታት ፊት ቸር
ነቱን አሳየን፤ የአምላካችንን ቤት እንደ ገና
እንድንሠራና ፍርስራሾቹን እንድንጠግን አዲስ
ሕይወት ሰጠን፤ በይሁዳና በኢየሩሳሌ ምም
የመከላከያ ቅጥር ሰጠን።
10አሁን ግን አምላካችን ሆይ፤ ከዚህ በኋላ

9፥5 ዘፀ29፥41፤ ነህ8፥6፤ መዝ28፥2፤134፥2
9፥6 2ዜና28፥9፤ ኢዮ42፥6፤መዝ38፥4፤ ኢሳ59፥12፤ ኤር3፥25፤ 14፥20፤31፥19፤ራእ18፥5
9፥7 ዘዳ28፥37፡64፤ 2ዜና29፥6፤ሕዝ21፥1-32
9፥8 ዘፍ45፥7፤ መዝ13፥3፤19፥8፤ 25፥16፤67፥1፤ 119፥58፤መክ12፥11፤ ኢሳ22፥23፤33፥2
9፥9 ዘፀ1፥14፤ 2ነገ25፥28፤ነህ9፥36፤ መዝ69፥35፤106፥46፤ ኢሳ43፥1፤ 44፥26፤ 48፥20፤52፥9፤63፥9፤ ኤር32፥44፤ ዘካ1፥16-17
9፥10 ዘዳ11፥8፤ ኢሳ1፥19-20
9፥11 ዘሌ18፥25-28፤ ዘዳ4፥5፤9፥4፤18፥9፤ 1ነገ14፥24
9፥12 ዘፍ45፥18፤ ዘፀ34፥15፤ዘዳ11፥8፤ መዝ103፥17፤ሕዝ37፥25፤ ኢል3፥20
9፥13 ዘፀ32፥22፤ ኢዮ11፥6፤15፥5፤22፥5፤ 33፥27፤መዝ103፥10
9፥14 ዘዳ9፥8፡14፤ ነህ13፥27
9፥15 ዘፍ18፥25፤ 1ነገ8፥47፤2ዜና12፥6፤ ነህ9፥8፤መዝ51፥4፤ 76፥7፤129፥4፤130፥3፤ 145፥17፤ኢሳ24፥16፤ ኤር12፥1፤23፥6፤33፥16፤ ሰቆ1፥18፤ዳን9፥7፤ሶፎ3፥5፤ ሚል3፥2

ምን እንላለን? ትእዛዞችህን ኢቃለናልና፤ 11ያቃለ
ልነውም በባሮችህ በነቢያት ፣ አማካይነት፣
'ለመውረስ የምትገቡባት ምድር በሕዝቦቿ
ርኵሰት ተበክላለች፤ ከዳር እስከ ዳርም በአስ
ጸያፊ ድርጊታቸውና በርኵሰታቸው ተሞል
ታለች'፣ 12ስለዚህ ሴቶች ልጆቻችሁን ለወንዶች
ልጆቻቸው አትስጡ፤ ሴቶች ልጆቻቸውንም
ለወንዶች ልጆቻችሁ አትውሰዱ። ብርቱዎች
እንድትሆኑ፣ የምድሪቱን መልካም ነገር እንድ
ትበሉና ለልጆቻችሁም የዘላለም ርስት እንድ
ታወርሱ ከእነርሱ ጋር ምንም ዐይነት ውል
አታድርጉ' ብለህ የሰጠኸውን ትእዛዝ ነው።
13"ይህ ሁሉ የደረሰብን በክፉ ሥራች
ንና በብዙ በደላችን ምክንያት ነው፤ አምላ
ካችን ሆይ፤ አንተ ግን እንደ በደላችን ብዛት
አልቀጣኸንም፤ ይልቁንም ቅሬታን ተውህ
ልን። 14ታዲያ ትእዛዞችህን እንደ ገና ተላል
ፈን እንዲህ ያለውን አስጸያፊ ድርጊት ከሚፈ
ጽሙ ሕዝቦች ጋር መጋባት ተገቢ ነውን?
አንተስ ቅሬታ እስከማይኖር ወይም፣ አንድም
ሰው እስከማይድን ድረስ ተቈጥተህ አታጠ
ፋንምን? 15የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ አንተ ጻድቅ ነህ፤ እኛም በዚህ ዕለት ተር
ፈን በሕይወት አለን። እነሆ በፊትህ ከነበደ
ላችን ቀርበናል፤ ከበደላችን የተነሣ ግን
በፊትህ ሊቆም የሚችል ማንም የለም።

### *ሕዝቡ ኀጢአቱን ተናዘዘ*

10 ዕዝራ በእግዚአብሔር ቤት ፊት ወድቆ
በሚጸልይበት፣ በሚናዘዝበትና በሚ

10፥1 ዘኍ25፥6፤ 2ዜና20፥9፤ዳን9፥20

9፥5 *በሐዘን ከተቀመጥሁበት*፤ ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል ከጊዜ በኋላ "ጾም" የሚል ትርጕም ይዞአል። የዘሌ 16፥29፡31 ማብ ይመ። *በጕልበቴም ተንበርክኬ*፤ ከ1ነገ 8፥54፤ መዝ 95፥6፤ ዳን 6፥10 ጋር ያነጻጽሩ። *እጆቼን ... በመዘርጋት*፤ የዘፀ 9፥29 ማብ ይመ። የዕዝራ ጸሎት (ቍ 6-15) ከነህምያና (ነህ 9፥5-37) ከዳንኤል (ዳን 9፥4-19) ጸሎት ጋር ሊነጻጸር ይችላል።

9፥6 *ኀጢአታችን ... በደላችንም*፤ ከቍ 7፡13፡15፤10፤ 10፡19፤ 1ዜና 21፥3፤ 2ዜና 24፥18፤ መዝ 38፥4 ጋር ያነጻጽሩ። *ወደ ሰማያ የደረሰ*፤ የእግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረት ከበደላችን ሁሉ በላይ ነው (መዝ 103፥11-12)። *ዐፍሬአለሁ፤ ተዋርጃለሁም*፤ 8፥22 እና ማብ እንዲሁም ሉቃ 18፥13 ይመ። ዕዝራ ስለ ራሱ በደልና ስለ ሕዝቡ ኀጢአት በእግዚአብሔር ፊት ዕፍረትና በሕዝቡም ፊት ውርደት ተሰማው። እነዚህ ሁለት የዕብራይስጥ ቃላት አብዛኛውን ጊዜ አይነጣጠሉም፤ መዝ 35፥4፤ ኢሳ 45፥16፤ ኤር 31፥19 ይመ።

9፥7 *ከአባቶቻችን ዘመን ጀምሮ*፤ እስራኤላውያን ከቀደምት አባቶቻቸው ጋር ፍጹም የሆነ ኅብረትና አንድነት እንዳላቸው በሚገባ ያውቃሉ። *ለሰይፍ*፤ ከነህ 4፥13 ጋር ያነጻጽሩ። በሕዝ 21 ላይ "የባቢሎን ንጉሥ ሰይፍ" (21፥19) እግዚአብሔር ፍርዱን የሚገልጥበት መሣሪያ እንደሆነ ተገልጾአል። *ውርደት*፤ ከዳን 9፥7-8፤ ከ2ዜና 32፥21 ጋር ያነጻጽሩ።

9፥8 *ቅሬታ*፤ ዘፍ 45፥7፤ ኢሳ 1፥9፤10፥20-22 እና ማብ ይመ። *ጽኑ ስፍራ*፤ በቀሙ "ምስማር" ወይም "ችንካር" ማለት ሲሆን፣ በቀጥታ ግድግዳ ላይ የሚመታውን ምስማር (ኢሳ 22፥23 እና ማብ ይመ) ወይም መሬት ውስጥ የሚተከለውን የድንኳን ካስማ ያመለክታል (ኢሳ 33፥20፤ 54፥2)። *ለዐይናችን ብርሃን*፤ የብርሃን ድምቀት አየለ ማለት ብርታትና ደስታ ተጨመረ ማለት ነው (መዝ 13፥3፤ 19፥8፤ መክ 8፥1)።

9፥9 *የፋርስ ነገሥታት*፤ የአቃሚኒድ ሥርወ መንግሥት ያላቸው የፋርስ ነገሥታት ለአይሁድ ሕዝብ በጎ ሥራ ሠርተዋል፤ ቂሮስ (ከ539-530 ዓ.ቅ.ክ.) ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ፈቅዶላቸው ነበር (ም 1)፤ ስሙ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይጠቀስም ልጁ ካምብሲስ (ከ530-522 ዓ.ቅ.ክ) በኤሌፋንታይ ከተገኘው የፓጺስ ጽሑፍ እንደምንረዳው፣ የአይሁድን ሕዝብ ይወድ ነበር፤ ቀዳማዊ ዳርዮስ (ከ522-486 ዓ.ቅ.ክ) ቂሮስ አውጥቶት የነበረውን ዐዋጅ አድሶት ነበር (ም 6)፤ ልጁ ጠረክሲስ (ከ486-465 ዓ.ቅ.ክ) የአይሁድ ሕዝብ ልዩ ልዩ መብት እንዲሰጣቸውና ጥበቃም እንዲደረግላቸው ፈቅዶ ነበር (አስ 8-10)፤ ልጁ ቀዳማዊ አርጤክስስ (465-424 ዓ.ቅ.ክ) ለዕዝራ (ም 7) እንዲሁም ለነህምያ (ነህ 2) መብትና ሥልጣን ሰጥቶአቸው ነበር። *ፍርስራሾቹን እንድንጠግን*፤ እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ፍርስራሽ እንደሚጠገን ኢሳይያስ ተንብዮ ነበር (ኢሳ 44፥26)፤ ያን ጊዜ በዝማሬ ትፈነድቃለች (ኢሳ 52፥9፤ከ58፥12፤ 61፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። *የመከላከያ ቅጥር*፤ በሚክ 7፥11 ላይ ብቻ ስለ ከተማ ቅጥር ተነግሮአል፤ እዚህ ላይ ግን ቃሉ የገባው በትእምርታዊ ዘይቤ ነው (ከዘካ 2፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ)።

*9፥11-12*፤ ይህ ክፍል የያዘው ሐሳብ በሌሎችም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ይገኛል፤ ከእነዚህም ዘዳ 11፥8-9፤ ኢሳ 1፥19፤ ሕዝ 37፥25 የመሳሰሉት ክፍሎች ይገኛሉ።

9፥11 *በባሪያዎችህ በነቢያት*፤ የኤር 7፥25፤ ዘካ 1፥6 ማብ ይመ። *ርኵሰት*፤ በከነዓን ምድር የነበረውን የጣዖት አምልኮ ልማድና አብሮት የሚሄደውን የርኩሰት ተግባር የሚያመለክት ነው (ዘሌ 18፥3፤ 2ዜና 29፥5፤ ሰቆ 1፥17፤ ሕዝ 7፥20፤ 36፥17 ይመ)። የከነዓናውያን ድርጊትና እምነት በጥንት ዑጋሪታውያን ጽሑፎች ላይ ሰፍሮ ይገኛል።

9፥14 *ተቈጥተህ*፤ የእግዚአብሔር ቍጣ በእስራኤላውያን ላይ የወረደው፣ ከአምላካቸው ጋር የገቡትን ኪዳን አፍርሰው ስለ ተገኙ ነው (ዘዳ 7፥4፤ 11፥16-17፤ 29፥26-28፤ ኢሱ 23፥16፤ መሳ 2፥20)።

9፥15 *አንተ ጻድቅ ነህ*፤ የመዝ 4፥1 ማብ ይመ። *ከነበደላችን*፤ እግዚአብሔር ምን ያህል ቅዱስ እንደ ሆነ ከተረዳን፣ የማንረባ መሆናችንን ወዲያውኑ እንገነዘባለን። ኢሳ 6፥1-5፤ ሉቃ 5፥8 ይመ፤ እስራኤል በኅብረት ያቀረበችውን ዋይታ መዝ 44፥60፤74፤79-80፤83፤85፤ 90፤ 108፤126፤129፤137 ላይ ይመ።

10፥1 *በሚያለቅሱት ጊዜ*፤ ዕዝራ በዝምታ እያነባ ብቻ ሳይሆን እየጮኸም ነበር (3፥13 እና ነህ 1፥4፤ ኢል 2፥12 ይመ)። *ወድቆ*፤ ነቢያትና ሌሎች የሕዝብ መሪዎች አንዳንድ ጊዜ ሕዝቡን ለማስተማር

ያለቅስበት ጊዜ ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆች
የሚገኙበት እጅግ ብዙ የእስራኤል ማኅበር
በዙሪያው ተሰበሰበ፤ እነርሱም እንደዚሁ አምር
ረው አለቀሱ:: 2ከዚያም ከኤላም ዘሮች አንዱ
የሆነው የይሒኤል ልጅ ሴኬንያ ዕዝራን እን
ዲህ አለው፤ በዙሪያችን ካሉት አሕዛብ፣ ባዕ
ዳን ሴቶችን በማግባታችን በአምላካችን ታማ
ኞች ሆነን አልተገኘንም፤ ይህም ሆኖ አሁንም
ለእስራኤል ተስፋ አለ:: 3አሁንም እንደ ጌታዬ
ምክርና የአምላካችንን ትእዛዝ እንደሚፈሩ
ሰዎች እነዚህን ሴቶችና ልጆቻቸውን ለመስ
ደድ በአምላካችን ፊት ቃል ኪዳን እንግባ፤ በሕ
ጉም መሠረት ይፈጸም:: 4ዕዝራ፣ ነገሩ በእጅህ
ነው፤ ተነሥ! እኛም እንደግፍሃለን፤ በርትተ
ህም፤ አድርገው::

5ዕዝራም ተነሥቶ ዋና ዋናዎቹ ካህናት፣
ሌዋውያንና እስራኤል ሁሉ የቀረበውን ሐሳብ
እንዲፈጽሙ አስማላቸው፤ እነርሱም ማሉ::
6ከዚያም ዕዝራ ከእግዚአብሔር ቤት ፊት ተነሥቶ
ወደ ኤልያሴብ ልጅ ወደ ዮሐናን ክፍል ገባ፤
ምርኮኞቹ ታማኞች ሆነው ባለመገኘታቸው
ያለቅስ ነበር፤ በዚያም ምግብ አልቀመሰም፤
ውሃም አልጠጣም::

7ከዚያም ምርኮኞቹ ሁሉ በኢየሩሳሌም
እንዲሰበሰቡ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ዐዋጅ
ተነገረ፤ 8ዐዋጁም በሦስት ቀን ውስጥ ያልመጣ
ማንም ሰው በሹማምቱና በሽማግሌዎቹ ውሳኔ
መሠረት ንብረቱ ሁሉ እንዲወረስ፣ ራሱም
ከምርኮኞቹ ጉባኤ እንዲወገድ የሚያዝ ነበር::

9ስለዚህ በሦስት ቀን ውስጥ የይሁዳና
የብንያም ሰዎች ሁሉ፣ በኢየሩሳሌም ተሰበ
ሰቡ፤ በዘጠነኛው ወር በሃያኛውም ቀን ሕዝቡ
ሁሉ ስለ ወቅቱ ጉዳይና ስለ ከባዱ ዝናብ
በመጨነቅ በእግዚአብሔር ቤት ፊት ባለው
አደባባይ ተቀምጠው ነበር:: 10ከዚያም ካህኑ
ዕዝራ ተነሥቶ እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ ታማ
ኞች አልነበራችሁም፤ በእስራኤል በደል ላይ
በደል በመጨመር ባዕዳን ሴቶችን አገባችሁ::
11አሁንም ለአባቶቻችሁ አምላክ ለእግዚአብሔር
ተናዘዙ፤ ፈቃዱን ፈጽሙ፤ በዙሪያችሁ ካሉት
አሕዛብና ከባዕዳን ሚስቶቻችሁ ተለዩ::”

12ጉባኤውም ሁሉ እንዲህ ሲሉ በታላቅ
ድምፅ መለሱ፤ “እውነት ብለሃል፤ ያልኸውን
መፈጸም ይገባናል:: 13ይሁን እንጂ በዚህ የተሰበ
ሰበው ሕዝብ ብዙ ነው፤ ወቅቱም ክረምት
ነው፤ ስለዚህ ውጭ መቆም አንችልም፤ ከዚህም
በላይ በዚህ ነገር ብዙ ኀጢአት ስለ ሠራን፣
ይህ ጉዳይ በአንድና በሁለት ቀን የሚያልቅ
አይደለም:: 14ስለዚህ ሹሞቻችን በማኅበሩ ሁሉ
ምትክ መደረግ ያለበትን ያድርጉ:: ከዚያም
በዚህ የተነሣ የመጣው የአምላካችን ብርቱ
ቍጣ ከእኛ እስኪመለስ ድረስ፣ በየከተሞ
ቻችን ያሉ ባዕዳን ሴቶችን ያገቡ ሁሉ
በየከተማው ካሉት ሽማግሌዎችና ዳኞች ጋር

10፥2 ቍ26፤ ዘዳ30፥8-10፤ዕዝ9፥2
10፥3 ዘፀ34፥16፤ 2ነገ11፥17
10፥5 ነህ5፥12፤13፥25
10፥6 ዘፀ34፥28፤ ዘዳ9፥18፤መዝ102፥4፤ ዮና3፥7
10፥9 ዕዝ1፥5
10፥10 2ዜና28፥13፤ ዕዝ7፥21
10፥11 ዘዳ24፥1፤ ነህ9፥2፤ሚል2፥10-16
10፥12 ኢሱ6፥5
10፥14 ዘኍ25፥4፤ ዘዳ16፥18፤2ዜና29፥10

ሲሉ ለየት ያሉ ድርጊቶችን በማሳየት መልእክታቸውን ያስተላልፉ ነበር (ኢሳ 7፥3፤ 8፥1-4፡18፤ ኤር 13፥1-11፤ 19፤ 27፥2-12፤ ሕዝ 4፥1-5፥4 ይመ)፤

*10፥2፤ ዕዝራ አስተዋይ መምህር እንደ መሆኑ መጠን ምን መደረግ እንዳለበት፣ ውሳኔውን ለራሱ ለሕዝቡ ተወው::* ***ሴኬንያ፤*** ምናልባት በቍ 26 ላይ የተጠቀሰው ይሒኤል አባቱ ሳይሆን አይቀርም፤ ምክንያቱም በሁለቱም ቦታ የተጠቀሰው ሰው ከኤላም ወገን ነው:: ይህም ከሆነ፣ አባቱ አይሁዳዊት ያልሆነች ሴት በማግባቱ፣ ሴኬንያ በጣም አዝኖ ነበር ማለት ነው፤ ከኤላም ወገን ስድስት ሰዎች ከባዕዳን ወገን ሚስት አግብተው ነበር (ቍ 26)::

10፥3 ***ቃል ኪዳን እንግባ፤*** ይህ በዕብራይስጡ “ኪዳን እንቁረጥ” የሚል ትርጉም አለው (የዘፍ 15፥18 ማብ ይመ):: ***ሴቶችና ልጆቻቸውን፤*** ጋብቻ ፈርሶ ተጋቢዎች በሚለያዩበት ጊዜ፣ ልጆች ከእናታቸው ጋር እንዲቆዩ ይደረግ ነበር:: አጋር ከቤት በተባረረች ጊዜ፣ እስማኤል አብሮአት እንዲሄድ ተደርጎአል (ዘፍ 21፥14):: በሐሙራቢ ሕግ መሠረት፣ በባቢሎን ባላቸውን የፈቱ ሴቶች ሌላ ባል ከማግባታቸው በፊት ልጆቻቸው እስኪያድጉ ድረስ የመጠበቅ ግዴታ ነበረባቸው:: በግሪክ አገር የነበረው ልማድ ግን ከዚህ የተለየ ነው፤ ትዳር በሚፈርስበት ጊዜ፣ ልጆች ከአባታቸው ጋር እንዲቀመጡ ይደረግ ነበር::

10፥4 ***ተነሥ፤*** ዳዊት ከሰጠው ምክር ጋር ያነጻጽሩ (1ዜና 22፥16)::

10፥5 ***አስማላቸው፤*** እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ከሆነ፣ መሐላ አንድ ሰው የገባውን ቃል ሳይፈጽም ቢቀር፣ “እንዲህ ካላደርግህ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ያድርግብህ፤ ይህን ያን ይጨምርብህ...” የሚለውን ርግማን ያስከትላል (የ1ሳሙ 3፥17 ማብ ይመ):: አልፎ አልፎ ግን ርግማኑ የሚያስከትለው ነገር በግልጽ ይቀመጣል (ዘኍ 5፥19-22፤ ኢዮ 31፤ መዝ 7፥4-5፤ 137፥5-6)፡፡

10፥6 ***ክፍል፤*** ይህን የመሰለው የቤተ መቅደሱ ጓዳ ለዕቃ ማስቀመጫ ይሆን ነበር (8፥29፤ ነህ 13፥4-5):: ***ምግብ አልቀመሰም፤ ውሃም አልጠጣም፤*** ከምግብና ከውሃ ፈጽሞ መጾም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እምብዛም የተለመደ አይደለም:: ነገር ግን ሙሴ የዚህ ዐይነቱን ጾም ሁለት ጊዜ ጾሞአል (ዘፀ 34፥28፤ ዘዳ 9፥18)፤ የነነዌ ሰዎችም እንዲሁ ጾመው ነበር (ዮና 3፥7):: ሌሎችም ሰዎች ለምሳሌ ሐና (1ሳሙ 1፥7)፣ እንዲሁም ዳዊት (2ሳሙ 3፥35) ጾመው ነበር:: ***ያለቅስ ነበር፤*** ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል፣ ተገቢ የሆነ የፍርድ ቅጣት በሰው ላይ ሲመጣ የሚሰማውን ስሜት የሚገልጽ ነው (ዘፀ 33፥4፤ ዘኍ 14፥39 ይመ)::

*10፥7-8፤ ዕዝራ በጾምና በጸሎት ላይ ሳለ፣ የሕዝብ አለቆችና የአገር ሽማግሌዎች ምርኮኞቹ ሁሉ በኢየሩሳሌም እንዲሰበሰቡ አዘዙ:: ዕዝራ ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው ሰው ቢሆንም (7፥25-26)፣ ሥልጣኑን ሁሉ ከመጠቀም የተቈጠበና በአካሄዱም ለሕዝቡ መልካም አርአያ የሆነ ሰው ነበር::*

10፥8 ***በሦስት ቀን ውስጥ፤*** የይሁዳ ግዛት በጣም ተቀንሶ ስለ ነበር፣ ከሩቅ መጡ የሚባሉ ሰዎች እንኳ ቢበዛ ከ80 ኪ.ሜ በላይ አልተጓዙም:: የግዛት ወሰኑም በሰሜን እስከ ቤቴል፣ በደቡብ እስከ ቤርሳቤህ፣ በምሥራቅ እስከ ኢያሪኮ ድረስ ሲሆን፣ በምዕራብ በኩል ደግሞ እስከ ኦኖ ይደርስ ነበር (ከነህ 7፥26-38፤ 11፥25-35 ጋር ያነጻጽሩ):: ***እንዲወረስ፤*** ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል፣ “ለርኩሰት አገልግሎት ይውል የነበረውን ንብረት በመውረስ፣ ለእግዚአብሔር ሥራ ብቻ እንዲውል ማድረግ” የሚል ትርጉም አለው፤ ይኸውም ፈጽሞ በማጥፋት (ዘፀ 22፥20፤ ዘዳ 13፥12-18 እንዲሁም አማራጭ ትርጉሙን ይመ) ወይም ወደ እግዚአብሔር ግምጃ ቤት በማስገባት (ከዘሌ 27፥28፤ ከኢያ 6፥19፤ 7፥1-15 ጋር ያነጻጽሩ) ነበር::

10፥9 ***ይሁዳና ብንያም፤*** የ1፥5 ማብ ይመ:: ***አደባባይ፤*** ይህ ቦታ፣ ከቤተ መቅደሱ ውጭ ያለው አካባቢ ወይም “የውሃ በር” በመባል ከሚታወቀው መግቢያ (ነህ 8፥1) ፊት ለፊት ያለው ቦታ ሊሆን ይችላል:: ***ዝናብ፤*** ይህን ለመግለጽ የገባው በዕብራይስጡ ቃል የዝናቡን ክብደት የሚያሳይ ሲሆን እዚህ ላይ የተጠቀሰው ግን የዶፍን ዝናብ ለማ መልከት ሳይሆን አይቀርም:: ዘጠነኛው ወር ቂስሌቭ (ኅዳር/ታኅሣሥ) በዝናቡ ወቅት (ቍ 13) አጋማሽ ላይ ይውላል፤ ይኸውም በጥቅምት ወር ማክፉት ይጀምርና እስከ ሚያዝያ ወር አጋማሽ ድረስ ይዘልቃል፤ በታኅሣሥና በጥር ወር ኢየሩሳሌምና አካባቢው ቀዝቃዛ ይሆናል፤ ሕዝቡም ይንቀጠቀጥ የነበረው ዝናቡ ስላበሰበሰው ብቻ ሳይሆን፣ ዝናቡ ከባድ ስለነበር የእግዚአብሔር ቍጣ ይሆናል ብለው ሳይፈሩ አልቀሩም (1ሳሙ 12፥17-18፤ ሕዝ 13፥11፡13 ይመ)::

10፥10 ***በእስራኤል በደል ላይ በደል በመጨመር፤*** ዘፀ 9፥34፤ መሳ 3፥12፤ 4፥1፤ 2ዜና 28፥13 ይመ:: ከምርኮ የተመለሱት አይሁድ ኀጢአታቸውና ውድቀታቸው ታላቅ ሆኖ ሳለ፣ ይህም አነሰ ብለው የአሕዛብን ሴቶች በማግባት በበደል ላይ በደል ጨመሩ::

10፥11 ***ተለዩ፤*** ዘኍ 16፥21፤ 2ቆሮ 6፥14 ይመ::

10፥12 በታላቅ ድምፅ፤ ነህ 9፥4 ይመ::

10፥14 ***በየከተማው ካሉት ሽማግሌዎች፤*** ዘዳ 16፥18፤

በተወሰነው ቀን ይምጡ።” [15]ይህንንም ነገር
የተቃወሙት ከሜሱላምና ከሌዋዊው ከሳባታይ
ድጋፍ ያገኙት የአሣሄል ልጅ ዮናታንና የቴ
ቁዋ ልጅ የሕዝያ ብቻ ናቸው።
[16]ስለዚህ ምርኮኞቹ እንደ ተባለው አደረጉ፤
ካህኑ ዕዝራም ከእያንዳንዱ የቤተ ሰብ ምድብ
አንዳንድ የቤተ ሰብ ኀላፊ የሆነ ሰው መረጠ፤
ሁሉም በየስማቸው ተመዘገቡ። ከዚያም በዐ
ሥረኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ጒዳዩን
ለመመርመር ተቀመጡ፤ [17]በመጀመሪያው
ወር በመጀመሪያው ቀን ባዕዳን ሴቶችን ያገቡ
ትን ወንዶች ሁሉ አጣርተው ጨረሱ።

## ከባዕዳን ሴቶች ጋር የተጋቡት ሰዎች

[18]ከካህናት ዘሮች መካከል ባዕዳን ሴቶ
ችን ያገቡት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤
ከኢዮሴዴቅ ልጅ ከኢያሱ ዘሮችና ከወንድ
ሞቹ መካከል፤ መዕሤያ፣ አልዓዛር፣ ያሪብና
ጎዶልያስ። [19]እነዚህ ሁሉ ሚስቶቻቸውን
ለመፍታት ቃል በመግባት እጃቸውን ሰጡ፤
ስለ በደላቸውም እያንዳንዳቸው ከመንጋው
አንዳንድ አውራ በግ ለበደል መሥዋዕት
አቀረቡ።

[20]ከኢሜር ዘሮች፤
አናኒና ዝባድያ።
[21]ከካሪም ዘሮች፤
መዕሤያ፣ ኤልያስ፣ ሽማያ፣ ይሒኤ
ልና ዖዝያ።
[22]ከፋስኩር ዘሮች፤
ኤልዮዔናይ፣ መዕሤያ፣ ይስማኤል፣
ናትናኤል፣ ዮዛባትና ኤልዓሣ።
[23]ከሌዋውያኑም መካከል፤
ዮዛባት፣ ሰሜኢ፣ ቆሊጣስ የሚባል
ቆልያ፣ ፈታያ፣ ይሁዳ፣ አልዓዛር።
[24]ከመዘምራኑም መካከል፤
ኤልያሴብ። ከበር ጠባቂቹም፣ ሰሎም፣
ጤሌም፣ ኡሪ።
[25]ከሌሎቹ እስራኤላውያን መካከል፤
ከፋሮስ ዘሮች፤ ራምያ፣ ይዝያ፣ መልክያ፣
ሚያሚን፣ አልዓዛር፣ መልክያና በናያስ።

10፥15 ነህ11፥16
10፥18 መሳ3፥6፤ዕዝ2፥2
10፥19 ዘሌ5፥15፤
6፥6፤2ነገ10፥15
10፥20 1ዜና24፥14
10፥21 1ዜና24፥8
10፥22 1ዜና9፥12
10፥23 ነህ8፥7፤9፥4
10፥24 ነህ3፥1፤
12፥10፤13፥7፡28
10፥25 ዕዝ2፥3
10፥26 ቍ28፥3
1ዜና3፥22፤ዕዝ2፥3

[26]ከኤላም ዘሮች፤
መታንያ፣ ዘካርያስ፣ ይሒኤል፣ አብዲ፣
ይሬሞትና ኤልያ።
[27]ከዛቱዕ ዘሮች፤
ዔሊዮዔናይ፣ ኢልያሴብ፣ መታንያ፣
ይሬሞት፣ ዛባድና ዓዚዛ።
[28]ከቤባይ ዘሮች፤
ይሆሐናን፣ ሐናንያ፣ ዛባይና
አጥላይ።
[29]ከባኒ ዘሮች፤
ሜሱላም፣ መሉክ፣ ዓዳያ፣ ያሱብ፣
ሸዓልና ራሞት።
[30]ከፈሐት ሞዓብ ዘሮች፤
ዓድና፣ ክላል፣ በናያስ፣ መዕሤያ፣
መታንያ፣ ባስልኤል፣ ቢንዊና ምናሴ።
[31]ከካሪም ዘሮች፤
አልዓዛር፣ ይሺያ፣ መልክያ፣ ሽማያ፣
ስምዖን፣ [32]ብንያም፣ መሉክና ሰማራያ።
[33]ከሐሱም ዘሮች፤
መትናይ፣ መተታ፣ ዛባድ፣ ኤሊፋላት፣
ይሬማይ፣ ምናሴና ሰሜኢ።
[34]ከባኒ ዘሮች፤
መዕዳይ፣ ዓምራም፣ ኡኤል፣ [35]በናያስ፣
ቤድያ፣ ኬልቅያ፣ [36]ወንያ፣ ሜሪሞት፣
ኤልያሴብ፣ [37]መታንያ፣ መትናይና
የዕሡ።
[38]ከቢንዊ ዘሮች፤
ሰሜኢ[f]፣ [39]ሰሌምያ፣ ናታን፣ ዓዳያ፣
[40]መክነድባይ፣ ሲሲይ፣ ሸራይ፣ [41]ኤዝር
ኤል፣ ሰሌምያ፣ ሰማራያ፣ [42]ሰሎም፣
አማርያና ዮሴፍ።
[43]ከናባው ዘሮች፤
ይዒኤል፣ መቲትያ፣ ዛባድ፣ ዘቢና፣
ያዳይ፣ ኢዮኤልና በናያስ።
[44]እነዚህ ሁሉ ባዕዳን ሴቶችን ያገቡ ናቸው፤
ከእነርሱም ጥቂቶቹ ከእነዚህ ሴቶች[k] ልጆችን
ወልደው ነበር።

[f]37:38 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም (እንዲሁም መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል 9፣34) ይመ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *የዕሡ፣ ባኒና ቤኑዊ* ይላል።
[k]44 ወይም *ከልጆቻቸው ጋር ላኩአቸው*

19፥12፤ 21፥3፡19፤ ሩት 4፥2 ይመ።

*10፥15*፤ እነዚህ አራት ሰዎች ይህን እርምጃ የተቃወሙት፣ ምናልባት ሊደርስ ከሚችል አስፈሪ ሁኔታ ራሳቸውን ወይንም ዘመዶቻቸውን ለመጠበቅ ብለው ይሆናል፤ ወይም እርምጃው በጭካኔ የተሞላ ነው ብለው አስበው ይሆናል። *ቴቁዋ*፤ የስሙ ትርጒም፣ “ተስፋ” ማለት ሲሆን፣ ቃሉ በሌላ ስፍራ የሚገኘው በ2ነገ 22፥14 ላይ ብቻ ነው። *የሕዝያ*፤ የስሙ ትርጒም፣ “እግዚአብሔር ይይ” ማለት ሲሆን፣ የሚገኘውም እዚሁ ላይ ብቻ ነው። *ሜሱላም*፤ የ8፥16 ማብ ይመ። በቁ 29 ላይ የተጠቀሰው ሜሱላም ከሆነ፣ እርሱ ራሱ ከአሕዛብ ወገን ሚስት አግብቶአል ማለት ነው። *ሳባታይ*፤ ይህ ስም ተጠቀሶ የሚገኘው እዚህ ላይና በነህ 8፥7፤ እንዲሁም 11፥16 ላይ ብቻ ነው፤ የስሙ ትርጒም ፣ “በሰንበት ቀን የተወለደ” ማለት ሊሆን ይቻላል።

*10፥16-17*፤ የተመረጡት ሰዎች ኀላፊነታቸውን የተወጡት በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ነበር፤ ይኸውም 110 ያህል ወንዶች ከአሕዛብ ወገን ሚስት በማግባት በደል ፈጽመው ተገኝተዋል።

*10፥18-22*፤ 2፥36-39 ይመ።

10፥19 *እጃቸውን ሰጡ*፤ እጅ ለእጅ መጨባበጥ የሚሰጠው ትእምርት ምን እንደሆን 2ነገ 10፥15፤ ሕዝ 17፥18 ይመ። *አውራ በግ* የበደል መሥዋዕት የሚቀርበው ሳይታሰብ ድንገት ለተፈጸመ ኀጢአት ነበር (ዘሌ 5፥14-19)፤ እንዲሁም ሆን ተብሎ ለተፈጸመ ኀጢአትም ሊቀርብ ይችላል (ዘሌ 6፥1-7) ታዲያ ለሁለቱም ተገቢ መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበው አውራ በግ ነበር (ዘሌ 5፥15፤6፥6)።

*10፥24*፤ አንድ ዘማሪና ሦስት በር ጠባቂዎች ብቻ ከባዕዳን ወገን ማግባታቸው አስደናቂ ነው፤ ከቤተ መቅደሱ አገልጋዮች (2፥43-54) ወይም ከሰሎሞን አገልጋዮች ዝርያ (2፥55-57) መካከል አንድም ሰው ከአሕዛብ ጋር በመጋባት በደል የፈጸመ አልነበረም።

*10፥25-43*፤ 2፥3-20 ይመ።

10፥30 *ባስልኤል*፤ ከዘፀ 31፥2 ጋር ያነጻጽሩ።

10፥31 *ስምዖን*፤ ይህን ስም ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ስም ከያዕቆብ ሁለተኛ ልጅ ከስምዖን ስም ጋር አንድ ነው፤ ትርጒሙም “የሚሰማ” ማለት ነው።

10፥43 *ናባው*፤ በዕብራይስጥ ስሙ የሚጻፈው በዚህ ዐይነት ሲሆን፣ የመጣውም ናቡ ከሚባል የባቢሎናውያን ጣዖት ስም ነው (ኢሳ 46፥1 ይመ)፤ የሰው ስም ሆኖ የገባው እዚህ ላይ ብቻ ነው።

*10፥44*፤ ከአሕዛብ ሴቶች ጋር ጋብቻ ከፈጸሙት ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ልጆች አፍርተው ነበር፤ ነገር ግን ይህ እንደ ምክንያት ተቈጥሮ ፍቺውን ማስቀረት አይችልም። አማራጭ ትርጒሙን ይመ።